Geography in Amharic.
From the Chh. Miss^y Soc^y.
Presented at Comm^ee Meet^g
Aug^t 1. 1842.

# ጌዎግራፊያ ፡

## የምድር ፡ ትምህርት ።

La Ethiop
G345

[Geography]

# ጌዎግራፊያ ፡

ማለት ፡

# የምድር ፡ ትምህርት ።

ላበሻ ፡ ተማሮች ፡ ለረባቸው ፡ ተጻፈች ፡

በእንግሊዝም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሚስዮን ፡ ጉባኤዋ ፡ ፈቃድ ፡

ታተመች ፡

410148
24.2.43

በሎንደን ፡ በእንግጣር ፡ ከተማ ፡ ከዚያም ፡ በሪቸርድ ፡
ወትስ ፡ ማኅተምያ ፡ በልደት ፡ አመት ፡ ፲፰፻፵፩።

[1841]

# መቅድም ::

በአብና ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ስም ፡ አንድ ፡
አምላክ ፡፡ አሜን ::

ወደጄ ፡ ተማሪና ፡ አንባቢ ፡ ሆይ ፡፡ ይህችን ፡ መጽሐፍ ፡ እነሆ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ረዴት ፡ ጻፍሁልህ ፡ የምድርን ፡ ትምርት ፡ ተምረህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጥበብና ፡ ፍቅር ፡ ታይ ፡ ዘንድ ፡ እንዴህ ፡ ያለውን ፡ መኖርያ ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ፈጥርዋልና ፡ አሕዛብንም ፡ ሁሉን ፡ በየምድራቸው ፡ አስቀምጥዋልና ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሁነው ፡ የሚመጣውን ፡ ዓለምን ፡ ደህንነት ፡ ይሹ ፡ ዘንድ ፡ በክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡፡ ይህችን ፡ መጽሐፍ ፡ በጣም ፡ ብትማር ፡ በቤት ፡ ተቀምጠህ ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ እንደሚሔድ ፡ ሰው ፡ ትሆናለህ ፡ በቀድሞም ፡ ስማቸውን ፡ እንኳ ፡ ያልሰማሀውን ፡ አሕዛብ ፡ መኖርያቸውን ፡ ጠባያቸውንም ፡ ስራቸውንም ፡ ንብረታቸውንም ፡ ከዚህ ፡ ታገኛለህ ፡፡ ሁላቸውም ፡ ወንድሞችህ ፡ ናቸው ፡ ሁላቸውም ፡ ታላቆችና ፡ ታናሾች ፡ ብልሃተኞችና ፡ አሬዊትም ፡ በጎችና ፡ ክፎችም ፡ ዘመደችህ ፡ ያባትህ ፡ የአደም ፡ ልጆች ፡፡ እወቃቸው ፡ ተማርባቸውም ፡ ስራቸውንም ፡ መርመር ፡ የምታገኝባቸውንም ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ ጠብቅ ፡ ክክፉም ፡ ሽሽ ፡፡ ሁላቸውንም ፡ ውደድ ፡ ነፍስህን ፡ ትወድ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደሚሻ ፡፡ ከ

## መቅድም ፡፡

ሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ነፍስህን ፡ ጥየቅ ፡ እንዴህ ፡ ብለህ ፡፡ እግ ዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ፈጠረኝ ፡፡ የአግዚአብሔርም ፡ ፈ ቃድ ፡ በኔ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡፡ እኔም ፡ እንዴት ፡ አፈጽማለ ሁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡፡ ምንድርም ፡ ነው ፡ የእግ ዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ በሕዝቢ ፡ በወገኖቼም ፡፡ እኛም ፡ የሐ በሻ ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሻብን ፡ እናድርገዋለን ን ፡፡ ባላደረግነውም ፡ ምን ፡ ይገባናል ፡ እንጊዴህ ፡ እናድር ግ ፡ ዘንድ ፡፡ እንዴሁም ፡ ብትጠይቅ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በጣም ፡ ይመልስልሃል ፡ እርሱንም ፡ ስማ ፡ ተከተለውም ፡፡ አሜን ፡፡

የእግዚአብሔርንም ፡ በረከት ፡ ይለምንልሃል ፡ ወደጅህ ፡

ቻርልስ ፡ ዊልየም ፡ ኢዘንበርግ ፡
የወንጌል ፡ መለክተኛ ፡፡

# መክፈቻ ፡

ላያሌ ፡ በዚች ፡ መጽሐፍ ፡ ላሉ ፡ ምልክቶች ፡ ለታጸረ
ም ፡ በሀበሻም ፡ ላልታወቁ ፡ ቃላት ፡፡

° ኣርዝ ፡ ማለቱ ፡ ማዕረግ ፡፡ ዙርያ ፡ ሁሉ ፡ በ፫፷፤ በተካ
ከሉ ፡ ክፍሎች ፡ ይከፈላል ፡ ክፍልም ፡ ሁሉ ፡ ኣርዝ ፡ ወ
ይስ ፡ ማዕረግ ፡ ይባላል ፡፡ የምድር ፡ ኣርዞች ፡ መኻከለኛ ፡
ርዝመት ፡ ፷፱፤ ሚላ ፡ ወይስ ፡ ለግረኛ ፡ የሶስት ፡ ቀን ፡ ተኩ
ል ፡ መንገድ ፡ ነው ፡፡ ፬°፤ ማለት ፡ ኣራት ፡ ኣርዝ ፡ ነው ፡፡

′ደ ቂ ቅ ፡ የሰዓት ፡ ክፍል ፡ ከ፷፤ ኣንድ ፡፡ በጌዎግራፊያ
ም ፡ ኣርዝ ፡ ደግሞ ፡ በ፷፤ ክፍል ፡ ይከፈላል ፡ ክፍልም ፡
ሁሉ ፡ ደቂቅ ፡ ይባላል ፡፡ ፲′፤ ማለቱ ፡ ኣሥር ፡ ደቂቅ ፡ ማለ
ት ፡ ነው ፡፡

—፡ እስከ ፡ ድረስ ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ ፴°፤ — ፵°፤ ማለት ፡ ከ
ሠላሳ ፡ ኣርዝ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ኣርባ ፡ ኣርዝ ፡ ድረስ ፡ ነው ፡፡

ስ ፡ ማለቱ ፡ ስፍራ ፡ በኣርዝና ፡ በደቂቅ ፡ ተሰፍሮ ፡ እን
ደ ፡ ታወቀ ፡፡

ወ ፡ ወሰን ፡፡

ታት ፡ ታላቅነት ፡፡ ታ ፡ ታላቅ ፡ ወይስ ፡ ታላቆች ፡፡

ወድ ፡ ወርድ ፡ የስፍራ ፡ ርቀት ፡ ካስተካካይ ፡ ወደ ፡ ሰ
ሜን ፡ ወይስ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡፡

ርት ፡ ርዝመት ፡ የስፍራ ፡ ርቀት ፡ በግሪኒች ፡ ከሚያልፍ ፡
ከመጀመርያ ፡ ሜሪዲያን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ወይስ ፡ ወደ ፡
ምዕራብ ፡፡

ምቅ ፡ ምሥራቅ ፡፡ ሰ ፡ ሰሜን ፡፡

ምብ ፡ ምዕራብ ፡፡ ደ ፡ ደቡብ ፡፡

ሚ ላ ፡ የርቀት ፡ መስፈርያ ፡፡ ኣንድ ፡ ኣርዝ ፡ ፷፱፤ ሚላ ፡
እንግሊዝ ፡ ኣለው ፡ ወይስ ፡ ፲፭፤ ሚላ ፡ ንምሳዊ ፡፡ በዚች ፡
መጽሐፍ ፡ ሚላ ፡ ሲል ፡ ሚላ ፡ እንግሊዝ ፡ ነው ፡ እርሱም ፡
፱፷፪፤ እርምጃ ፡ ኣለው ፡፡

ሚ ልዮ ን ፡ ቍጥር ፡ ነው ፡ መቶ ፡ እልፍ ፡፡

# መክፈቻ ።

ቢብልዮቴካ ፡ ማለት ፡ የመጻሕፍት ፡ መሰብሰቢያ ፡ ነው ።

ኡኒቬርሲታስ ፡ ታላቅ ፡ ማስተማርያ ፡ ነው ፡ ለቀሳውስት ፡ ለሕጋውያንም ፡ ለባለ ፡ መድኃኒቶችም ፡ ለፊሎሶፎችም ።

ኮለጅና ፡ አክዴሚያ ፡ ግምናስዩምም ፡ የታላቆች ፡ ማስተማርዮች ፡ አይነት ፡ ናቸው ፡ ከኡኒቬርሲታስ ፡ ግን ፡ ያንሳሉ ።

ሜትሮጶሊታን ፡ ማለት ፡ መጀመርያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ነው ፡ አንደ ፡ መጥራን ። በግእዝም ፡ መጥረብሊጥ ፡ ማለቱ ፡ ጳጳስ ፡ ይባላል ።

ሚስዮን ፡ ማለት ፡ መልእክት ፡ ነው ። የሚስዮን ፡ ጉባኤ ፡ ማለት ፡ የምድርን ፡ አሕዛብ ፡ በወንጌል ፡ ለማስተማር ፡ የክርስቶስንም ፡ እውቀት ፡ በመኻከላቸው ፡ ለመዘረጋት ፡ ቀሳውስትንና ፡ መምህራንን ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ የሚልኩ ፡ የተገናኙ ፡ በፈቃደቸውም ፡ ለጉባኤ ፡ ክርስቲያን ።

የቀረ ፡ መሥጢር ፡ ሁሉ ፡ መምህር ፡ ሊፈታ ፡ ነው ።

## ጊዎግራፊያ ፡

## የምድር ፡ ትምህርት ፡፡

ጊዎግራፊያ ፡ በ፫፡ ክፍል ፡ ትከፈላለች ፡፡

፩፡ ክፍል ፡፡ ጊዎግራፊያ ፡ መትማቲቄ ፡፡
፪፡ . . . . . . . . . . . ፊሲቄ ፡፡
፫፡ . . . . . . . . . . . ጶሊቲቄ ፡፡

## መጀመርያ ፡ ክፍል ፡፡

### ጌዎግራፊያ ፡ መትማቲቄ ፡፡

ጊዎግራፊያ ፡ መትማቲቄ ፡ ታስተምረናለች ፡ ምድሪቱን ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ገጠመች ፡ ከሌላ ፡ ካለም ፡ ፍጥረት ፡ ከፀሐይና ፡ ከጨረቃ ፡ ከከዋክብትም ፡ ጋራ ፡፡ የምድርንም ፡ ታላቅነት ፡ ታስታውቀናለች ፡፡


ያለምም ፡ ፍጥረት ፡ እጅግ ፡ ነው ፡ ቍጥርንም ፡ አጣ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ እርሱ ፡ ኃይሉን ፡ ጥበቡንም ፡ ታላቅነቱንም ፡ ፍቅሩንም ፡ ለመግለጽ ፡ የፈጠራቸው ፡ ሁላቸውን ፡ ያውቃል ፡ በየስማቸውም ፡ ይጸራቸዋል ፡፡ ይሳይያስ ፡ ፵፡ ፳፮፡፡ እኛ ፡ የምናውቀው ፡ ከከዋክብት ፡ ነገር ፡ ጥቂት ፡ ነው ፡፡ አዋቆችም ፡ እንኳ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይማሩበታል ፡፡ በሚማሩም ፡ መጠን ፡ እጅግ ፡ በቀድም ፡ ያልታወቀውን ፡ ነገር ፡ ያገኙሉ ፡፡

ከዋክብትንም ፡ ሁሉን ፡ በ፫፡ ወገን ፡ እንከፍላለን ፡፡ እርሳቸውም ፡

፩፡ የሚጸኑ ፡ ከዋክብት ፡ ስፍራቸውን ፡ የማይለውጡ ፡ ብርሃናቸውም ፡ በየራሳቸው ፡ ያላቸው ፡፡

፪፡ ጵላኔቶች ፡ ማለት ፡ በየሥርዓታቸው ፡ የሚዞሩ ፡ ስፍራቸውንም ፡ ወትሩ ፡ የሚለውጡ ፡ በየራሳቸውም ፡ ተጨልመው ፡ ብርሃናቸውን ፡ ከፀሐይ ፡ የሚቀበሉ ፡ ከዋክብት ፡፡

፫፡ ኮሜቶች ፡ ጅራት ፡ ያላቸው ፡ ከዋክብት ፡፡




የምድርም ፡ ክብነት ፡ ከዚህ ፡ ይገለጻል ። ፩፡ የምድር ፡ ጽላ ፡ በጨረቃ ፡ ቢታይ ፡ ክብ ፡ ነው ። ፪፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ የፀሓይ ፡ መውጣትና ፡ መግባት ፡ ይቀድማቸዋል ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ከሚኖሩ ፡ በፊት ። ፫፡ የከዋክብት ፡ ሁሉ ፡ መልክ ፡ አረርን ፡ ይመስላል ። ፬፡ በምድር ፡ ከፍ ፡ በሚል ፡ ስፍራ ፡ ብንወጣ ፡ ማየታችን ፡ ይስፋል ፡ በመውጣታችን ፡ መጠን ። ፭፡ ማየታችን ፡ በሌላ ፡ ነገር ፡ ባይከለከል ፡ የምናየው ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ክብ ፡ ሁኖ ፡ ይታያል ። ፮፡ ካመት ፡ ፲፭፻፲፱፡ ጀምሮ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ምድ

ርን ፡ በመርከብ ፡ ሰረው ፡ ዞርዋት ፡፡ የሰረሩትንም ፡ መንገ
ዳቸውን ፡ አቀንተው ፡ ወደ ፡ ፊታቸው ፡ ሲሔዱ ፡ ሳይለው
ጡትም ፡ በመጨረሻ ፡ ወትረ ፡ ወደ ፡ ጀመሩበት ፡ ስፍራ ፡
ደረሱ ፡፡ ፯፡፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ከሚሔዱ ፡ መርከቦች ፡ ላይን ፡
በመጀመርያ ፡ የሚጠፋ ፡ ነገር ፡ የታችኛ ፡ መርከብ ፡ ነው ፡
በኋላም ፡ ደክሎች ፡ ይጠፋሉ ፡፡ ከሚመጡም ፡ መርከቦ
ች ፡ ደክሎች ፡ በፊት ፡ ይታያሉ ፡ መርከቦችም ፡ በኋላ ፡፡

## የምድር ፡ መኻከለኛ ፡ ልክ ፡፡ ዞዲያኮስ ፡፡ የምላሽ ፡ ዙርያ ፡፡ ሖሪዞን ፡፡ ፬፡ ማዕዝን ፡፡ አርዞች ፡፡

ምድርን ፡ በመዞር ፡ የፊትዋ ፡ ታላቅነት ፡ ተገኘ ፡፡ ዙርያዋ
ም ፡ ፳፬፡ ሺህ ፡ ፱፻፩፡ ሚላ ፡ ነው ፡፡ ይህም ፡ ለግረኛ ፡ መንገ
ድ ፡ ከሆነ ፡ የሺህ ፡ ተስማንያ ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ቢሆን ፡፡ የ
ምድርም ፡ መኻከለኛ ፡ ልክ ፡ ፯፱፻፡፡ ሚላ ፡ ያህላል ፡፡ ምድ
ርም ፡ ያለ ፡ መለወጥ ፡ በየ፳፬፡ ሰዓት ፡ ከምዕራብ ፡ ወደ ፡
ምሥራቅ ፡ አድርጋ ፡ በራስዋ ፡ ትዞራለች ፡ እንዲሁም ፡ ቀን
ና ፡ ሌሊት ፡ ይሆናሉ ፡፡ ምድር ፡ ደግሞ ፡ ባንድ ፡ አመት ፡ ከ
ጨረቃ ፡ ጋራ ፡ ፀሓይን ፡ ትዞራለች ፡፡ ምድርም ፡ እንዴህ ፡ ስ
ትዞር ፡ ፀሓይ ፡ የሚዞር ፡ ይመስላል ፡ በውነት ፡ ግን ፡ ምድ
ር ፡ ትዞራለች ፡፡

ፀሓይም ፡ እንዴህ ፡ ዙሮ ፡ ሲመስል ፡ ፲፪፡ የከዋክብትን ፡
ምልክቶች ፡ ዞዲያኮስ ፡ የሚሉትን ፡ ያልፋል ፡፡ እርሳቸው
ም ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡

ሚዛን ፡፡ ♎ ፡፡ ጊንጥ ፡፡ ♏ ፡፡ ወርዋሪ ፡፡ ♐ ፡፡ ዋላ ፡፡ ♑ ፡፡
ወኃዊ ፡፡ ♒ ፡፡ ዓሦች ፡፡ ♓ ፡፡ ደንገሌ ፡፡ ♈ ፡፡ ወይፈን ፡፡ ♉ ፡፡
መንታ ፡፡ ♊ ፡፡ ከንክር ፡፡ ♋ ፡፡ አንበሳ ፡፡ ♌ ፡፡ ቆንጆ ፡፡ ♍ ፡፡
ፀሓይም ፡ ወደ ፡ ከንክር ፡ ምልክት ፡ ሲገባ ፡ በኛ ፡ በኩል ፡
ቀን ፡ ይረዝማል ፡ በምድር ፡ ሁለተኛ ፡ እኩሌታ ፡ ግን ፡ ያ
ጽራል ፡፡ ወደ ፡ ዋላም ፡ ምልክት ፡ ሲገባ ፡ የኩሌታችን ፡ ቀ
ን ፡ ያጽራል ፡ የሁለተኛ ፡ እኩሌታ ፡ ቀን ፡ ግን ፡ ይረዝማል ፡፡
በሌህ ፡ ሁለት ፡ ምልክቶች ፡ ፀሓይ ፡ ገብቶባቸው ፡ መመለ
ስ ፡ ይመስላልና ፡ ይህ ፡ የ ፀ ሓ ይ ፡ ም ላ ሽ ፡ ይባላል ፡፡ በም
ላሹም ፡ በኩል ፡ ያለ ፡ የምድር ፡ ዙርያ ፡ የ መ ላ ሽ ፡ ዙ ር
ያ ፡ ይባላል ፡፡ ከርሳቸውም ፡ አንዱ ፡ የ ከ ን ክ ር ፡ ምላሽ ፡

ዙርያ ፡ ነው ፡ አንዲም ፡ የዋላ ፡ ምላሽ ፡ ዙርያ ፡፡

ከፉ ፡ በሚል ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ብንቆም ፡ ሰማይ ፡ ክረቅ ፡ ክብ ፡ ሁኖ ፡ ምድርን ፡ የሚወስን ፡ ይመስላል ፡፡ ይህም ፡ የማየት ፡ ዙርያ ፡ ወይስ ፡ ሖሪዞን ፡ ይባላል ፡፡ እኛም ፡ በመኻከሉ ፡ ነን ፡፡ ይህም ፡ በ፫፻፷፤ በተካከሉ ፡ ክፍሎች ፡ ይከፈላል ፡ አርዝ ፡ አይተባሉ ፡፡ ከዚህ ፡ መክፈልም ፡ በቀር ፡ ሖሪዞን ፡ ደግሞ ፡ በአራት ፡ ክፍል ፡ ይከፈላል ፡፡ እርሳቸውም ፡ ያለም ፡ ወይስ ፡ የሰማይ ፡ ፬፤ ማዕዝንት ፡ ይባላሉ ፡ ስማቸውም ፡ ምሥራቅ ፡ ምዕራብም ፡ ሰሜንም ፡ ደቡብም ፡፡ ክፍልም ፡ ሁሉ ፡ ከየባልንጀራው ፡ ፺፤ አርዝ ፡ ይርቃል ፡፡ እሊህ ፡ ፬፤ ክፍሎች ፡ ደግመው ፡ ይከፈላሉ ፡ በመርከቦችም ፡ ፫፻፷፤ ክፍል ፡ አላቸው ፡ መንገዳቸውንና ፡ ንፋሳቸውን ፡ በጣም ፡ ያውቁበት ፡ ዘንድ ፡ ብለው ፡፡ ይህ ፡ መክፈልም ፡ ከመግኔትስ ፡ መርፌም ፡ ጋራ ፡ የተገኘበት ፡ እቃ ፡ ደር ፡ ይባላል ፡፡ ለመርከብም ፡ ለመንገደኛም ፡ እንደ ፡ መሪ ፡ ያገለግላል ፡፡

የምድር ፡ አረር ፡ አስተካካይ ፡ በሚሉት ፡ መስምር ፡ በሁለት ፡ እኩሌቶች ፡ ይከፈላል ፡፡ አንደኛቱም ፡ የሰሜን ፡ እኩሌታ ፡ አንደኛቱም ፡ የደቡብ ፡ እኩሌታ ፡ ናት ፡፡ አስተካካይ ፡ በሰሜንና ፡ በደቡብ ፡ መኻከል ፡ ረጥዋልና ፡ ፪፤ እኩሌቶች ፡ በጣም ፡ የተካከሉ ፡ ይሆናሉ ፡፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ በሰሜንና ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ አያሌ ፡ መስምሮች ፡ አሉ ፡ እንደርሱ ፡ የሚሮጡ ፡ እርሳቸውም ፡ ጳራሌል ፡ ዙርያ ፡ ይባላሉ ፡፡ እንዲሁም ፡ የከንክርና ፡ የዋላ ፡ ምላሽ ፡ ዙርያ ፡ የመውጫም ፡ ፪፤ ዙርያ ፡፡ የምላሽም ፡ ዙርያ ፡ ኢያንዳንዱ ፡ ፳፫፤ አርዝ ፡ ተኩል ፡ ካስተካካይ ፡ ይርቃል ፡፡ አስተካካይ ፡ ግን ፡ ከጳራሌል ፡ ዙርያ ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ መረዲያኖች ፡ በሚባሉ ፡ ከሰሜን ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ በሚሮጡ ፡ መስምሮች ፡ ቀንተው ፡ ይቈረጣሉ ፡፡ መሪዲያንም ፡ ሁሉ ፡ በየስፍራው ፡ ምድርን ፡ በምሥራቅና ፡ በምዕራብ ፡ ይከፍላል ፡፡

## የምድር ፡ ወርድና ፡ ርዝመት ፡፡

የስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ርቀት ፡ ካስተካካይ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ወይስ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ወርዲ ፡ ይባላል ፡፡ ርቀቱም ፡ ከመጀመር

ያ ፡ መሪደ.ያን ፡ ርዝመቱ ፡ ነው ፡፡ የስፍራም ፡ ወርድ ፡ ካስ
ተካካይ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ቢኖር ፡ የሰሜን ፡ ወርድ ፡ ይባላ
ል ፡፡ ወደ ፡ ደቡብም ፡ ቢኖር ፡ የደቡብ ፡ ወርድ ፡ አለው ፡፡ የ
ወርድም ፡ አርዝ ፡ ሁሉ ፡ በመሪደ.ያን ፡ ይቈጠራል ፡፡ የርዝ
መትም ፡ አርዝ ፡ ባስተካካይ ፡፡ የመውጫ ፡ ከፍታ ፡ ባን
ድ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ የስፍራ ፡ መውጫ ፡ ከፍታ ፡ ይባላል ፡ እ
ርሱም ፡ ከወርደ. ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡፡ ካንድ ፡ መሪደ.ያ
ን ፡ በታች ፡ ያለ ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ርዝመቱና ፡ ቀትሩ ፡ አን
ድ ፡ ነው ፡፡

## የምድር ፡ ዞና ፡ ወይስ ፡ መታጠቅያ ፡፡

ምድር ፡ በፀሓይ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በምትኖር ፡ መጠን ፡ ባም
ስት ፡ ዞና ፡ ወይስ ፡ መታጠቅያ ፡ በሚሉት ፡ ክፍል ፡ ትከ
ፈላለች ፡፡ የምድርን ፡ አረር ፡ እንደ ፡ መታጠቅያ ፡ ከብዋታ
ልና ፡፡ በሁለት ፡ ምላሽ ፡ ዙርያ ፡ መኻከል ፡ ያለች ፡ ምድ
ር ፡ ሁሉ ፡ ትኵስ ፡ ዞና ፡ ትባላለች ፡፡ የፀሓይ ፡ ብልጭታ ፡
በራስዋ ፡ ላይ ፡ ጰርጰንደ.ኩላሪተር ፡ ቀንቶ ፡ ይወድቅባታል
ና ፡፡ ፀሓይም ፡ እጅግ ፡ ትኵሶባታልና ፡፡ የዚህም ፡ ዞና ፡ ወ
ርድ ፡ ፵፯፤ አርዝ ፡ ነው ፡፡ በየመውጫና ፡ በየመውጫ ፡ ዙ
ርያ ፡ መኻከልም ፡ ያለ ፡ ስፍራ ፡ የውርጭ ፡ ዞና ፡ ይባላል ፡፡
ፀሓይ ፡ ካጠገቡ ፡ አድርጎ ፡ ኦብሊኩተር ፡ ያበራዋልና ፡ አያ
ሞቀውምም ፡፡ በየብርድና ፡ በትኵስ ፡ ዞና ፡ መኻከልም ፡
ወደ ፡ ሰሜንና ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ አንድ ፡ መኻከለኛ ፡ የሚባ
ል ፡ ዞና ፡ [illegible] ፡ ትኵሳትና ፡ ብርድ ፡ በርሱ ፡ መኻከለኛ ፡ ነ
ው[illegible] እንዲሁም ፡ የምድር ፡ ትኵሳትና ፡ ብርድ ፡ ይበዛል
ና ፡ ያንሳል ፡፡ ቀንና ፡ ሌሊትም ፡ ያጽራልና ፡ ይረዝማል ፡፡ በ
ትኵስ ፡ ዞና ፡ የቀንና ፡ የሌሊት ፡ ርዝመት ፡ ጥቂት ፡ ይለያ
ል ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ባመት ፡ ሁላንትና ፡፡ በመኻከለ
ኛ ፡ ዞናም ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ያጽራሉ ፡ አንድ ፡
ጊዜም ፡ ይረዝማሉ ፡፡ በየመውጫ ፡ በኩልም ፡ ከሁሉ ፡ የ
ሚረዝም ፡ ቀን ፡ ፯፤ ወር ፡ ይኖራል ፡፡ ከሁሉም ፡ የምትረ
ዝም ፡ ሌሊት ፡ ፯፤ ወር ፡፡

ይህ ፡ ነገርም ፡ ሁሉ ፡ ግሎቡስ ፡ በሚሉት ፡ በምድር ፡ ም
ሳሌ ፡ ይገኛል ፡፡

## ሁለተኛ ፡ ክፍል ፡፡
## ጊዎግራፊያ ፡ ፊሲቂ ፡፡

ጊዎግራፊያ ፡ ፊሲቂ ፡ የምድርን ፡ ፊሲስ ፡ ማለት ፡ ጠባይ
ዕ ፡ ታስተምረናለች ፡ መሬቱንም ፡ ተራራውንም ፡ ውኃው
ንም ፡ ፍሬውንም ፡ ታስታውቀናለች ፡፡

### የምድር ፡ አረር ፡፡

ከምድር ፡ አረር ፡ ፊቱን ፡ ብቻ ፡ ተከፍሎ ፡ እናውቃለን ፡
በውሥጡ ፡ ያለውን ፡ ግን ፡ አናውቅም ፡፡ በምድር ፡ ፊት
ም ፡ ድርቅ ፡ ምድር ፡ ከውኃ ፡ ተለየ ፡፡ ውኃውም ፡ በምድ
ር ፡ ላይ ፡ ዝቅ ፡ በሚል ፡ ስፍራ ፡ ተከማችትዋል ፡፡ የምድ
ር ፡ ፊት ፡ ታላቅ ፡ ጥልቅ ፡ የውኃም ፡ ሁሉ ፡ መሰብሰቢያ ፡
ባሕር ፡ ነው ፡፡ ደርቅ ፡ ምድርን ፡ ሁሉን ፡ የሚዞር ፡ ታላቅ ፡
ባሕር ፡ ያለም ፡ ባሕር ፡ ይባላል ፡ በዮናኒ ፡ ቋንቋም ፡ ዎ
ቅያኖስ ፡፡ የድርቅ ፡ ምድርም ፡ ታላቅ ፡ መስብሰቢያ ፡ ሁ
ሉ ፡ ኮንቲነንት ፡ ይባላል ፡ ወይስ ፡ የምድር ፡ ክፍል ፡፡ የ
ምድር ፡ ክፍሎችም ፡ ፭፤ ናቸው ፡ እርሳቸውም ፡ ኤውሮ
ጳ ፡ እስያም ፡ አፍሪካም ፡ አሜሪካም ፡ ኣውስትራ
ልያም ፡፡ በምድር ፡ ፊት ፡ ውኃ ፡ ይበዛል ፡ ድርቅ ፡ ምድር
ም ፡ ያንሳል ፡፡ ደርቅ ፡ ምድር ፡ ፩/፫ ፡፡ ውኃ ፡ ግን ፡ ፪/፫ ፡ ነው ፡፡

### በደርቅ ፡ ምድር ፡ ስላሉ ፡ ስለ ፡ ተራሮችና ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡፡

ማናቸይቱ ፡ ምድር ፡ ተራራ ፡ ባደገኝባት ፡ ወይስ ፡ ታና[illegible] ፡ ኮ
ረፍታ ፡ ብቻ ፡ ቢገኝባት ፡ ሜደ ፡ ትባላለች ፡፡ ከፍ ፡ የሚል
ም ፡ የምድር ፡ ስፍራ ፡ ብቻውን ፡ የሚኖር ፡ ተራራ ፡ ይባላ
ል ፡፡ አያሌ ፡ ተራሮችም ፡ ባንድ ፡ ቢገኙ ፡ የተራሮች ፡ መ
ሰብሰቢያ ፡ ወይስ ፡ የተራሮች ፡ ሰንስለት ፡ ወይስ ፡
የተራሮች ፡ ተርታ ፡ ይልዋቸዋል ፡፡ በተራሮች ፡ መኻከ
ልም ፡ ያለች ፡ ምድር ፡ ወይስ ፡ ሜደ ፡ ወይስ ፡ ቆላ ፡ ይልዋ
ታል ፡፡ ታላቅ ፡ ብትሆንም ፡ ድንገትም ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ብት
ወርድ ፡ ቍልቍለት ፡ ወይስ ፡ ጕድጓድ ፡ ትባላለች ፡፡ ከ

ምድር ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ የሚወጣ ፡ ጥቂት ፡ ከፍ ፡ የሚልም ፡ ምድር ፡ ካ ጵ ፡ ማለት ፡ ራስ ፡ ይባላል ፡፡ የምድር ፡ ከፍታ ፡ ሁሉ ፡ በባሕር ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ በሚል ፡ መጠን ፡ ይሰፈ ራል ፡፡ ከፍ ፡ የሚልም ፡ የተካከለም ፡ ምድር ፡ ወርዱ ፡ የ ማይበዛ ፡ የ ምድ ር ፡ ጀ ር ባ ፡ ይባላል ፡፡ ታላቅም ፡ ሰፊም ፡ ቢሆን ፡ የ ከ ፍ ታ ፡ ሜ ዳ ፡ ወይስ ፡ ጵ ላ ቶ ፡ ይባላል ፡፡ ም ድርም ፡ ከጵላቶ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ በጥቂት ፡ በጥቂትም ፡ የም ትወርድ ፡ የ ጵ ላ ቶ ፡ ጠ ፈ ር ፡ ትባላለች ፡፡ ከሁሉ ፡ የሚበ ልጡ ፡ ጵላቶች ፡ በደቡብ ፡ አሜሪካና ፡ በመኻከለኛ ፡ እስ ያ ፡ በአፍሪካም ፡ ይገኛሉ ፡፡ እሌህም ፡ ባሸዋ ፡ በረኾች ፡ ና ቸው ፡ እልያ ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ፍርያም ፡ ናቸው ፡፡

የሚጠቅሙም ፡ ማነሪሎች ፡ የውኋ ፡ ምንጬችም ፡ የጭ ውና ፡ የጤና ፡ ምንጬችም ፡ ሁሉ ፡ በተ ራ ሮች ፡ ይገኛሉ ፡፡ ተራሮችም ፡ በ፫ ፡ ይከፈላሉ ፡፡ የሚቀድሙ ፡ ተራሮች ፡ መ ኻከለኞችም ፡ አይነተኞችም ፡ ተራሮች ፡፡ የሚቀድሙም ፡ ተራሮች ፡ ታናሾች ፡ ናቸው ፡፡ መኻከለኞችም ፡ ከርሳቸው ፡ ጥቂት ፡ ይበልጣሉ ፡፡ በሌህ ፡ ሁለትም ፡ ከድሮ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ እጅግ ፡ መለዋወጥ ፡ ሆነባቸው ፡፡ ከርሳቸው ፡ የ ሚበልጡ ፡ አይነተኞች ፡ ተራሮች ፡ የመጀመርያ ፡ ተራሮች ፡ ይባላሉ ፡ ከጥንትም ፡ ጥቂት ፡ መለወጥ ፡ የሆነባቸው ፡ ይ መስላሉ ፡፡ በርሳቸውም ፡ የተገኘ ፡ የግራኒት ፡ ድንጊያ ፡ ብርቱ ፡ ነው ፡፡ ሁለት ፡ ታላላቆች ፡ ተራሮች ፡ አሉ ፡ አን ዱም ፡ ሺ ም ቦ ረ ሶ ፡ በደቡብ ፡ አሚሪካ ፡ ከፍታውም ፡ ፳፩፬፪፬፡ እግር ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ፲፬፡ ሺህ ፡ ፪፡ መቶ ፡ ፹፬፡ ክን ድ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡፡ ሁለተኛም ፡ ደ ወ ለ ጊ ር ፡ በስያ ፡ ነው ፡ ከፍታው ፡ ፳፮፰፮፪፡ እግር ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ያለ ፡፡ አያሌ ፡ ተራሮችም ፡ አንደንድ ፡ ጊዜ ፡ እሳትን ፡ ይተፋሉ ፡ ዉ ል ካ ኖ ችም ፡ ይባላሉ ፡፡ የምድር ፡ መናወጽም ፡ ከሳትና ፡ ከው ኋ ፡ የተነሣ ፡ ይመስላል ፡፡ ብዙ ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ተራሮች ፡ ወ ትሩ ፡ ውርጭንና ፡ በረደን ፡ ይለብሳሉ ፡፡ በተራሮች ፡ ውሥ ጥም ፡ አያሌ ፡ ጊዜ ፡ ዋሾች ፡ ይገኛሉ ፡፡ ሁለት ፡ ኮንቲነንቶ ችን ፡ ባንድ ፡ የምታገናኛቸው ፡ በሁለት ፡ ባሕሮችም ፡ መኻ ከል ፡ የምታልፍ ፡ ጸቢብ ፡ ምድር ፡ ኢስትሞስ ፡ ትባላለ

ች ፡፡ እጅግም ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ የምትገባ ፡ ጸቢብ ፡ ምድር ፡ የምድር ፡ ምላስ ፡ ትባላለች ፡፡

## በደርቅ ፡ ምድር ፡ ስላሉ ፡ ፈሳሾችና ፡ ባሕሮች ፡ ስለ ፡ ሌሎች ፡ ውኆችም ፡፡

የደርቅ ፡ ምድር ፡ ውኆች ፡ ምንጮች ፡ ፈሳሾችም ፡ ወንዞችም ፡ መስኖችም ፡ ባሕሮችም ፡ ናቸው ፡፡ እሌህም ፡ ከጭው ፡ ባሕር ፡ ለመለየት ፡ የምድር ፡ ባሕሮች ፡ ይባላሉ ፡፡ ከሁሉ ፡ የሚበልጡ ፡ የምድር ፡ ባሕሮች ፡ የከስጲያ ፡ ባሕር ፡ በሩስያ ፡ መንግሥት ፡ የካነደ ፡ ባሕሮችም ፡ ባሜሪካ ፡ ናቸው ፡፡ መናቸው ፡ ምንጭ ፡ ሲወጣ ፡ ታናሽ ፡ ፈሳሽ ፡ ይሆናል ፡፡ ብዙ ፡ ፈሳሾችም ፡ ባንድ ፡ ሲገናኙ ፡ ወንዝ ፡ ይሆናል ፡፡ ፈሳሽ ፡ ወይስ ፡ ወንዝ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ወንዝ ፡ ወይስ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ወደሚገባበት ፡ ስፍራ ፡ የፈሳሽ ፡ ወይስ ፡ የወንዝ ፡ አፍ ፡ ይባላል ፡ የሚያልፍባትም ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ግዛቱ ፡ ትባላለች ፡፡ ወንዝ ፡ ከታላቅ ፡ ከፍታ ፡ ድንገት ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ቢወርድ ፡ የወንዝ ፡ ፏፏቴ ፡ ወይስ ፡ ከተረክት ፡ ይሆናል ፡፡ ሁለት ፡ ወንዞችን ፡ ባንድ ፡ የሚገጥም ፡ ውኃ ፡ መስኖ ፡ ይባላል ፡፡ ከምንጮችም ፡ አያሌ ፡ አሉ ፡ አንደንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የሚፈሉ ፡፡ አያሌም ፡ የሚነሩል ፡ ምንጮች ፡ ናቸው ፡፡ ከርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ ለጤና ፡ ያገለግላሉ ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሕማም ፡ ተሽሮባቸዋልና ፡፡

## ዎቅያኖስ ፡ ታላቅ ፡ ባሕር ፡፡

በፅርዕ ፡ ቋንቋ ፡ ዎቅያኖስ ፡ የሚሉት ፡ ታላቅ ፡ ባሕር ፡ ደርቅ ፡ ምድርን ፡ ሁሉን ፡ ይዞራል ፡፡ ጥልቁም ፡ ባንደንድ ፡ ስፍራ ፡ ፭፡ ሚላ ፡ ያህላል ፡፡ በውሥጡም ፡ ሚደና ፡ ተራራ ፡ ደንጊያም ፡ አታክልትም ፡ አለ ፡፡ ከውኃ ፡ በላይ ፡ የሚወጡ ፡ ተራሮች ፡ ደሴቶች ፡ ይባላሉ ፡፡ ዎቅያኖስም ፡ በ፭፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ ይከፈላል ፡ እርሳቸውም ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡ የሰሜን ፡ ውርጭ ፡ ባሕር ፡፡ የምዕራብም ፡ ዎቅያኖስ ፡ አትላንቲስ ፡ የሚባል ፡ የህንድም ፡ ዎቅያኖስ ፡፡ የምሥራቅም ፡ ወይስ ፡ የጸጥታ ፡ ዎቅያኖስ ፡፡ የደቡብም ፡ ውርጭ ፡ ባሕር ፡፡ ቍጥርም ፡ ከሌለው ፡ ከታናሾች ፡

ፈሳሾች ፡ በቀር ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ የሚፈሱ ፡ ከ፷፱። የሚበዙ ፡ ታላቆች ፡ ወንዞች ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ይገባሉ ። ወደ ፡ ባሕርም ፡ የሚገባ ፡ ውኃ ፡ ሁሉ ፡ ይጻፈጣል ፡ የባሕር ፡ ውኃ ፡ ሁሉ ፡ መራራና ፡ ጨው ፡ ነው ። ባንደንድ ፡ ስፍራም ፡ የባሕር ፡ ውኃ ፡ በሌሊት ፡ ያበራል ። ከባሕርም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ጉም ፡ ሁኖ ፡ የሚወጣ ፡ ውኃ ፡ በደመና ፡ ይሰበሰባል ፡ ንፋስም ፡ ወደ ፡ ደርቅ ፡ ምድር ፡ ይወስደዋል ፡ በኋላም ፡ ዝናም ፡ ሁኖ ፡ በረደም ፡ ሁኖ ፡ ውርጭም ፡ ሁኖ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይዘንማል ። ባሕርም ፡ በየጊዜው ፡ ይነሣልና ፡ ይወድቃል ። በብዙ ፡ ስፍራም ፡ ይህ ፡ በየስድስት ፡ በሌላ ፡ ስፍራም ፡ በያራት ፡ ስዓት ፡ ነው ፡ ይህም ፡ በእንግሊዝ ፡ ቋንቋ ፡ ተይድስ ፡ ይባላል ። የተይድስም ፡ መክንያት ፡ ጨረቃና ፡ ፀሓይ ፡ ነው ። ንፋስ ፡ ባይኖር ፡ የባሕር ፡ ፊት ፡ ጸጥ ፡ ይላል ፡ መስተወትንም ፡ ይመስላል ፡ ንፋስ ፡ ግን ፡ ሞገድን ፡ ያስነሣል ። አውሎ ፡ ንፋስም ፡ ታላቅ ፡ ቤት ፡ የሚመስልን ፡ ሞገድ ፡ ያስነሣል ። ባንደንድ ፡ ስፍራ ፡ መደ ፡ አለ ፡ በባሕር ፡ በየጊዜው ፡ ወይስ ፡ ወትሩ ፡ መርከቦችን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የሚወስድ ። አንደንድ ፡ ስፍራም ፡ አለ ፡ ውኃው ፡ የሚዞርበት ። መርከብም ፡ ወደዚያ ፡ ቢቀርብ ፡ ውኃ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ይወስደዋል ፡ መደንም ፡ የለም ። በባሕር ፡ ደርቻ ፡ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ ባሕር ፡ ወይስ ፡ እጅግ ፡ ወይስ ፡ ጥቂት ፡ ወደ ፡ ደርቅ ፡ ምድር ፡ ይገባል ፡ ያም ፡ ስፍራ ፡ ጉበት ፡ ይባላል ፡ ወይስ ፡ ቤይ ። ከዚያም ፡ መርከቦች ፡ ያርፋሉ ፡ መርስንም ፡ ወይስ ፡ ሚናን ፡ ያገኛሉ ። በዙርያዋ ፡ ሁሉ ፡ ውኃ ፡ ያላት ፡ ምድር ፡ ደሴት ፡ ናት ። ባንድ ፡ ወገን ፡ ግን ፡ ከኮንቲነንት ፡ ጋራ ፡ ብትገጠም ፡ ጴኒንሱላ ፡ ትባላለች ። ብዙ ፡ ደሴቶችም ፡ ባንድ ፡ ቢገኙ ፡ አርኪጴላጎስ ፡ ይባላሉ ።

## አየር ። አትሞስፌራም ። ሜቲዎርም ። ንፋሳትም ፡ ትኩሳትና ፡ ብርድም ።

ያ ፡ ረቂቅ ፡ ማየትንም ፡ የሚያሳልፍ ፡ ከቢድም ፡ እለስቲቄም ፡ ነገር ፡ ወትሩ ፡ የምንነፍሰው ፡ ባካላችንም ፡ ሰምተን ፡ የሚናየው ፡ አየር ፡ ነው ። የሚከበነም ፡ ያየር ፡ ክፍ

ል ፡ የውኃና ፡ የምድር ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ወዝ ፡ ጤስም ፡ ኣ
ስተንፈስም ፡ የሚገባበት ፡ ኣትሞስፌሬ ፡ ይባላል ፡ ኣር
ሶም ፡ ያየር ፡ ሶስት ፡ ደርብ ፡ ናቸው ፡ ኣርሶ ፡ በርሳቸው ፡
የተለዩ ። ታችኛ ፡ ደርብም ፡ የሞቀ ፡ ነው ። ሁለተኛ ፡ ደርብ
ም ፡ ብርድ ፡ ነው ፡ የበረደ ፡ የውርጭመ ፡ ስፍራ ። በታቹ ፡
ውኃ ፡ የነበረ ፡ በላይ ፡ ይረጋልና ። ሶስተኛ ፡ ደርብም ፡ ከሁ
ሉ ፡ ይልቅ ፡ ይበርዳል ። ባትምስፌሬም ፡ ያለ ፡ ሁሉ ፡ የሚ
ታይም ፡ ሜቴዎር ፡ ይባላል ፡ እንዲሁም ፡ ጉም ፡ ጸጋግም ፡
ደመናም ፡ ዝናምም ፡ የዝናም ፡ ቀስትም ፡ የደመና ፡ ፍሬ
ሽም ፡ ጉርፍም ፡ የመሬት ፡ ኩርፌትም ፡ የውኃ ፡ ኩርፌት
ም ። ሁለተኛ ፡ ፀሓይም ፡ ሁለተኛ ፡ ጨረቃም ፡ መጽባትና ፡
መሸትም ፡ በረድም ፡ መብረቅም ፡ ነጐድጓድም ፡ የሰሜን
ና ፡ የደቡብ ፡ ብርሃንም ፡ የሳት ፡ ኣረርም ፡ የከዋክብት ፡ መ
ወርወርም ፡ ነፋሳትም ፡ የሚቀርም ። ያየር ፡ ክብድ ፡ ቢለ
ወጥ ፡ ሚዛኑም ፡ ባይከከል ፡ ኣየር ፡ ተናውጥዋልና ፡ ነፋስ ፡
ይሆናል ። በየጊዜያቸው ፡ የሚለወጡ ፡ ነፋሳት ፡ ኢሌሀ ፡
ናቸው ፡ በመላሽ ፡ ዙርያ ፡ በኩል ፡ የሚነፍሱ ፡ የጾሳት ፡
ነፋሳት ፡ በህንድ ፡ ባሕርም ፡ መውሱን ፡ የሚባል ፡ ነፋስ ፡
በየ፮፡ ወር ፡ የሚለወጥ ። በየጊዜያቸውም ፡ ያሉ ፡ የባሕር
ና ፡ የምድር ፡ ነፋሳት ፡ የምሥር ፡ ኸምሲን ፡ የፋርስም ፡
ሰሙም ፡ የምዕራብ ፡ ኣፍሪካ ፡ ሀርመታንም ፡ የኢጣልያ ፡
ሺሮኮም ፡ እንዲህ ፡ ናቸው ።

ትኩሳትና ፡ ብርድ ። በየዞና ፡ የምድር ፡ ተኩሳትና ፡
ብርድ ፡ ይለያል ። በባሕር ፡ ደርም ፡ በምድር ፡ መኻከልም ፡
ያለ ፡ ከፍ ፡ የሚልና ፡ ዝቅ ፡ የሚልም ፡ እጅግ ፡ የሚተከል
በትም ፡ የማይተከልበትም ፡ ኣገር ፡ ሁሉ ፡ በሙቀት ፡ እር
ሶ ፡ በርሳቸው ፡ ይለያሉ ።

ፊሲቁ ፡ ጵሮጌኔ ። ፊሲቁ ፡ ጵሮጌኔ ፡ ማለት ፡ ሁሉ ፡ ነው ፡
ከባሕርና ፡ ከምድር ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ ወይስ ፡ እንዲያው ፡ የ
ሚወጣ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ። የብልሃት ፡ ጵሮጌኔ ፡ ማለት ፡ ከሰ
ው ፡ ብልሃትና ፡ ስራ ፡ የሚወጣ ። ፊሲቁ ፡ ጵሮጌኔ ፡ ከ፫፡ ከ
ፍጥረት ፡ መንግሥቶች ፡ ይወጣል ። ከሚነራል ፡ ወይስ ፡ ደ
ንጊያ ፡ መንግሥት ፡ ካታክልትም ፡ መንግሥት ፡ ከንስሶች

ም ፡ መንግሥት ፡፡ ሚነራሎችንም ፡ ባራት ፡ ክፍል ፡ ይከፍላሉ ፡፡ ፩፡ የመሬትና ፡ የደንጊያ ፡ ወገን ፡፡ ፪፡፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ጭው ፡ ወገን ፡፡ ፫፡፡ የሚነዱ ፡ ሚነራሎች ፡፡ ፬፡፡ ሚታሎች ፡፡ ከሚታሎችም ፡ አሁን ፡ ፳፫፡ ልዩ ፡ አይነት ፡ ተገኙ ፡፡ ያታክልትም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አይነት ፡ አሁን ፡ ፵፲፱፡፡ ታወቁ ፡ የንስሮችም ፡ ፳፲፱፡፡ ልዩ ፡ አይነት ፡፡

## ስለ ፡ ሰው ፡፡

ምድራችን ፡ ለሰው ፡ ማደርያ ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ተፈጠረች ፡፡ እርሱም ፡ በምድር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምስጋና ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ በሁሉ ፡ ያመሰግን ፡ ዘንድ ፡ ነበር ፡፡ ሰውም ፡ በኃጢአት ፡ ሳይወድቅ ፡ በምድር ፡ የታድላ ፡ ገነት ፡ ነበረ ፡፡ በኃጢአት ፡ ግን ፡ ከወደቅን ፡ በኋላ ፡ ፍጥረትም ፡ ከጥፋት ፡ መርገም ፡ በታች ፡ ተደረገች ፡ በሰው ፡ መክንያት ፡፡ ክርስቶስም ፡ አርነት ፡ ያወጣን ፡ ዘንድ ፡ መጣ ፡፡ የሰውም ፡ ትውልድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲመለስ ፡ የቀረች ፡ ፍጥረትም ፡ ከጥፋት ፡ መርገም ፡ አርነት ፡ ትወጣለች ፡፡ እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ ምድራችን ፡ የጥፋት ፡ የመከራም ፡ የመጋደልም ፡ ስፍራ ፡ ናት ፡፡ ካደም ፡ ልጆችመ ፡ ጥቂት ፡ ናቸው ፡ መድኃኒታቸውን ፡ አውቀው ፡ የተቀበሉት ፡ የደኑበትም ፡፡ ብዙ ፡ ናቸው ፡ በመንፈሳዊት ፡ ጨለማ ፡ በሞትም ፡ ጽላ ፡ የተቀመጡ ፡፡ የሰው ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ ቍጥራቸው ፡ ፲፱፡ ሚልዮን ፡ ያህላል ፡፡ ከርሳቸውም ፡ ፮፱፡ ሚልዮን ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ በስም ፡ ክርስቲያን ፡ የተባሉ ፡፡ ፮፱፡፡ ሚልዮንም ፡ እሥላሞችና ፡ አይሁድ ፡ የቀሩም ፡ ፯፱፡ ሚልዮን ፡ አረማውያን ፡ ናቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ የማያውቁ ፡ ለጣዖታትም ፡ የሚሰግዱ ፡፡ ለክርስቲያንም ፡ ይገባል ፡ ያለ ፡ ክርስቶስ ፡ ለሚኖሩ ፡ ወንድሞቹ ፡ ያዝን ፡ ዘንድ ፡ ወንጌልም ፡ እስኪደርስላቸው ፡ ይደክም ፡ ዘንድ ፡ ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደዘዘው ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡፡ ስምህ ፡ ይቀደስ ፡፡ መንግሥትህ ፡ ትምጻ ፡፡ ፈቃድህ ፡ በምድር ፡ ትሁን ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ በሰማይ ፡፡ አሜን ፡፡

## ክፍል ፡ ፫።

### ጌዎግራፊያ ፡ ጶሊቲቂ ።

ጌዎግራፊያ ፡ ጶሊቲቂ ፡ ታሳዮናለች ፡ ምድሪቱን ፡ በብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ተከፍላ ፡ የሰው ፡ ትውልድ ፡ መኖርያ ፡ እንደ ፡ ሆነች ። ብዙ ፡ ሰዎች ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ በጉባዔ ፡ ተሰማምተው ፡ ለብቻቸው ፡ ቢቀመጡ ፡ በየምድሪቸው ፡ በየወጋቸውም ፡ ለየመኳንንታቸውም ፡ ተገዝተው ፡ እርሳ ቸው ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ፡ ጉባኤያቸውም ፡ መንግሥት ፡ ት ባላለች ።

የመንግሥት ፡ ሁሉ ፡ ስፍራ ፡ ወሰንም ፡ ታለቅነትም ፡ መክፈልም ። የምንግሥት ፡ ሁሉ ፡ ስፍራ ፡ በምድር ፡ ር ዝመትና ፡ ወርድ ፡ ባርዛቸው ፡ ይታወቃል ። ወሰንዋም ፡ ወ ደስ ፡ በተራሮች ፡ ባሕሮችም ፡ ፈሳሾችም ፡ ነው ፡ ወደስ ፡ በ መንግሥት ፡ ሕግ ፡ ተሰራ ። የመንግሥትም ፡ ሁሉ ፡ ታላቅነ ት ፡ በሚሎች ፡ ቍጥር ፡ ትታወቃለች ፡ በየወርደና ፡ በየረዝ መቱ ። መክፈልዋም ፡ በየመንግሥት ፡ ሥርዓት ፡ ነው ።

### የሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ብዛት ፡ ጠባዩም ፡ መማሩም ፡ ዕውቀ ቱም ፡ ብልሃቱም ፡ ማምለኩም ፡ ቋንቋውም ።

መናቸይቱ ፡ ሕዝብ ፡ ቍጥርዋ ፡ በውነት ፡ ይታወቃል ፡ የ ሚወለዱና ፡ የሚሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በድብደቤ ፡ ቢጻ ፉ ፡ ሹማምትም ፡ ይህችን ፡ ድብደቤ ፡ ወትሩ ፡ ቢጠብቁ ። የሰው ፡ ሕዝብም ፡ ሁሉ ፡ ጠባይዕ ፡ በታላቅ ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡ በታናሽ ፡ ነገር ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ ይለያያሉ ። አ ንዲት ፡ ሕዝብ ፡ ልባም ፡ ናት ፡ የታመነችም ፡ ቁም ፡ ነገርን ም ፡ ትወደለች ፡ አትፈሪምም ። ሌላይቱ ፡ ሕዝብም ፡ ል ብ ፡ የላትም ፡ አሰትንም ፡ የምትወድ ፡ ፈሪም ፡ ናት ፡ አል ታመነችም ። አንዲት ፡ ሕዝብም ፡ ደህና ፡ ሥርዓት ፡ አላት ፡ ትጠብቀውማለች ፡ በጥቂትም ፡ በጅግም ፡ እግዚአብሔር ን ፡ ትፈራለች ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ በረከት ፡ ተቀብላ ፡ በሃይማኖት ፡ በባለጠግነትም ፡ በትምህርትም ፡ በውቀት

ም ፡ በብልሃትም ፡ ታድጋለች ። ሌላ ፡ ሕዝብም ፡ ይህ ፡ በ ጎ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አይገኝባትምና ፡ በጨለማ ፡ ትኖራለች ። አ ውቀትና ፡ ብልሃት ፡ በማስተማርዮች ፡ ይማራሉ ። ማስ ተማርዮችም ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ አይነት ፡ አሉ ። በየመንግሥቱ ም ፡ ደህንነት ፡ መጠን ፡ ይበዛሉ ፡ ወይስ ፡ ያንሳሉ ። የመን ግሥት ፡ ሁሉ ፡ ተስፋ ፡ ወይስ ፡ ፍርሃት ፡ ዐሸክሮች ፡ ናቸው ና ፡ እርሳቸው ፡ በጎን ፡ ነገርን ፡ ሁሉን ፡ በታናሽነታቸው ፡ ቢ ማሩ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ቢወዱ ፡ በታላቅነታቸውም ፡ ለ መንግሥታቸው ፡ ለሰውም ፡ ሁሉ ፡ ይጠቅማሉ ። ባይማ ሩ ፡ ግን ፡ በልባቸው ፡ ክፋትና ፡ ጨለማ ፡ ኑረው ፡ ራሳቸው ንና ፡ ባልንጀሮቻቸውን ፡ ይጕዳሉ ። የክርስቶስ ፡ ቃል ፡ ዝ ም ፡ ብሎ ፡ አይቈጠር ፡ እንዲህ ፡ ሲል ። ከሁሉ ፡ በፊት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥትና ፡ ጽድቁን ፡ እሹ ፡ የሚቀርም ፡ ሁሉ ፡ እንዲያው ፡ ይጨመርላችኋል ።

ስለ ፡ ማምለክም ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ ይከፈላ ሉ ። ፩። አንድን ፡ አምላክ ፡ የሚያመልኩ ። ፪። ብዙ ፡ አ ማልክትንና ፡ ጣዖታትን ፡ የሚያመልኩ ። አንድን ፡ አም ላክ ፡ የሚያመልኩ ፡ እሌህ ፡ ናቸው ። ፫። ክርስቲያን ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ አይነት ። እርሳቸውም ፡ ሁላቸው ፡ በስም ፡ ለ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተቈጠረች ፡ መንጋ ፡ ናቸው ፡ ሁላቸ ው ፡ ግን ፡ የርሱ ፡ አይነተኛ ፡ ወገን ፡ አይደሉም ። የሁላቸ ው ፡ መሠረት ፡ የየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጽሩ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ እር ሱንም ፡ ብቻውን ፡ የሚከተል ፡ ቃሉንም ፡ በልቡ ፡ ጽሩ ፡ የሚጠብቅ ፡ የሚፈጽመውም ፡ ገንዘቡ ፡ ነው ፡ የቀሩትን ፡ ግን ፡ ክርስቶስ ፡ ለገንዘቡ ፡ አያውቃቸውም ። ፬። አይሁ ድ ። ፭። እሥላሞች ።

ብዙ ፡ አሕዛብም ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ በቋንቋቸው ፡ ተለ ዩ ። ዛሬ ፡ የታወቁ ፡ የምድር ፡ ቋንቋዎች ፡ ከ፯፻፡ ይበዛሉ ፡ ገ ናም ፡ ያልታወቁ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። መጽሐፈ ፡ ቅዱስም ፡ አሁ ን ፡ በ፱፻፡ ቋንቋዎች ፡ ተጽፎ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ይወጣል ።

የሰው ፡ መክፈል ፡ ስራም ፡ መኖርያም ።

ሥርዓት ፡ ባለባት ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ ሰዎች ፡ በልዩ ፡ ል ዩ ፡ ማዕረግ ፡ ተከፈሉ ፡ እንደህ ። አካበሮች ። የመቅደ

ስሞ ፡ አገልጋዮች ፡፡ ባላገሮችም ፡፡ ገባሮችም ፡፡ ወይ
ስ ፡ እንዲህ ፡፡ መኳንንት ፡፡ ወታደርም ፡፡ የመቅደስ ፡
አገልጋዮችም ፡፡ ባላገሮችም ፡፡ ገባሮችም ፡፡ ገባሮችና ፡
ሰራተኞችም ፡ ወይስ ፡ ከብትንና ፡ ፈሬን ፡ ለማብዛት ፡ ይደ
ክማሉ ፡ እንደ ፡ ገባሮች ፡ አራሾችም ፡ ተራራውንም ፡ የሚ
ወቅሩ ፡ ሰዎች ፡ ተካዮችም ፡ ከብትንም ፡ የሚያሳድጉ ፡
ዓሣ ፡ አዕማጆችም ፡ አደኞችም ፡ የሚቀሩም ፡፡ ወይስ ፡ የ
ተገኘውን ፡ ነገር ፡ ይሰራሉ ፡ በብረት ፡ በንጨትም ፡ በደንጊ
ያም ፡ በሌሎች ፡ ሚነራሎችም ፡ በፈትልም ፡ ሸማኖችም ፡
የሚቀሩም ፡፡ ወይስ ፡ ይነግዳሉ ፡፡ ለሁሉም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡
ሥርዓት ፡ አለ ፡፡ የሰውም ፡ መኖርያ ፡ ወይስ ፡ ከተማ ፡ ነ
ው ፡ ያገር ፡ ኃዢ ፡ የሚኖርባት ፡ ወይስ ፡ ታናሽ ፡ መንደር ፡
ወይስ ፡ መኻከለኛ ፡ የገቢያም ፡ አገር ፡፡

## ያገር ፡ መግዛት ፡ ልዮነት ፡፡

ለመንግሥት ፡ ሁሉ ፡ አንዲት ፡ ታላቅ ፡ ሥልጣን ፡ አለች ፡
ሕግን ፡ የምትሰጥ ፡ የምታደርገውም ፡፡ ይህች ፡ ሥልጣንም ፡
ሞናርኪቂ ፡ ናት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ቢገዛ ፡ ሕግንም ፡ ቢ
ሰጥ ፡፡ አልተወሰነችም ፡ እርሱ ፡ በፈቃዱና ፡ ባውቀቱ ፡ ብቻ
ውን ፡ ቢገዛ ፡፡ ተወሰነች ፡ ግን ፡ ከሕዝቡ ፡ ፈቃድ ፡ ጋራ ፡ ቢ
ገዛ ፡፡ ሬጱብሊካም ፡ ናት ፡ ንጉሥ ፡ ባይኖር ፡ ሕዝብም ፡ ሁ
ሉ ፡ ወይስ ፡ የሕዝብ ፡ ሽማግሎችና ፡ ታላቆች ፡ ባንድ ፡
ቢገዙ ፡፡

## የምድር ፡ ክፍል ፡፡

ምድር ፡ ባምስት ፡ ክፍል ፡ ተከፈለች ፡ እርሳቸውም ፡
እሌህ ፡ ናቸው ፡፡ ኤውሮጳ ፡ እስያም ፡ አፍሪካም ፡ አሜሪ
ካም ፡ ኣውስትራልያም ፡፡

የስከንዲናዊያ : ባሕር : ከኖርዌግን : ባሕርና : ከሰሜን : ባ
ሕር : ጋራ :: የሰሜን : ባሕርም : በከትገት : በሆንድም : በ
ታናሽና : በታላቅ : በልትም : ከምሥራቅ : ባሕር : ጋራ : ይ
ገጠማል :: ከምሥራቅ : ባሕርም : የሊፍላንድ : የፊንላን
ድም : የቦትኒያም : ጉብቶች : ይነሣሉ :: ፫፥ ያትላንቲስ :
ባሕር : ወይስ : የምዕራብ : ውቅያኖስ :: እርሱም : በእን
ግሊስ : መስና : በከለይስ : ደጅም : አድርጎ : ከሰሜን : ባ
ሕር : ጋራ : ይገጠማል :: ከርሱ : ዘንድም : ያኲታኒያና : የ
ቢስካያ : ባሕሮች : አሉ :: ፬፥ መኻከለኛ : ባሕር : በግብረ
ልታር : ደጅ : ከምዕራብ : ውቅያኖስ : ጋራ : ይገጠማል :: በ
ኤውሮጳም : በስያም : በአፍሪካም : በመኻከል : ይኖራ
ል :: የመኻከለኛ : ባሕርም : ክፍሎች : ወይስ : ጉብቶች :
እሌህ : ናቸው :: የኤትሩርያ : ባሕር :: ያድርያም : ባሕ
ር :: የዮንያ : ባሕርም :: የሩምም : አርኪጴላጎስ :: የደር
ደኔሎችም : መንገድ :: የመርሞራ : ባሕርም :: የቍንስታን
ቲኒያ : ደጅም :: ጥቁር : ባሕርም :: የፌዎደስያ : ደጅም ::
ያሶው : ባሕርም :: የምድር : ባሕሮች :: የለደጋና : የኦኔ
ጋ : ባሕሮች : በሩስያ :: የሜላርና : የወተርም : ባሕሮች :
በሽዌድን :: የጽላትን : ባሕርም : በሁንጋርያ :: የኪርክኒ
ጽ : ባሕርም : በክራይን :: የቦድን : ባሕርና : የገንፍ : ባሕ
ርም : በሄልዌትያ :: ታላቅ : ባሕርና : የኮም : ባሕርም : በ
ኢጣልያ :: ልፍሌንም : ልፍኒም : በኢርላንድ :: ታላቆች :
ወንዞች :: ዎልጋ :: ድዊናም : ደንም : ድኒጵርም :: ዊስቱላ
ም :: ደኑብም :: ረይንም :: ኤልብም :: ዌስርም :: ኦድር
ም :: ሮንም :: ጋሮናም :: ልዋርም :: ሴናም :: ጶም :: ኤብ
ሮም :: ታጉስም :: ቴምስም :: ከሌህ : በቀርም : በኤውሮ
ጳ : ከ፫፻፤ የሚበዙ : ወንዞች : አሉ : መርከቦች : የሚሔ
ዱባቸው : ብዙም : የተቈፈሩ : መስኖች : አሉ : በታላቅ :
ብሪታኒያ : በፍራንስም : በታችኛ : ምድርም ::

ክሊማ :: ወደ : ደቡብ : ያለች : ምድር : ሙቅ : ናት : እ
ርስዋም : ጶርቱጋል : ስጳንያም : የደቡብ : ፍራንስም : የደቡ
ብ : ኢጣልያም : የኤውሮጳ : ቱርክያም :: መኻከለኛ : ብ

ርድና ፡ ሙቀት ፡ አለ ፡ በላየኛ ፡ ኢጣልያና ፡ ፈረንሰ ፡፡ በን ምሳም ፡ በሄልቬትያም ፡ በሁንጋርያም ፡ በታችኛ ፡ ምድር ም ፡ በታላቅ ፡ ብሪታንያና ፡ በኢርለንድም ፡ በደንመርክም ፡ በጵረስያም ፡ በጶሎንያም ፡ በገሊትያም ፡ በደቡብ ፡ ስከን ደናዊያም ፡ በደቡብ ፡ ረስያም ፡፡ ወደ ፡ ሰሜንም ፡ ያለች ፡ ምድር ፡ ብርድ ፡ ናት ፡፡

ምድር ፡ የምታውጣ ፡፡ ካታክልት ፡ መንግሥት ፡፡ በኤ ውሮጳ ፡ ከሚበቀሉ ፡ አታክልት ፡ ብዙ ፡ ከሌላ ፡ አገር ፡ መ ጡ ፡፡ የሚገኝም ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ የብዙ ፡ አይነት ፡ እህል ፡ የ ዛፍ ፡ ፍሬም ፡ ለምግብና ፡ ለመድኃኒት ፡ የሚሆን ፡፡ ጳታት ስም ፡ ያታክልትም ፡ ብቋያ ፡ ቶምባሆም ፡ ከነቢስም ፡ ለሳ ትና ፡ ለመስሪትም ፡ የሚሆን ፡ እጅግ ፡ እንጨት ፡ ወይን ም ፡ ረዝም ፡ ሎሚንም ፡ ቦርቱጋንም ፡ በለስም ፡ ዘይትም ፡ ለውዝም ፡ ሢካርም ፡ ጥጥም ፡ የሚቀርም ፡፡ ከንስሳም ፡ መንግሥት ፡፡ የቤት ፡ እንስሳ ፡ ሁሉ ፡፡ ያንደንድ ፡ አይነ ትም ፡ ከምድረ ፡ በደ ፡ እንስሳ ፡ ንብም ፡ የሀር ፡ ትልም ፡ ዓሣም ፡ የሚቀርም ፡፡ ከ ሚ ነ ሪ ሎ ች ፡ መንግሥትም ፡፡ እጅግ ፡ ብረት ፡ ነሃስም ፡ ቆርቆሮም ፡ ባዜቃም ፡ ወርቅም ፡ ብርም ፡ ልዩ ፡ ልዩም ፡ ከከበረ ፡ ደንጎች ፡ ጨውም ፡ ባመ ት ፡ ባመት ፡ ፴፩፡ ሚልዮን ፡ ቅንጣር ፡ የሚያህል ፡፡ የሚ ነሪ ልም ፡ ምንጩች ፡፡

የጅ ፡ ስራ ፡፡ መሻየጥም ፡፡ የጅ ፡ ስራ ፡ እጅግ ፡ መል ካም ፡ በእንግሊጣር ፡ በፈረንስም ፡ በታችኛ ፡ ምድርም ፡ በ ሄልቬትያም ፡ በንምሳም ፡ ይደረጋል ፡፡ እጅግም ፡ የሚሻ የጡ ፡ መንግሥቶች ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡ እንግሊጣር ፡ ከሁ ሉ ፡ ይልቅ ፡፡ ታችኛ ፡ ምድርም ፡፡ ፈረንስም ፡፡ ረስያም ፡፡ ስጳንያም ፡፡ ጶርቱጋልም ፡፡ ደንመርክም ፡፡ ሸዌድንም ፡፡ ኖ ርዌግንም ፡፡ ጵረስያም ፡፡ ፫፡ የመሻየጥ ፡ ከተሞችም ፡፡ አ ውስትርያም ፡፡ የኤውሮጳ ፡ መሻየጥ ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ተ ዘርግትዋል ፡፡ በኤውሮጳም ፡ ያለ ፡ ያልተቀረጸ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ነሃስም ፡ ፳፱፡ ሚልዮን ፡ ቅርሽ ፡ ያህላል ፡፡

የኤውሮጳ ፡ ተቀማጮች ፡፡ በኤውሮጳ ፡ የሚቀመጡ ፡

ወስትም ፡ አሉ ፡፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ ሕዝብን ፡ በጨለማ ፡ ት
ተው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጽሩ ፡ ቃል ፡ ፈንታ ፡ የሰውን ፡ ት
ምርት ፡ አስተምረዋልና ፡ እግዚአብሔር ፡ በጸላቶቻቸው ፡
እጅ ፡ ሰጣቸው ፡፡

የመንግሥት ፡ መግዛት ፡፡ የንጉሥ ፡ ሥልጣን ፡ ኮርተ
ስ ፡ በሚልዋቸው ፡ በመካሮች ፡ ጉባኤ ፡ ተወሰነች ፡፡ ከንጉ
ሥ ፡ ልጆችም ፡ ወንድ ፡ ቢታጣ ፡ ሴት ፡ ልጁ ፡ ትነግሣለች ፡፡
ዛሬም ፡ የምትነግሥ ፡ ሴት ፡ ናት ፡ ስምዋንም ፡ ደና ፡ ማር
ያም ፡ ደግሎርያ ፡ ይሉታል ፡፡ ይህች ፡ መንግሥትም ፡ በቅድ
ም ፡ ታላቅ ፡ ነበረች ፡፡ እግዚአብሔር ፡ በህንድ ፡ በደቡብ ፡
አሜሪካም ፡ እጅግ ፡ ምድር ፡ በጃቸው ፡ ይሰጥ ፡ ነበር ፡፡ እ
ርሳቸው ፡ ግን ፡ በግፍ ፡ ገዝተዋታልና ፡ የባላገሮችንም ፡ ደህ
ንነት ፡ በማውጣት ፡ ፈንታ ፡ ቀምተዋቸዋልና ፡ ባሮችንም ፡
አድርገዋቸዋልና ፡ አሁን ፡ ብዙ ፡ አህጋር ፡ በላያቸው ፡ ተነ
ሥተው ፡ ሸፈጡ ፡ ለየራሳቸውም ፡ ተገዙ ፡፡ የእግዚአብሔ
ርም ፡ ቃል ፡ አሁን ፡ ፫፻፤ አመት ፡ የሚያህል ፡ በኤውሮጳ ፡
አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ላይ ፡ ሲነሣ ፡ እንግልጣርም ፡ የን
ምሳም ፡ ክፍል ፡ ሲቀበሉት ፡ ሲረቡበትም ፡ በስጳንያና ፡ በ
ጶርቱጋል ፡ በፍራንስም ፡ በኢጣልያም ፡ በሌላ ፡ አገርም ፡ አ
ልተቀበሉትም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ የተቀበሉት ፡ የ
ጵሮትስታንቶችን ፡ ጉባኤ ፡ አሳደዱ ፡ እንጅ ፡፡ ዛሬም ፡ የኃ
ጢአታቸውንና ፡ የግፋቸውን ፡ ደመወዜ ፡ ይቀበላሉ ፡፡ በጶ
ርቱጋልና ፡ በስጳንያ ፡ ያሉ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በየጋ
ዣቸው ፡ ተቀሙ ፡፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃልም ፡ ፈንታ ፡ የጳ
ጳሳትንና ፡ የቀሳወስትን ፡ ቃል ፡ አድርገዋልና ፡ ዛሬ ፡ ሁለ
ቱን ፡ ባንድ ፡ ይጣላሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ከቀሳወ
ስታቸው ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ ገና ፡ ይታገሥላቸ
ዋል ፡ በእንግሊዝ ፡ እጅም ፡ የሥጋንና ፡ የነፍስን ፡ ረዴት ፡
ይሰድላቸዋል ፡፡ የነፍስን ፡ ረዴት ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ቃል ፡ የሚቀበሉ ፡ ጥቂት ፡ ናቸውና ፡ የሥጋ ፡ ረዴት ፡ ወርቅ
ና ፡ ብር ፡ ወታደርም ፡ ብልሃትም ፡ ጸላታቸውንና ፡ ፅባቸው
ን ፡ ለማጥፋት ፡ አይጠቅማቸውም ፡፡

መክፈል :: ጶርቱጋል ፡ በሁለት ፡ ክፍል ፡ ትከፈላለች :: እርሳቸውም ፡ ያይነተኛ ፡ ጶርቱጋል ፡ መንግሥት :: የአልጋርብያም ፡ መንግሥት ::

ላይነተኛ ፡ ጶርቱጋልም ፡ ፫፤ ጵሮዊንሶት ፡ አልዋት ፡ እርሳቸውም ፡ እስትረመደራ :: በይራም :: እንትረ ፡ ዱሮኤሚንኮም :: ትራሶስ ፡ ሞንተስም :: አሌንቴዮም ::

ታላቆች ፡ ከተሞችና ፡ አህጋርም ፡ እሌህ ፡ ናቸው ::

ሊስቦን ፡ የጶርቱጋል ፡ ሁሉ ፡ ከተማ ፡ ፵፩፤ ሺህ ፡ ቤቶችና ፡ ፴፻፻፤ ሰዎች :: ከርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ እንግዶች ፡ እንግሊዞች ፡ ፈራንሲሶችም ፡ ንምሳዎችም ፡ አይሁድም ፡ ኻንክሎችና ፡ ሙለቶችም :: ከዚያም ፡ የሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ መቀመጫ ፡ ነው :: ፫፻ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት :: ፶፤ ገዳሞችም :: ታላቅ ፡ ሆስጲታልም :: ቤትም ፡ ተጥለው ፡ የተገኙ ፡ ሕፃናት ፡ ወደ ፡ ሚያሳድግዋቸው :: ታላቅ ፡ ቢብልዮቴካም ፡ የንጉሥ ፡ ገንዘብ ፡ ፲፻፻፤ ትራዝን ፡ የሚዝ :: አያሌ ፡ አካዴምዮችም :: መልወጫም :: የከበረም ፡ የውኃ ፡ መንገድ ፡ በ፴፫፤ በመርሞር ፡ ቀስቶች ፡ ላይ ፡ የተሰራ :: ታላቅና ፡ ደህና ፡ መርስም ፡ ብዙ ፡ ታላቆች ፡ መርከቦች ፡ የሚጠጉበት :: ለጶርቱጋል ፡ መሻየጥም ፡ ሊስቦን ፡ መጀመርያ ፡ ስፍራ ፡ ናት :: ቤሌምም ፡ በሚሉት ፡ በከተማ ፡ ክፍል ፡ ለሄሮኒሚቶች ፡ የተዋበ ፡ ገደም ፡ አላቸው :: ከዚያም ፡ የነገሥታት ፡ ቤትና ፡ መቃበር ፡ አሉ :: እጅግ ፡ መፍረስም ፡ ሆነ ፡ ባመት ፡ ፲፯፶፭፤ ምድር ፡ በተናወጠች ፡ ጊዜ ::

መፍራ :: ያውጉሥቲኖች ፡ ታላቅ ፡ ገደምና ፡ የመርሞር ፡ ቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ወደሉበት ፡ ፮፤ የንጉሥ ፡ ቤቶችም ::

ችንትራ ፡ የንጉሥ ፡ አምባና ፡ ገደም ፡ ወደሉበት :: ያም ፡ በ፮፤ ሚልዮንና ፡ ፳፻፤ ሺህ ፡ ቅርሽ ፡ ተሠራ ::

ቶረስ ፡ ዌድረስ :: ሴቱዋል ፡ ፲፮፲፻፤ ሰዎች ፡ የባሕርን ፡ ጨው ፡ ከዚህ ፡ እጅግ ፡ ያፈላሉ ፡ የሙስካት ፡ ወይንም ፡ ይወጣል ::

ኮይምብራ ፡ ፲፫፲፻፤ ሰዎች :: የከበረችም ፡ ኡኒዌርሲታስ ::

ራሮች : የኢ.ቤርያም : ተራሮች : ሴራ. : ሞሬናም :: ካጶችም :: ካጵ : ፊኒስተሬ : ኦርትጋልም : ተርፋልጋርም : ጋታም : ጳሎስም : ማርቲንም :: ታላቆች : ወንዞችም :: ታጉስ : ኤብሮም : ጓደልኲዊርም : ሚኘኆም : ዱኤሮም : ጓድያናም : ቲንቶም ::

ምድር : የምታውጣ :: ብዙ : እንስሶች : ደህናም : የበግ : ጸጉር : ፈረ.ስም : አህያም : በቅሎም : የሀር : ትልም : የበረኻ : ብሬም : ደህናም : የልዩ : ልዩ : አይነትም : ወይን : የደቡብ : ፍሬም :: ጥጥም : ሡክርም : ዘይትም : ቶምባኾም : እህልም : ኮርክም : ሶደም : የጻፈጠ : እንጨትም :: የከበረ : ሜታሎችም : ነሣስም : ብረትም : ባዜቃም : የባሩድ : ጭውም : የወጽ : ጭውም ::

የጅ : ስራ :: መሻየጥም :: ሀር :: የተልባግርም :: ሸማም :: የጉኝ : ልብስም : ተምበኾም :: ኮርድዋንም :: ሰምናም :: ክርታስም :: ማስተወትም :: የብረት : ስራም : ለጉደያቸው : ግን : አይበቃም :: ወደ : ሌላ : አገር : የሚሻየጥ : ይህ : ነው :: በግ : የበግ : ጸጉርም : ወይንም : ወርቅም : ብርም ::

ባላገሮች :: ፲፩ ሚልዮን : ያህላሉ :: ቋንቋቸውም : የጶርቱጊዝን : ቋንቋ : ይመስላል : እንጅ : ለብቻው : ነው :: አምልኳቸውም : የሮምያ : አምልኮ : ነው :: ፫ ሚትሮጶሊ.ታኖችም : ፶፩ ኤጲስቆጶሳትም : አልዋቸው :: ጵሮትስታንቶችም : በቅድም : በዚች : መንግሥት : እጅግ : ተሳደዱ : ማንም : ጥቂት : ሲጠራጠር : በቄስ : ወይስ : በጳጳስ : በትምህርቱ : ወይስ : ባካሔደ : በሞነክሶች : ፍርድ : ሞተ :: አሁን : ግን : አለማመን : በዝትዋልና : ያች : ፍርድ : ተሻረች :: ከቅድምም : ጵሮትስታንቶችን : የእግዚአብሔርን : ቃል : ተከታዮች : እንደ : አሳደደ : እንዴሁም : አሁን : ሞነክሶችንና : ቀሳወስታቸውን : ያሳደሉ ::

የመንግሥት : መግዛት :: እንደ : ጶርቱጋል : ነው :: የንጉሥ : ፈቃድ : በኮርተስ : ጉባኤ : ተወሰነች :: በንጉሥ : ሞትም : ወንድ : ልጅ : ባይኖር : ሴት : ልጅ : ትነግሣለች :: ዛሬም : የሞተው : ንጉሥ : ሴት : ልጅ : ታናሽ : ስትሆን :

እናትዋ : ትነግሣለች : ዕድሜዋ : እስኪፈጸም : ድረስ :: የ
ልጂቱም : ስም : ኢሳቤላ : ነው :: እናትዋም : ክርስቲ
ና : ትባላለች :: የሞተ : ንጉሥ : ወንድም : ግን : ከርሎስ :
የሚባል : መንግሥትን : ይፈልጋል : ስለዚህ : አሁን : ፲ አ
መት : የሚያህል : ጾርን : ያደርጋሉ : እርሱ : በርሳቸው :
እንዲሁም : አገራቸውን : ያጠፋሉ ::

መክፈል :: በ፲፬ በቅድም : መንግሥታት : በነበሩ : ክፍ
ሎች : ስጳንያ : ትከፈላለች ::

## ፩ አዲስ : ከስቲልያ ::

እርስዋም : በ፭ ግዛቶች : ተከፈለች :: ፩፩ መድሪድ ::
፪፪ ቶሌድ :: ፫፫ ጊደለክሳ :: ፬፬ ኵንካ :: ፭፭ ለመንካ ::

መድሪድ : ታላቅ : ከተማ :: ፳፲፻ ቤቶች : ፲፯፻፻ ሰዎች
ም :: ፫፯ አብያተ : ክርስቲያናትም : ፫፩ ገደሞችም :: የ
ንጉሥ : ቤት : ታላቅና : ውብ : ነው : የሥእል : ታላቅ : መ
ሰብሰብያ : አለበት : የናቱራልያም : መሰብሰብያ : ቢብል
ዮቴካም : የከዋክብትም : መጠበቅያ :: የትምርትም : አ
ታክልት :: ፲፫ አካደምዮችም :: ሰን : ፈርናንደ : የሚሉ
ትም : ሆስጲታል :: አምፌቴያትርም : ለመጫወት :: የንጉ
ሥ : አምቦች : ብወንርቲሮ : እልጽራደም : አራንደዌጽም ::

ሳኬደን : የከበሩ : የጤና : ምንጮች : ያሉባት ::

ቶሌደ : በታጉስ : ደር : ፳፭፲፻ ሰዎች :: የሜትሮጶሊጣን :
መቀመጫ : ኡኒዌርሲታስም ::

ጊደለክስሬ : ፲፭፲፻ ሰዎች :: ከዚያ : እጅግ : ደህና : ጉ
ኝ : ይሰራሉ ::

አልሜደ : የባዜቃ : ተራራ : ወደለባት ::

ተለዌራ : ደለረይና : ታላቅ : ማስተማርያ :: የሐር
ም : መስሪያ ::

## ፪ የቅድም : ከስቲልያ ::

በ፬ ክፍል : ተከፈለች :: ፩፩ ቡርጎስ :: ፪፪ ሶርያ ::
፫፫ ስጎዊያ : ፬፬ ስዊላ ::

ቡርጎስ : ፲፩፲፻ ሰው :: የሜትሮጶሊታን : መቀመጫ ::
ኡኒዌርሲታስ :: የበግ : ጸጕርም : ገቢያ ::

ሰንታንድር ፡፡ ፱፻ ሰዎች ፡ መርስም ፡ የመሻየጥም ፡ ስፍራ ፡፡

ስኅዊያ ፡ ፱፲፻ ሰዎች ፡፡ የብር ፡ መቅረጫ ፡፡ የትረያኑስ ፡ ውኃ ፡ መንገድ ፡፡ የረቂቅ ፡ ጉኝ ፡ መስሪያ ፡፡ የበግ ፡ ጸጉር ፡ መሻየጥ ፡፡

ሰን ፡ ኢልድፎንሶ ፡ የንጉሥ ፡ አምባ ፡፡ የሥእልና ፡ የተጸረቡ ፡ አምሳል ፡ መሰብሰብያ ፡፡ የማስተወትም ፡ መስሪያ ፡፡

እስኩርያል ፡ የንጉሥ ፡ ታላቅ ፡ አምባ ፡ መሥሪቱ ፡ ፲ ሚልዮን ፡ ብር ፡ የፈጀ ፡ ፲፬፲፻ መሳኮት ፡ የብርሃን ፡ ማስተወት ፡ ደጀች ፡ ያሉበት ፡፡ ታላቅ ፡ ቢብልዮቴካም ፡፡ የነገሥታትም ፡ መቃበር ፡፡

## ፫ ፡ አስቱርያ ፡፡

ኦዌደ ፡ ፳፲፻ ፡ ሰዎች ፡፡ ኡኒዌርሲታስ ፡፡ የነፍጥም ፡ መስሪያ ፡፡ የስራ ፡ ቤት ፡ ለክፉ ፡ አድራጎች ፡፡ የተጣሉ ፡ ሕፃናትም ፡ ቤት ፡፡

## ፬ ፡ ገሊጵያ ፡፡

ስን ፡ ያጎ ፡ ደ ኮምጶስተላ ፡፡ ፳፪፲፻ ሰዎች ፡ የሜትሮጶሊታን ፡ መቀመጫ ፡ ኡኒዌርሲታስ ፡፡ ለነፍሳቸውም ፡ መድኃኒት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ክርስቶስን ፡ የማያውቁ ፡ ወደዚህ ፡ ይሔደሉ ፡፡

ኮሩና ፡ ፲፩፲፻ ሰዎች ፡፡ መርስ ፡ የመርከቦችም ፡ ማበርያ ፡ ግምብ ፡፡ እጅግ ፡ መሻየጥም ፡፡ የተልባግርና ፡ የቦርኔታ ፡ መስሪያ ፡፡

ፈሮል ፡ የጾር ፡ መርስ ፡ የነፍጥና ፡ የመድፍም ፡ መሰብሰብያ ፡፡

## ፭ ፡ ሌዎን ፡፡

ወለደሊድ ፡ ፳፭፲፻ ሰው ፡ ኡኒዌርሲታስ ፡፡ ጌዎግራፊቂ ፡ አካደሚያ ፡፡ መስሪዮችም ፡፡

ሰለመንካ ፡ ፲፫፲፻ ሰው ፡፡ የስጳንያ ፡ መጀመርያ ፡ ኡኒዌርሲታስ ፡፡

ኪዊደድ ፡ ሮድሪጎ ፡ ፰፲፻ ሰው ፡ ብርቱ ፡ አምባ ፡፡

## ፮፤ እስትረማዱራ ፡፡

ባዳዮጽ ፡ በጓዲድያና ፡ ወንዝ ፡ ፲፪፲፻፤ ሰው ፡፡ የወሰን ፡ አምባ ፡፡

ጵላጸንጪ ፡ ፭፲፻፤ ሰው ፡፡

## ፯፤ አንደሉስያ ፡፡

ኮርዶባ ፡ በጓደልኩዊር ፡ ወንዝ ፡ ፭፻፻፤ ሰው ፡፡ የተዋበች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡፡ የፈረስ ፡ ማሳደግያና ፡ ገቢያ ፡፡ ሉካኑስና ፡ ፪፤ ሲኒኮች ፡ ከዚህ ፡ ተወለዱ ፡፡

ስዊልያ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡፡ መከበብያዋም ፡ ፻፹፯፤ ግምብ ፡ አለው ፡፡ ፲፫፲፻፤ ቤቶች ፡፡ ፱፻፻፤ ሰዎች ፡፡ የሜትሮጶሊታን ፡ መቀመጫ ፡፡ ታላቅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ የኮሎምብ ፡ መቃበር ፡ ወደለበት ፡፡ የቶምበኾ ፡ መስሪያ ፡፡ ብዙም ፡ የሀር ፡ መስሪዮች ፡፡ የባሕር ፡ መሻየጥ ፡፡ የሮምያ ፡ ቄሣሮችም ፡ ትረያኑስ ፡ ሃድርያኑስም ፡ ቴዎደስዮስም ፡ ከዚህ ፡ ተወለዱ ፡፡

ሼሬስ ፡ ፰፲፻፤ ሰው ፡ እጅግ ፡ ወይን ፡ ከዚህ ፡ ይወጣል ፡፡

ካዲክስ ፡ የመሻየጥ ፡ መጀመርያ ፡ ከተማ ፡ በስጳንያ ፡ ፲፫፰፻፤ ቤቶች ፡ ፸፲፻፤ ሰዎች ፡፡

ጊብረልጣር ፡ እጅግ ፡ ብርቱ ፡ ከተማ ፡ የእንግሊዞች ፡ ገንዘብ ፡ በስጳንያ ፡፡ ደህና ፡ መርስ ፡፡ ፱፲፻፤ ሰው ፡፡ እድግ ፡ መሻየጥ ፡፡

## ፰፤ ግራነደ ፡፡

ግራነደ ፡ ፭፲፻፤ ሰው ፡፡ በድሮ ፡ የእስላሞች ፡ ነገሥታት ፡ መቀመጫ ፡፡ የተዋበች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡፡ ኡኒቬርሲታስም ፡፡ የሀርም ፡ መስሪዮች ፡፡

መለጋ ፡ ፯፻፻፤ ሰዎች ፡፡ ደህና ፡ መርስ ፡፡ እጅግ ፡ መሻየጥ ፡ በወይን ፡ በዘይትም ፡ በደቡብ ፡ ፍሬም ፡ በሀርም ፡፡ ደህና ፡ ወይንም ፡ ከዚህ ፡ ይበቅላል ፡፡

## ፱፤ ሙርጽያ ፡፡

ሙርጽያ ፡ ፴፯፲፻፤ ሰው ፡፡ የሀር ፡ መስሪያ ፡፡ የጤና ፡ ምንጬም ፡፡

ክርታግና : ፷፱፲፻፡ ሰው :: አምባ :: ደህና : መርስ :: ለባሕር : ጾርም : ያለ : መድፍና : ነፍጥ : ከዚያ : ይሰበሰባል :: መኻየጥ ::

## ፲፡ ዋለንጫ ::

ዋለንጫ : ፲፻፻፡ ሰው :: ግሪ.ዋም : የተባለ : መርስ :: የሜትሮጶሊታንም : መቀመጫ :: ታላቅ : ቤተ : ክርስቲያንም :: ኡኒቬርሲታስም :: የሀር : መስሪያም :: መኻየጥም ::

አሊከንታ : ፪፻፻፡ ሰዎች :: መርስ :: እጅግ : መርከቦችና : መኻየጥ :: ብዙ : ወይንም ::

## ፲፩፡ ከተሎንያ ::

በርቸሎና : ፲፫፻፻፡ ሰው :: ብርቱ : ከተማ : መርስም : ኡኒቬርሲታስም : ታላቅ : አርስናልም :: መድፎችም : ከዚህ : ይቀለጣሉ :: የስጳንያ : ስራ : ሁሉ : መጀመርያ : መስሪያ : ከሌላ : ይልቅም : በሀርና : በጥጥ :: እጅግ : መኻየጥም ::

መታሮ : ፷፩፲፻፡ ሰው : የሀርና : የጥጥ : መስሪያ :: መኻየጥም ::

ታራጎና : ፻፻፡ ሰው : መኻየጥ : መርስም ::

ሞንትሰረት : የቤኔዲክቲኖች : ገደም :: ሎዮላም : ከዚህ : ተወለደ ::

## ፲፪፡ አራጎንያ ::

ሰረጎሳ : በኤብሮ : ወንዝ : ፰፻፻፡ ሰዎች :: የሜትሮጶሊታን : መቀመጫ :: ኡኒቬርሲታስም :: የሀርም : የበግ : ጸጉርም : የሌላ : ስራም : መስሪዮች :: እጅግ : መኻየጥም ::

## ፲፫፡ ቢስካያ ::

ጶንጵሉና : ፲፩፲፻፡ ሰው :: አምባ :: ኡኒቬርሲታስም ::

ቢልባዎ : ፲፰፲፻፡ ሰው : የነጋደች : ቤቶች : ከርሳቸውም : ብዙ : እንግሊዞች :: እጅግ : መኻየጥ : በበግ : ጸጉር ::

ሰን : ሴበስትያን : ፲፪፲፻፡ ሰው : ብርቱ : መርስ :: የመብሪት : ግምብ : ለመርከበኞች :: እጅግ : መኻየጥ : በብረትና : በሌላ : እቃ ::

## ፲፱ ማዮርካ ።

የባሌኣር ፡ ደሴቶች ፡ ፩ ማዮርካ ፡ ከኩበሬራና ፡ ከድራጎኔራ ፡ ጋራ ፡ ፲፰፻፻ ሰዎች ። ፪ ሚኖርካ ፡ ፫፻፻ ሰዎች ። ከዚያም ፡ ጾርት ፡ ማሆን ፡ አለ ፡ ብርቱ ። አምባ ፡ ከላዘሬቶና ፡ ከደህና ፡ መርስ ፡ ጋራ ።

የጲትዩስ ፡ ደሴቶች ፡ ኢቪሳና ፡ ፎርመንቴራ ።

ለስጳኝያም ፡ በቅድም ፡ ብዙ ፡ ግዛት ፡ ነበረ ፡ በአሜሪካ ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ ሁሉ ፡ ሸፈጥዋልና ፡ ጥቂት ፡ ቀረላት ።

ባፈሪካም ፡ ያለ ፡ የስጳኝያ ፡ ግዛት ፡ ይህ ፡ ነው ። ቸውታ ፡ ሜሊላም ፡ ጰኖን ፡ ደዋሌጽም ፡ የከናርያ ፡ ደሴቶችም ፡ ያንቦያም ፡ የፈርናንደ ፡ ደልጶም ፡ የጋዂም ፡ ደሴቶች ።

ከእስያ ፡ ደሴቶችም ። የፊሊጲኖች ፡ የላድሮኖችም ፡ የባሽም ፡ ደሴቶች ፡ የስጳኝያ ፡ ግዛት ፡ ናቸው ።

---

## ፈራንስ ።

ስፈራ ፡ ወሰንም ፡ ታላቅነትም ። ርዝመት ፡ ከ፭° ምዕራብ ፡ እስከ ፡ ፰° ምሥራቅ ። የሰሜን ፡ ወርድዋም ፡ ፵፪° — ፶፩° ነው ። ወሰንዋም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ኢጣልያ ፡ ሄልዌትያም ፡ ንምሳም ፡ ናቸው ። ወደ ፡ ደቡብም ፡ መኻከለኛ ፡ ባሕር ። ወደ ፡ ምዕራብም ፡ ስጳኝያና ፡ የምዕራብ ፡ ውቅያኖስ ። ወደ ፡ ሰሜንም ፡ የሰሜን ፡ ባሕር ፡ በልጊዩምም ፡ ንምሳም ። ታላቅነትዋም ፡ ፪፰፩፲፪ ሚላ ፡ በወርድና ፡ በርዝመት ፡ ታህላለች ።

የምድር ፡ ጠባይዕ ። ክሊማ ፡ መኻከለኛ ፡ ነው ። ምድርም ፡ ባያሌ ፡ ስፈራ ፡ እንጅ ፡ ፍርያም ፡ ናት ። ተራሮች ። ጲረኔዎች ። አልጶችም ። ዩራም ። አርደኖችም ። የኦወርኘም ፡ ተራሮች ። ሴወኖችም ። ወጌሶችም ። ካጾች ። ካጽ ፡ ፊኒስተሬና ፡ ካጽ ፡ ደላሆክ ። ታላቆች ፡ ወንዞች ። ልዋር ፡ ጋሮናም ፡ ደርደኝም ፡ ሴናም ፡ ሮናም ፡ ረደንም ። አያሌም ፡ የተቈፈረ ፡ መስኖች ፡ መርከብ ፡ የሚሰርባቸው ።

ምድር ፡ የምታወጣ ። እህል ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ወይንም ፡ ዘይትም ፡ ከጽርም ፡ ለውዝም ፡ ከስታንያም ፡ የዛፍም ፡

ፍሬ ፡ እጅግ ፡፡ ማርም ፡ ሰፍሪንም ፡ የተልባግርም ፡ ከነቢስ
ም ፡ ሀርም ፡ ቶምባኮም ፡ ሰምዕም ፡ እንጨትም ፡ ለመጸ
ረብና ፡ ለመንደድ ፡፡ ላምም ፡ በግም ፡ ፍየልም ፡ ፈረስም ፡
በቅሎም ፡ ዓሣም ፡፡ ነሓስም ፡ እጅግ ፡ ብረትም ፡ ጥቂት ፡ ብ
ሩርም ፡ ብዙም ፡ የድንጊያ ፡ ቀሰል ፡ ጭውም ፡ የሚነሬል ፡
ምንጨችም ፡፡

የጅ ፡ ስራ ፡፡ መሻየጥም ፡፡ የሀር ፡ ስራ ፡ ሽሽም ፡ የወ
ርቅና ፡ የብር ፡ ልብስም ፡ በጅም ፡ የተሰራ ፡ የሽልም ፡ ልብ
ስ ፡ የሀርም ፡ ሾራብና ፡ ማሰርያ ፡ ጉኝም ፡ የተልባግርና ፡ የ
ሸማም ፡ ስራ ፡ ሁሉ ፡ ታጼቶችም ፡ ቀርበትም ፡፡ ነፍጥም ፡
የዝናድና ፡ የብረት ፡ እቃም ፡ ጨንም ፡ ቦርኔታም ፡ ዘርፍ
ም ፡ ክርታስም ፡ ማስተወትም ፡ የሽልምና ፡ የጫወታ ፡ ስራ
ም ፡ የሚቀርም ፡፡ መሻየጥም ፡ እጅግ ፡ ነው ፡፡

ባላገሮች ፡ ፴፫፡ ሚልዮን ፡ ናቸው ፡፡ መጀመርያ ፡ ቋንቋ
ቸው ፡ ፍሪንሲስ ፡ ነው ፡፡ ያለርቱም ፡ የንምሳውን ፡ የብር
ታኛንም ፡ የበስክንም ፡ የኢጣልያንም ፡ ቋንቋች ፡ ይናገሪ
ሉ ፡፡ የብዙም ፡ አምልኮ ፡ የሮምያ ፡ አምልኮ ፡ ነው ፡ ከዚ
ያም ፡ ጋራ ፡ ጽሮትስታንቶች ፡ አይሁድም ፡ እሥላሞችም ፡
ኢያምልኳቸው ፡ ይቀመጣሉ ፡፡ በውቀትና ፡ በብልሃት ፡ ፍ
ሪንሲሶች ፡ እጅግ ፡ ያድርጋሉ ፡ በሃይማኖት ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡
ነው ፡ የሚያድርጉት ፡፡

የመንግሥት ፡ መግዛት ፡፡ ንጉሥ ፡ ከሕዝቡ ፡ ጉባኤ ፡
ጋራ ፡ ይገዛል ፡፡ ሕጉን ፡ ሥርዓትንም ፡ አብረው ፡ ይቈርጣ
ሉ ፡ ንጉሥም ፡ ለተሰሪች ፡ ሕግ ፡ ኃይሉን ፡ ይሰጣል ፡፡ የቀ
ድም ፡ ንጉሥ ፡ ቻርልስ ፡ ፲፡ ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፡ ተጻልተዋልና ፡
ፍሪንሲሶች ፡ ሻሩት ፡ ባሠት ፡ ፲፰፴፡ ሌላውንም ፡ ልዊስ ፡
ፌሊጵ ፡ የሚሉትን ፡ ዘመዱን ፡ አነገሡት ፡ እርሱም ፡ ዛሬ ፡
ይነግሣል ፡፡

መክፈል ፡፡

ፍሪንስ ፡ በ፹፮፡ ዴጳርትመንቶች ፡ በ፫፻፷፡ ዙርዮችም ፡
በ፪፯፻፱፡ ከንቶኖችም ፡ በ፴፰፱፯፡ ጉባኤዮችም ፡ ተከፈ
ለች ፡፡

ኮምጴኝ ፡ የንጉሥ ፡ አምባ ፡፡ የመድፉም ፡ ማስተማርያ ፡፡

፬፡ ሴናና ፡ ማርና ፡፡

ሚሉን ፡፡ ሞክስ ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ መቀመጫ ፡፡

ፎንቴንብሎ ፡፡ ቦናጳርት ፡ ከዚህ ፡ ባመት ፡ ፲፰፲፬፡ መንግሥቱን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ፡ በነገሥታት ፡ እጅ ፡፡

፭፡ ኤስና ፡፡

ላወን ፡፡ ስዋሶንስ ፡፡ ሰንካንተን ፡ መስሪዮች ፡፡

፮፡ ታችኛ ፡ ሴና ፡፡

ሩዋን ፡ ፱፻፻፡ ሰዎች ፡፡ የሚትሮጶሊታን ፡ መቀመጫ ፡፡ የወርቅና ፡ የብርም ፡ መቅረጫ ፡፡ መርስም ፡፡ ታላቆች ፡ መስሪዮችም ፡፡ መሻየጥም ፡፡

ድየጳ ፡ አምባ ፡ ፰፲፻፡ ሰው ፡፡

ሣብር ፡ ድግረስ ፡ ፲፭፲፻፡ ሰው ፡፡ ብርቱ ፡ መርስ ፡፡

፯፡ ኤውር ፡፡

ኤብሬው ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ መቀመጫ ፡፡ ሉዌ ፡ መስሪዮች ፡፡

፰፡ ከልዋደስ ፡፡

ካኦን ፡ ፫፻፻፡ ሰዎች ፡ ኡኒዌርሲታስ ፡ መስሪዮችም ፡፡

፱፡ ለማንሽ ፡፡

ሸርቡርግ ፡ አምባ ፡ የጾርም ፡ መርስ ፡፡ የመርከቦችም ፡ መስሪያ ፡፡ መሻየጥም ፡፡

፲፡ ኦርና ፡፡ አላንሶን ፡ መስሪዮች ፡፡ ፲፩፡ ኤውርና ፡ ልዋር ፡፡

፲፪፡ ኦብ ፡፡ ፲፫፡ ላይኛ ፡ ማርና ፡፡

፲፬፡ ማርና ፡፡ ረይምስ ፡ ፫፻፻፡ ሰዎች ፡፡ የሚትሮጶሊታን ፡ መቀመጫ ፡፡ ኤጵርኔ ፡ የሻምጳኝ ፡ ወይን ፡ ወደሚበቀልበት ፡ ስፍራ ፡፡

፲፭፡ አርደን ፡፡ ፲፮፡ ሶም ፡፡ አሚንስ ፡ ፬፻፻፡ ሰዎች ፡፡

፲፯፡ ጳድካሌስ ፡፡ ካሌስ ፡ ፯፲፻፡ ሰዎች ፡፡ ደህና ፡ መርስ ፡ በባሕር ፡ ደጅ ፡፡

ቡሎኝ ፡ ፲፫፲፻፡ ሰዎች ፡፡ ደህና ፡ ወደብ ፡፡

፲፰፡ ኖርድ ፡፡ ሊል ፡ ፸፰፲፻፡ ሰዎች ፡፡ ብርቱ ፡ አምባ ፡፡ ደ

፴፫፤ ዶርዶኝ ፡፡ ፴፬፤ ዢሮንድ ፡፡ ቦርዶ ፡ በዢሮንድ ፡ ወንዝ ፡፡ እጅግ ፡ መሻየጥ ፡፡ መርስ ፡፡ የሜትሮጶሊታን ፡ መቀመጫ ፡፡ ኡኒቨርሲታስም ፡፡ መልወጫም ፡፡ ብዙ ፡ መስሪዮችም ፡፡ የብረት ፡ ድልድል ፡ በወንዝ ፡ ላይ ፡፡ ደህና ፡ ወደንም ፡፡

፴፭፤ ላንድስ ፡፡ ፴፮፤ ጌርስ ፡፡ ፴፯፤ ታችኞች ፡ ጲረኔዎች ፡፡ ጶ ፡፡ ባዮና ፡፡

፴፰፤ ላይኞች ፡ ጲረኔዎች ፡፡ ፴፱፤ የምሥራቅ ፡ ጲረኔዎች ፡፡ ጶርጲኛን ፡፡

፵፤ ኦድ ፡፡ ፵፩፤ አሬዠ ፡፡ ፵፪፤ ላይኛ ፡ ጋሮና ፡፡ ቱሉሳ ፡ ፭፻፻፤ ሰዎች ፡፡ የሜትሮጶሊታን ፡ መቀመጫ ፡፡ ኡኒቨርሲታስም ፡ አካዴሚያም ፡ የከዋክብትም ፡ መጠበቅያ ፡፡

፵፫፤ ታርን ፡፡ ፵፬፤ ታርንና ፡ ጋሮና ፡፡ ሞንቶባን ፡ የጵሮት ስታንቶች ፡ አካዴሚያ ፡፡

፵፭፤ ህሮልት ፡፡ ሞንትጶሌር ፡ ፵፪፲፻፤ ሰው ፡ ኡኒቨርሲታስም ፡፡

፵፮፤ ጋርድ ፡፡ ኒምስ ፡ ፱፻፻፤ ሰው ፡፡ አካዴሚያ ፡፡ የሾራብና ፡ የሀር ፡ መስሪዮችም ፡፡

፵፯፤ ሎዜር ፡፡ ፵፰፤ አርዴሽ ፡፡ ፵፱፤ ድሮም ፡፡ ዋላንስ ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ መቀመጫ ፡፡

፶፤ ኢዜር ፡፡ ግሬኖብል ፡ ፭፲፻፤ ሰው ፡፡ ኡኒቨርሲታስ ፡፡

፶፩፤ ላይኞች ፡ አልጶች ፡፡ ፶፪፤ የሮና ፡ አፎች ፡፡ መርሰልያ ፡፡ አሮጊት ፡ አገር ፡ ፲፻፻፤ ሰዎች ፡ እጅግ ፡ መሻየጥ ፡፡ ኤክስ ፡ የሜትሮጶሊታን ፡ መቀመጫ ፡፡

፶፫፤ ታችኞች ፡ አልጶች ፡፡ ፶፬፤ ባር ፡፡ ቱሎን ፡ ፭፪፲፻፤ ሰው ፡፡ የጶር ፡ መርስ ፡፡

፶፭፤ ዋክሉስ ፡፡ አዊኞን ፡፡ በሮና ፡ ወንዝ ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ መቀመጫ ፡፡

ከሌሀ ፡ ዲጶርትመንቶችም ፡ ሌለ ፡ የፍራንስ ፡ ግዛት ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡

የኮርሲካ ፡ ደሴት ፡፡ ፻፵፭፲፻፤ ሰው ፡፡ አያቾ ፡ የቦናጶር

ት : የልደቱ : ስፍራ :: ደግሞም : አልጊርስ : ከሥላሞች : የወሰዷ : ባመት : ፲፰፴፡፡

በህንድም : ጶንዲሸሪ : ከሪካልም : ሸንድርናጉ ርም ::

ባፍሪካም : ሴኔጋል : ጎሬም : የቡርቦን : ደሴትም ::

ባሜሪካም ፤ ካየናና : አያሌ : ደሴቶች ::

---

## ታችኛ : ምድር ::

ደህች : ምድር : በቀድም : አንዲት : መንግሥት : ሁና : አሁን : ከ፲፤ አመት : በፊት : ሁለት : መንግሥታት : ሆነች :: የበልግዩም : ሰዎች : በንጉሣቸው : በሆላንድ : ንጉሥ : ዐ ምፀዋልና : ለሪሳቸውም : ንጉሥን : አድርገዋልና ::

በልግዩም : ወደ : ደቡብ : ናት : ሆላንድም : ወደ : ሰሜ ን :: የሁለታቸውም : ክሊማ : መኻከለኛ : ነው :: የሆለን ድ : ምድርም : እጅግ : ዝቅ : ትላለችና : ሁሉም : ውኃም : ናት : ሁሉም : ፍርያም : ናት ::

ጉበቶችና : ውኖች :: የዙይድር : ባሕር : ደላርትም : ቢ ስቦሽም :: ወንዞችም :: ረደን : ማስም : ሸልደም :: ብ ዙ : መስኖችም : አሉ : ወንዞችን : እርሶ : በርሳቸው : የ ሚያገናኙ ::

ምድር : የምታወጣ :: እህል : ጸታትስም : ቶምባኾ ም : ተልባም : ከነቢስም : ሸልገምም : የዛፍ : ፍሬም : ወ ደንም : አበባም : ለመሻየጥ : እንጨትም :: እጅግ : ደህ ና : ላምም : በግም : ፈረስም : ነብም : ዓሣም : ብረትም : እርሳስም : ነሃስም : የደንጊያ : ቀሰልም : የሸህላ : መሬ ትም : ገልመደም : ደ'ንም : ጭውም : የሚነሪል : ውኃም ::

እጅግ : መስሪዮችም : አሉ :: የሚሰሩትም : ደህ : ነ ው :: እጅግ : ደህና : የበግ : ጸጉር : ሸማ :: ደህናም : የተል ባግር : የጥጥም : ስሪ : ክርታስም : የሸህላ : ስሪም :: ቶ ምባኾም : የብረትና : የቀርበትም : ስሪ : ሠከርም : አረ ቂም :: ወፍጮችንና : መርከቦችንም : እጅግ : ደሰራሉ :: መሻየጥም : እጅግ : ነው ::

ዌርሲታስ ፡፡ የሮማያ ፡ ሚትሮጶሊታንም ፡ መቀመጫ ፡፡ የ
መጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ ጉባኤ ፡፡

፫፡ ሴለንድ ፡ ደህ ፡ ክፍልም ፡ በ፯፡ ደሴቶች ፡ ነው ፡፡

፱፡ ገልድርስ ፡፡ ኒምዌግን ፡ ብርቱ ፡ አገር ፡ ፲፻፲፻፡ ሰው ፡፡

፲፡ የሰሜን ፡ ብራበንት ፡፡ ደርትረኽት ፡ ፲፫፲፻፡ ሰው ፡፡
መርስ ፡፡ የንጨት ፡ መቍረጫ ፡፡ የታላቅ ፡ ሲኖደስ ፡ መሰብ
ሰብያ ፡ ባመት ፡ ፲፯፲፫፡፡

፲፩፡ የሊምቡርግ ፡ ክፍል ፡፡ ፲፪፡ ሉክሰምቡርግ ፡፡

ለሆላንድም ፡ ብዙ ፡ ግዛት ፡ አለ ፡ በስያ ፡ እርሱም ፡ በያ
ዋ ፡ ደሴት ፡ በሱመትራ.ም ፡ ቦርኔዎም ፡ ሴልቤስም ፡፡

በአፍሪካም ፡ በጊኔያ ፡ ደር ፡ ጥቂት ፡ ግዛት ፡ አላቸው ፡፡
በአሜሪካም ፡ ሱሪናም ፡ እውስታኪዩስም ፡ ቅዱስ ፡ ማ
ርቲንም ፡ ኩረሳዎም ፡፡

---

## ታላቅ ፡ ብርታንያና ፡ ኢርለንድ ፡፡

ስፍራ ፡፡ ወሰንም ፡፡ ታላቅነትም ፡፡ እሌህ ፡ ፪፡ ደሴቶ
ች ፡ ከሚቀሩ ፡ ከኤውሮጳ ፡ ደሴቶች ፡ ይበልጣሉ ፡፡ የሰሜ
ን ፡ ወርደቸው ፡ ፵፱°፡ ፶፩'፡—፷°፡፡ ርዝመታቸውም ፡ ፲°፡ ፲፯'፡
ምዕራብ ፡ እስከ ፡ ፩°፡ ፶'፡ ምሥራቅ ፡ ነው ፡፡

ወሰንዋም ፡ በምሥራቅ ፡ የሰሜን ፡ ባሕር ፡ ነው ፡ በደ
ቡብም ፡ የከለይስ ፡ ደጅ ፡፡ በምዕራብም ፡ የምዕራብ ፡ ው
ቅያኖስ ፡፡ በሰሜንም ፡ የከሌደንያ ፡ ባሕር ፡፡ ታላቅነትዋ
ም ፡ በወርድና ፡ በርዝመት ፡ ፻፲፪፱፵፩፡ ሚላ ፡ ነው ፡፡

የምድር ፡ ጠባይዕ ፡፡ ታላቅ ፡ ብርታንያ ፡ እንግልጣርና ፡
ስኮትለንድ ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ በንግልጣርና ፡ በኢርለንድ ፡ ክ
ሊማ ፡ መኻከለኛ ፡ ነው ፡ ምድርም ፡ እጅግ ፡ ታፈራለች ፡፡
በንግልጣርም ፡ እጅግ ፡ የተሰሪ.ች ፡ ናት ፡፡ ታላቆችም ፡ ተራ
ሮች ፡ ጥቂት ፡ ናቸው ፡፡ በስኮትለንድ ፡ በዌልስም ፡ በኢርለ
ንድም ፡ አያሌ ፡ ተራሮች ፡ አሉ ፡ በላያቸው ፡ ክሊማ ፡ ብር
ቱ ፡ የሚሆን ፡፡ ካጾችም ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡ ካጽ ፡ ለንድ
ስንድና ፡ ለይዘርድ ፡ በንግልጣር ፡ ደንግስቢሄድም ፡ በስኮ
ትለንድ ፡ ክሊርም ፡ በኢርለንድ ፡፡ ታላቆች ፡ ወንዞች ፡ በ

እንግልጣር ፡፡ ቴምስ ፡ ትረንትም ፡ ሴወርንም ፡ መርሴም ፡፡ እሌህም ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ በመልካሞች ፡ መስኖች ፡ ተገናኙ ፡፡ ታላቆች ፡ መስኖችም ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡ ግረንድ ፡ ጀንክሽን ፡ መስኖ ፡ የኑኦክስፎርድም ፡ መስኖ ፡ እርሳቸውም ፡ የቀረም ፡ መስኖች ፡ በብዙ ፡ ብር ፡ ተሰሩ ፡ መርከቦችን ፡ ባገር ፡ ሁሉ ፡ ለማሳለፊ ፡፡ የስኮትለንድም ፡ ወንዞች ፡፡ ቴ ፡ ስፔም ፡ ትዊድም ፡ ፎርትም ፡ ክለይድም ፡፡ የግለስጎም ፡ መስኖ ፡ ከሰሜን ፡ ባሕር ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ውቅያኖስ ፡ ይሔደል ፡፡ በኢርለንድም ፡ የሽኖንና ፡ የበሮ ፡ ወንዞች ፡ አሉ ፡፡ የምድርም ፡ ባሕሮች ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡ በእንግልጣር ፡ የዊንንድር ፡ ባሕር ፡ ፲፯፤ ደሴቶች ፡ ወደሉበት ፡፡ የሃውስ ፡ ውኃም ፡፡ በስኮትለንድም ፡ ሎኽ ፡ ለሞንድ ፡ ፳፰፤ ደሴቶች ፡ ወደሉበት ፡ ሌሎችም ፡፡

ምድር ፡ የምታወጣ ፡፡ በእንግልጣር ፡፡ እህል ፡ ሆጽም ፡ እጅግ ፡ ለከበረ ፡ ጠላ ፡፡ ጾታትስም ፡ የዛፎም ፡ ፍሬ ፡፡ ታላቅ ፡ ፈረስም ፡፡ ደህና ፡ በግም ፡፡ ማለፊያ ፡ ላምም ፡፡ ንብም ፡፡ ማለፊያ ፡ ቀርቀሮም ፡ እጅግ ፡ ነሃስም ፡ እርሳስም ፡ ብረትም ፡ የደንጊያ ፡ ቀሰልም ፡ የሚነሬልም ፡ ውኃ ፡፡ በስኮትለንድ ፡፡ እህለ ፡ ተልባም ፡ ከነቢስም ፡ እንጨትም ፡ ለመጽረብና ፡ ለመንደድ ፡፡ በኢርለንድ ፡፡ ላም ፡ በግም ፡ ተልባም ፡ ከነቢስም ፡ እህልም ፡ ጾታትስም ፡፡ ሶስታቸውም ፡ እጅግ ፡ ይተርፈሉ ፡ በርሳስ ፡ በብረትም ፡ በጭውም ፡ በደንጊያ ፡ ቀሰልም ፡ በባሕር ፡ ደርም ፡ ብዙ ፡ ዓሣውን ፡ ይበላሉና ፡ ይሸጣሉ ፡፡

የጅ ፡ ስራ ፡፡ መኻየጥም ፡፡ እንግሊዞች ፡ ስራውን ፡ ሁሉን ፡ በጢስና ፡ በሌላ ፡ መስሪያ ፡ በብልሃትም ፡ እጅግ ፡ ደግ ፡ አድርገው ፡ ይሰራሉ ፡፡ እጅግም ፡ የሚሰሩት ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ ቀርበት ፡ ዝናድም ፡ ብረትም ፡ የሚታል ፡ ሁሉም ፡ እቃ ፡፡ የበግ ፡ ጸጉርም ፡ የጥጥም ፡ የሀርም ፡ የተልባግርም ፡ ስራ ፡ ሁሉ ፡ ክርታስም ፡ የደንጊያም ፡ የጪንም ፡ እቃ ፡ የቢሉርም ፡ እቃ ፡፡ የለዚያም ፡ ቦርኔታ ፡ ሳምናም ፡ የሰዓትም ፡ የማትማቲቂም ፡ የመካኒቂም ፡ እቃ ፡ የብዙ ፡ ሌላ ፡ እቃም ፡ መስሪዮች ፡ ይበዛሉ ፡፡ የእንግሊዝም ፡ መኻየጥ ፡ ከሌላ ፡ መኻየጥ ፡ ሁሉ ፡ ይበልጣል ፡፡ የነጋደች ፡ መልወጫ ፡ በሎ

ንደን ፡ ፪፻ ሚልዮን ፡ ቅርሽ ፡ የሚያህል ፡ መዝገብን ፡ አለው ፡፡ ለመሸየጥም ፡ ብቻ ፡ የሚሰሩ ፡ መርከቦች ፡ ከ፳፲፻ ይበዛሉ ፡፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገርም ፡ ያለ ፡ መሸየጥ ፡ በያመቱ ፡ ሁሉ ፡ ፪፻ ሚልዮን ፡ ቅርሽ ፡ የሚያህል ፡ ያተርፋል ፡፡ የህንድ ፡ ኮምጳኒ ፡ የሚሉት ፡ የታላቆች ፡ ሸማቾች ፡ ጉባኤ ፡ ነው ፡፡ እርሳቸውም ፡ ካገሬቸው ፡ እጅግ ፡ የሚበልጠውን ፡ ግዛት ፡ ይደዛሉ ፡፡ መጀመርያ ፡ አገሮች ፡ ለመሸየጥና ፡ ለመርከቦች ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡ ሎንደን ፡ ሊብርጱልም ፡ ብሪስትልም ፡ ሁልም ፡ ኑካስትልም ፡ ሀሪችም ፡ ጵልመትም ፡ ጶርትስመትም ፡ ያርመትም ፡ ወይትሀውልም ፡፡ በስኮትለንድ ፡፡ ሊት ፡ ግላስጎም ፡ ደንዲም ፡ ኑአበርደንም ፡፡ በኢርለንድ ፡፡ ደብሊን ፡ ኮርክም ፡ ሊምሪክም ፡ በልፈስትም ፡፡ በጅ ፡ ስራም ፡ የሚበልጡ ፡ ከተሞች ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡ መንችስትር ፡ በርሚንግሀምም ፡ ሊድስም ፡ ኖርችም ፡ ሸፌልድም ፡ ግላስጎም ፡ ጲስሌም ፡፡

ባላገሮች ፡፡ የታላቅ ፡ ብርታንያና ፡ የኢርለንድ ፡ ሰዎች ፡ ቍጥር ፡ ፳፯ ሚልዮን ፡ ያህላል ፡፡ ከርሳቸውም ፡ ፲፮ ሚልዮን ፡ በእንግልጣር ፡ ፫ ሚልዮንም ፡ በስኮትለንድ ፡ ፰ ሚልዮንም ፡ በኢርለንድ ፡ ይቀመጣሉ ፡፡ የመንግሥትም ፡ አምልኮ ፡ ጵሮትስታንት ፡ ነው ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ አይነት ፡፡ ሁላቸውም ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስና ፡ በሚስዮን ፡ ጉደይ ፡፡ ከርሳቸውም ፡ በቀር ፡ የሌላ ፡ አምልኮ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ኢየሥርዓታቸው ፡ ኢየፈቃደቸውም ፡ ይኖራሉ ፡ እርሱ ፡ በርሳቸውም ፡ በማስተማርና ፡ በመጽሐፍ ፡ ትምርታቸውን ፡ ለመዝረጋት ፡ ይደክማሉ ፡ በግድም ፡ አይደሉም ፡፡ እንግልጣር ፡ የሰው ፡ ልጅነት ፡ መንግሥት ፡ ናትና ፡ በሃይማኖትም ፡ በአገር ፡ ሥርዓትም ፡ ባርነት ፡ የለም ፡፡ እንግልጣርም ፡ ያለም ፡ ወንጌላዊት ፡ ሆነች ፡፡ ብዙ ፡ ደህና ፡ ክርስቲያኖች ፡ አንድ ፡ ሆኑ ፡ በፍቅር ፡ መንፈስ ፡ በጨለማም ፡ ለተቀመጡ ፡ ላረማውያን ፡ ላይሁድም ፡ ለሥላሞችም ፡ ክርስቶስንም ፡ ለማያውቁ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አዝነው ፡ ከመንፈሳዊት ፡ ጨለማቸውና ፡ ከችጋሬቸው ፡ ይረድዋቸው ፡ ዘንድ ፡ ተሰማሙ ፡፡ እንደ ህም ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጉባኤ ፡

ተነሣች ፡ የሚሰዮንም ፡ ጉባእዮች ፡ የማስተማርም ፡ ጉባ
እዮች ። ታናሽ ፡ መጽሐፍንም ፡ የሚሰጡ ፡ ጉባእዮች ።
ድኖችንም ፡ በየቤታቸው ፡ አደተው ፡ ለሥጋቸውና ፡ ለነፍ
ሳቸው ፡ ደህንነት ፡ የሚደክሙ ፡ ጉባእዮች ። ስካርንም ፡
ምንዝርንም ፡ጽብንም ፡ ኃጢአትንም ፡ ሁሉን ፡ ለመሻር ፡
የጌታውንም ፡ ቀን ፡ ለመጠበቅ ፡ በወንድሞቻቸው ፡ ማኽ
ል ፡ የሚደክሙ ፡ ጉባእዮች ። እርሳቸውም ፡ በእንግሊዝ ፡
መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ ተዘርግተው ፡ መጀመርያ ፡ መቀመጫቸ
ውና ፡ መሰብሰብያቸው ፡ በሎንደን ፡ ነው ።

እንግሊዞች ፡ ስለ ፡ ብልሃትና ፡ ስለ ፡ እውቀት ፡ ሁሉ ፡ የታ
ወቁ ፡ ናቸው ። ፫፤ ኡኒቬርሲታቶች ፡ ብዙ ፡ ኮለጆችም ፡ አ
ከደሚዮችም ፡ ሌሎችም ፡ ማስተማርዮች ፡ አልዋቸው ።

የመንግሥት ፡ መግዛት ። ንጉሥ ፡ ሲሞት ፡ ከልጆቹ
ም ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ባደኖር ፡ ሴት ፡ ልጁ ፡ ትነግሣለች ። ዛሬ
ም ፡ የምትነግሥ ፡ ሴት ፡ ናት ፡ ስምዋንም ፡ ዊክቶርያ ፡
ይልዋታል ። ንጉሥም ፡ ከመንግሥቱ ፡ ጉባኤ ፡ ጋራ ፡ ሕግን ፡
ይሰራል ፡ እርሱም ፡ ለሕጉ ፡ ኃይልን ፡ ይሰጣል ። የመንግ
ሥትም ፡ ጉባኤ ፡ ጳርለመንት ፡ ትባላለች ፡ በ፪፤ ክፍልም ፡
ተከፈለች ፡ ላይኛ ፡ ቤትና ፡ ታችኛ ፡ ቤት ፡ በሚልዋቸው ። በ
ላይኛ ፡ ቤትም ፡ ሎርድስ ፡ የሚልዋቸው ፡ አካበሮች ፡ ይቀ
መጣሉ ፡ እርሳቸውም ፡ ጳጳሳትና ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ የንጉ
ሥ ፡ ዘመደችም ፡ ታላቆች ፡ መኳንንትም ፡ እርሳቸውም ፡
ለወትሩ ፡ መካሮች ፡ ናቸው ፡ ቍጥራቸውም ፡ ፬፻፤ ያህላ
ል ። በታችኛ ፡ ቤትም ፡ ያገር ፡ መለክተኞች ፡ ይቀመጣሉ ፡
እርሳቸውም ፡ በየምድራቸው ፡ በያገራቸውም ፡ የተመረ
ጡ ፡ ናቸው ፡ ላንድ ፡ አመት ፡ ያገረቸውንና ፡ የንጉሥን ፡ ጉ
ደይ ፡ ይመካከሩ ፡ ዘንድ ። እርሳቸውም ፡ ፯፻፤ ናቸው ። የ
ንጉሥም ፡ ሊቃውንት ፡ በሌህ ፡ ፪፤ ቤቶች ፡ ተከፈሉ ፡ ከጉ
ባእዮችና ፡ ከሎርድስም ፡ ጋራ ፡ ይመካከራሉ ። ንጉሥም ፡
ለራሱ ፡ ለቤቱም ፡ በያመት ፡ ፫፤ ሚልዮን ፡ ቅርሽ ፡ ይቀ
በላል ።

የመንግሥት ፡ መክፈል ።

## እንግልጣር ::

፩ ኤስክስ :: ሚድልሰክስ ::

ሎንደን ፡ በቴምስ ፡ ወንዝ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ ከተማ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ናት ። ፪ ሚልዮን ፡ ሰዎች ። የንጉሥና ፡ የጳርለመንት ፡ መኖርያ ። በቴምስ ፡ ላይ ፡ አያሌ ፡ ድልድሎች ፡ አሉ ። አንድ ፡ ድልድልም ፡ ብረት ፡ ነው ። አንድም ፡ ተነል ፡ የሚሉት ፡ መንገድ ፡ ከቴምስ ፡ በታች ፡ ይደረጋል ። ከከበሩ ፡ ቤቶች ፡ እሌህ ፡ ይታወቁ ። ቅዱስ ፡ ያዕቆብ ፡ (ሰንት ፡ ጀምስ ፡) የንጉሥ ፡ ቤትና ፡ አደሚሸ ። ተውርም ፡ ብርቱ ፡ የድሮም ፡ አምባ ፡ የመንግሥት ፡ ግዞትና ፡ መዝገብ ፡ ያለበት ። የህንድ ፡ ቤትም ። የመልወጫ ፡ ቤትም ፡ ነጋደች ፡ ሁሉ ፡ የሚሰበሰቡበት ። የእንግልጣር ፡ በንከም ። ጊልድሀውልም ። ኑጌትም ። እክስትርሀውልም ፡ ለሃይማኖትና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ለመዝረጋት ፡ የተሰሩ ፡ ጉባኤዮች ፡ ሁሉ ፡ እርሳቸውም ፡ ከ፶ የበዙ ፡ ናቸው ፡ ወደሚሰበሰቡበት ። አብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ ከ፫፻ ይበዛሉ ፡ ከርሳቸውም ፡ የምትበልጥ ፡ የቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ናት ፡ የግምብዋ ፡ ከፍታ ፡ ፪፻ ክንድ ፡ የሚያህል ። የወስትሚንስትር ፡ አቢም ፡ የምትባል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በርስዋ ፡ የሞቱ ፡ ነገሥታትና ፡ እጅግ ፡ የከበሩ ፡ ሰዎች ፡ ይቀበሬሉ ፡ አዲሶችም ፡ ነገሥታት ፡ ለመንግሥታቸው ፡ ይቀቡባታልና ፡ ይከለላሉ ። የእንግሊዝ ፡ ሙሲውምም ፡ የብልሃትና ፡ የውቀት ፡ ሁሉ ፡ መሰብሰብያ ። በርሶም ፡ ፫፻፻ ትሪዝ ፡ የሚዝ ፡ ቢብልዮቴካ ፡ አለበት ። ፹፪ ታላቆች ፡ ሆስጲታሎችም ፡ ለድውያን ፡ ፪ ሆስጲታሎችም ፡ ለእብዶች ። ፩ ኡኒቬርሲታስም ፡ ብዙም ፡ ሌሎች ፡ ማስተማርዮች ። ንጉሥም ፡ ወትሩ ፡ ፻፻ ድኖች ፡ አሽክሮችን ፡ ያሳደጋል ። የማስተማርም ፡ ጉባኤ ፡ የምትባል ፡ ብዙ ፡ መምህራንን ፡ ያሳድጋሉ ፡ በሎንደንም ፡ ባለ ፡ በማስተማርያቸው ፡ ወትሩ ፡ ፹፪፲፻ ድኖች ፡ አሽክሮች ፡ እኩሌታቸውም ፡ ወንዶች ፡ እኩሌታቸውም ፡ ሴቶች ፡ ያሳድጋሉና ፡ ያስተምርዋቸውማል ። እጅግም ፡ የሁሉ ፡ አይነት ፡ መስሪዮች ። የህንድ ፡ ኮምጳኒም ፡

ብረትና : በዝናድ :: ሊድስ : ፳፻፻ ሰዎች : የበግ : ጸጕር : መስሪዮች ::

ለንክሸር :: ለንክስትር : መርስ :: መንችስትር : ፲፻፻ ሰው :: ከዚያ : እጅግ : በጥጥ : ይሰራሉ : በሀርም : በበግ : ጸጕርም :: ሊብርጱል : ሁለተኛ : ከተማ : ለመሸየጥ : ፲፻፻ ሰው :: ሰዓትም : ሾሬብም : ቶምባኾም : ሡክርም : ብርጭቆም : ሌላም : ልዩ : ልዩ : ስራ : ብዙ : ይሰራሉ :: መፈወሻ : ለውሮች :: መልወጫም :: ለዚች : ከተማም : ፲፻ መርከቦች : አሉ : ገንዘብዋ ::

ደረምሺር :: ደ ረም : የኤጲስቆጶስ : መቀመጫ :: ሰን ድ ር ለ ን ድ : ፲፩፲፻ ሰዎች :: የብረት : መስሪዮች :: የብረት : ድልድልም ::

ኖርተምብርለንድሺር :: ኑ ከ ስ ት ል : ፬፻፻ ሰው : እጅግ : መሸየጥና : ስራ :: የኪሚያ : ማስተማርያ :: የብረትም : የወርቅና : የብርም : መስሪዮች :: ከ፹፫ ጕድጓዶች : የደ ንጊያ : ቀሰል : ይቈፈራሉ : በ፹፻ መርከቦችም : ወትሩ : ይህነን : ቀሰል : ወደ : ሎንደን : ይወስዲታል ::

ከምበርለንድሺር :: ካ ር ለ ደ ል : ፹፬፲፻ ሰው : የኤጲስ ቆጶስ : መቀመጫ :: የጥጥ : የቆርበትም : የሌላ : ስራም : መስሪዮች :: ወ ደ ት ሄ ብ ን : እጅግ : መስሪዮች ::

ወስትመርለንድ :: ማን : ደሴት ::

፩ ክ ን ት :: ክ ን ት ር ብ ሪ : የመጀመርያ : ሜትሮጶሊ ታ ን : መቀመጫ :: ደ በ ር : ብርቱ : አምባ :: መሻገርያ : ወደ : ፈራንስ :: ቸ ተ ም : መርስ :: የእንግሊጣር : መድፈና : የነ ፈጥ : መሰብሰብያ :: ግሪኒ ች : ለሎንደን : ትቀርባለች :: ታላቅ : ሆስጲታል : ለመርከበኞች : የመርከብም : ስራ : ማ ስተማርያ :: የኮከብም : መጠበቅያ : እንግሊዞች : ከርሶ : ጀምረው : የምድርን : ርዝመት : የሚቈጥሩ :: ያለበት : መነጽር : ርዝመቱ : ፹፪ ክንድ : ነው ::

፪ ሶ ስ ክ ሺ ር :: ብ ረ ደ ት ን : ፻፻ ሰው : የንጉሥ : መ ኖርያ ::

፫ ወ ሰ ክ ስ :: በ ር ክ ሺ ር :: ዊ ን ዝ ር : የንጉሥ : ቤትና : አታክልት ::

፪፡ መካከለኛ ፡ ስኮትላንድ ፡ በ፴፡ ክፍል ፡፡
ኑአብርደን ፡ ኡኒዌርሲታስ ፡ ፴፪፻፡ ሰው ፡፡ ብዙ ፡ መስ
ሪዮችም ፡፡
፫፡ የሰሜን ፡ ስኮትላንድና ፡ ላይኛ ፡ ምድር ፡ በ፳፡ ክፍል ፡፡
ለስኮትላንድም ፡ እሌህ ፡ ደሴቶች ፡ አሉ ፡፡ ፩፡ ሁብሪደ
ደች ፡ ፫፻፡ ታናሾች ፡ ደሴቶች ፡፡ ፪፡ ኦርካደች ፡ ፴፳፡፡ ፴፫፻፡
ሰው ፡፡ ፫፡፡ የሼትላንድ ፡ ደሴቶች ፡ ፹፳፡፡ ፴፩፻፡ ሰው ፡፡

## ኢርላንድ ፡፡

፩፡ ሌንስትር ፡ በ፲፪፡ ክፍል ፡፡
ደብሊን ፡ ፲፳፻፻፡ ሰው ፡፡ መርስ ፡፡ የንጉሥ ፡ መስለኔ ፡
መቀመጫ ፡ የሜትሮጶሊታንም ፡፡ ኡኒዌርሲታስም ፡ አያሌ ፡
ሌሎችም ፡ ማስተማርዮች ፡፡ ብዙ ፡ መስሪዮችም ፡፡
፪፡ አልስትር ፡፡ በዚች ፡ ክፍል ፡ የኃያላን ፡ መንገድ ፡ የሚ
ባል ፡ ፫፻፻፡ ታላቆች ፡ አዕማድ ፡ ያሉበት ፡ ይገኛል ፡፡ አልስ
ትርም ፡ በ፱፡ ክፍል ፡ ተከፈለች ፡፡
አርማግ ፡ የሜትሮጶሊታን ፡ መቀመጫ ፡፡
፫፡ ኮናት ፡ በ፭፡ ክፍል ፡፡
ቱአም ፡ የሜትሮጶሊታን ፡ መቀመጫ ፡፡
፬፡ መንስትር ፡ በ፮፡ ክፍል ፡፡
ሊምሪክ ፡ ፵፲፻፡ ሰው ፡ እጅግ ፡ መሻየጥ ፡፡ ኮርክ ፡
፰፻፻፡ ሰው ፡፡ የኤጲስቆጶስ ፡ መቀመጫ ፡፡ ብዙ ፡ መስሪዮ
ችና ፡ እጅግ ፡ መሻየጥ ፡፡

## ከታላቅ ፡ ብርታንያም ፡ በሜደ ፡ ለእንግሊዞች ፡ ያለች ፡ ግዛት ፡፡

## በኤውሮጳ ፡፡

፩፡ የሀኖብር ፡ መንግሥት ፡ የንጉሥ ፡ ገንዘብ ፡፡ የሀ
ኖብር ፡ ሥርዓት ፡ ግን ፡ ሴትን ፡ አታስነግሥምና ፡ ዛሬ ፡ ከእ
ንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ተለየች ፡ የሞተ ፡ ንጉሥም ፡ ወንድ
ም ፡ ይነግሥባታል ፡፡
፪፡ ሀልጎላንድ ፡ ደሴት ፡ በሆልስተይን ፡ ደርቻ ፡ ፪፡ መር
ሶች ፡ ፬፲፻፡ ሰዎች ፡፡

፫፤ ጊብረልታር ፡ በስጳንያ ፡፡
፬፤ ማልታ ፡ ደሴት ፡ በመካከለኛ ፡ ባሕር ፡፡
፭፤ የዮንያን ፡ ደሴቶች ፡ ይጠብቃሉና ፡ ይገዝዋቸዋል ፡፡

## በእስያ ፡፡

፩፤ ከህንድ ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ለእንግሊዞች ፡ ያልተገዛች ፡ ምድር ፡ ጥቂት ፡ ቀረች ፡፡ ፪፤ ስሎን ፡ ቡንውቅም ፡ ደሴቶች ፡ ከሌሎች ፡ ደሴቶችም ፡ ክፍል ፡ ከጵሪንስ ፡ ኦፍዌልስ ፡ ደሴትም ፡ ጋራ ፡፡ ፫፤ ዓደን ፡ በዓረብ ፡ ምድር ፡ በመንድብ ፡ ደጅ ፡፡

## በአፍሪካ ፡፡

የወርቅና ፡ የባሮች ፡ ደርቻ ፡ በሚሉት ፡ ደርቻ ፡ አያሌ ፡ ግዛት ፡፡ የሴራሌዎና ፡ ኮሎኒያም ፡ በምዕራብ ፡፡ የበጎ ፡ ተስፋ ፡ ካጵም ፡ የሚልዋት ፡ ምድር ፡ በደቡብ ፥ ሔሌናም ፡ ኢልድፍሪንስም ፡ ሞሪስም ፡ የሲሸል ፡ ደሴቶችም ፡፡

## በአሜሪካ ፡፡

በሰሜን ፡ አሜሪካ ፡፡ ለብራደር ፡ አደስ ፡ ዌልስም ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ካለው ፡ ከሌላ ፡ ግዛት ፡ ጋራ ፡፡ አደስ ፡ አልብዮንም ፡ ከነደም ፡ ኑፈውንድለንድም ፡ የቅደስ ፡ ዮሐንስም ፡ የአንቲኮስቲም ፡ የመግደላዊትም ፡ ደሴቶች ፡ ካጵ ፡ ብሪቶንም ፡ የበርሙደ ፡ ደሴቶችም ፡፡

በመካከለኛ ፡ አሜሪካም ፡፡ የማይካ ፡ ቅድስት ፡ ሊክያም ፡ በርቢደስም ፡ ሰን ፡ ዊንሰንትም ፡ ደሚኒካም ፡፡ ግሬናደም ፡ ክርስቶፎሮስም ፡ አንቲጒም ፡ ተባጎም ፡ ትሪኒደድም ፡ አያሌ ፡ ሌሎች ፡ ደሴቶችም ፡፡

በደቡብ ፡ አሜሪካም ፡፡ በርቢስ ፡ ዴመራራም ፡ እስኩቦም ፡ በጉያና ፡፡

## በአውስትራሊያ ፡፡

ባደስ ፡ ሆለንድና ፡ ባደስ ፡ ሴለንድ ፡ እጅግ ፡ ምድር ፡ የፈንደመንስለንድ ፡ ደሴትም ፡ ካያሌ ፡ ሌሎች ፡ ደሴቶች ፡ ጋራ ፡፡

ጉሥም ፡ ቢብልዮቴካ ፡ ፲፫፻፻፡ ትራዝን ፡ የሚዝ ፡ ፬፡ የንጉሥ ፡ አምቦች ፡ ፳፭፡ አቢያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡፡ የነጋዶችም ፡ መሰብሰቢያና ፡ መልወጫ ፡፡ ደህና ፡ መርስም ፡፡ መስሪዮችም ፡ ለሡክር ፡ ለቶምባኾም ፡ ለጥጥም ፡ ለተልባግርም ፡ ለጉኽም ፡ ለቀርበትም ፡ ለጨንም ፡ ለሰምም ፡ ለአረቂም ፡ ላሣ ፡ ሱብም ፡ ለሌላ ፡ ስራም ፡፡ እጅግ ፡ መሻየጥም ፡፡ የስያም ፡ ጉባኤ ፡ መቀመጫ ፡፡

ሀልሲንጌር ፡ ፯፲፱፡፡ ሰው ፡፡ መርስ ፡፡ መሻገርያም ፡ ወደ ፡ ሽዊድንና ፡ ኖርዊግን ፡፡

፪፪፡ ፏነን ፡፡ ኦድንሴ ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ መቀመጫ ፡፡ ብዙ ፡ መስሪዮችም ፡፡

፫፫፡ ላላንድ ፡፡

## ፪፡ የዩትላንድ ፡ ጴኒንሡላ ፡፡

፩፩፡ የሰሜን ፡ ዩትላንድ ፡፡

፪፪፡ የደቡብ ፡ ዩትላንድ ፡፡ ሽለስዊግ ፡ ፶፯፲፱፡፡ ሰው ፡ የንጉሥ ፡ መስለኒ ፡ መቀመጫ ፡፡ አያሌ ፡ መስሪዮችም ፡፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጉባኤ ፡፡

## ፫፡ የአይስላንድ ፡ ደሴት ፡፡

ባላገሮች ፡ ፵፯፲፱፡፡ ሰዎች ፡፡ ረይክያዊክ ፡ ከተማ ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ መቀመጫ ፡ የከዋክብትም ፡ መጠበቅያ ፡፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ ጉባኤ ፡፡

## ፬፡ የፈሬር ፡ ደሴቶች ፡፡

የቀረችም ፡ የደንማርክ ፡ ግዛት ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ በኤውሮጳ ፡፡ ሆልስተይን ፡፡ ለወንቡርግም ፡፡ ጲነበርግም ፡፡ አልቶናም ፡፡ በእስያም ፡፡ አያሌ ፡ አገር ፡ በህንድ ፡፡ በአሜሪካም ፡፡ ግሬንላንድ ፡ ፬፡ ደሴቶችም ፡ በመካከለኛ ፡ አሜሪካ ፡፡ በአፍሪካም ፡ ፬፡ አምቦች ፡ በወርቅ ፡ ደርቻ ፡፡

---

## ሽዊድንና ፡ ኖርዊግን ፡፡

ስፍሪ ፡፡ ወሰንም ፡፡ ታላቅነትም ፡፡ የምሥራቅ ፡ ርዝ

የመርከብ ፡ እንጨት ፡ ብረትም ፡ ዝናድም ፡ ቅጥሬንም ፡ ያሢ ፡ ሱብም ፡ ዓሣም ፡፡ የመ፫የጥም ፡ መርከቦች ፡ ፲፫፻ ናቸው ፡፡

ባላገሮች ፡፡ ፫ ሚልዮን ፡ ተኩል ፡ ናቸው ፡፡ የመንግሥት ፡ ማምለክ ፡ የጵሮትስታንቶች ፡ ማምለክ ፡ ነው ፡፡ እውቀትና ፡ ብልሃትም ፡ በዚች ፡ መንግሥት ፡ ይበዛል ፡ ፫ ኡኒቨርሲታቶች ፡ አሉ ፡፡

የመንግሥት ፡ መግዛት ፡፡ የንጉሥ ፡ ፈቃድ ፡ በሕዝቡ ፡ ጉባኤ ፡ ተወሰነች ፡፡ ከንጉሥ ፡ ዘመድም ፡ ወንድች ፡ ቢያልቁ ፡ ደህች ፡ ጉባኤ ፡ ሌላውን ፡ ታነግሢለች ፡፡ የዛሬም ፡ ንጉሥ ፡ ስም ፡ ካርል ፡ ዮሐንስ ፡ ነው ፡፡

የመንግሥት ፡ መክፈል ፡፡

## ፩ ሽዊድን ፡፡

፩፩ አይነተኛ ፡ ሽዊድን ፡ በ፫ ክፍል ፡፡ ኡጵላንድ ፡ ሱድርመንለንድም ፡ ኔሪክም ፡ ወስትርመንለንድም ፡ ደልከርልየንም ፡፡

ስቶክሆልም ፡ በሜላርና ፡ በምሥራቅ ፡ ባሕር ፡ የመንግሥት ፡ ከተማ ፡ የንጉሥም ፡ መኖርያ ፡ ፴፻፻ ሰው ፡፡ ደግ ፡ መርስ ፡፡ ሙሴውምም ፡ አያሌ ፡ አካዴምዮችም ፡ ግምናስዮምም ፡፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስና ፡ የሚስዮንም ፡ ጉባኤ ፡፡ ፮ ሆስጲታሎችም ፡ አያሌም ፡ ሌሎች ፡ የፍቅር ፡ ቤቶች ፡ የመንግሥትም ፡ መልወጫ ፡፡ አያሌ ፡ መስሪዮችም ፡ እጅግ ፡ መሸመትም ፡፡

ኡጵሳላ ፡፡ ፬፲፻ ሰው ፡፡ የሚትሮጶሊታንም ፡ መቀመጫ ፡ ኡኒቨርሲታስም ፡፡ የትምርትም ፡ አታክልት ፡፡ የከዋክብትም ፡ መጠበቅያ ፡ ሙሴውምም ፡ የሰባኮችም ፡ ሴሚናርዩም ፡፡

ወስትረስ ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ መቀመጫ ፡፡

፮፮ ጎትለንድ ፡፡

ጎትንቡርግ ፡ በጎታኤልፍ ፡ ፮፻፻ ሰው ፡፡ አምባ ፡፡ መርስም ፡ የነፍጥና ፡ የመድፍ ፡ መስሪያም ፡ የነጋዴችም ፡ መሰብሰብያ ፡፡

ሉንድ ፡ ፫፲፻፤ ሰው ፡ ኡኒዌርሲታስ ፡፡ የሰባኮችም ፡ ሲማ ናር ፡፡ የከዋክብትም ፡ መጠበቅያ ፡፡ የትምህርትም ፡ አ ታክልት ፡፡

ክልመር ፡ አምባ ፡፡ የኤጲስቆጶስ ፡ መቀመጫ ፡ አያሌ ፡ መስሪዮች ፡፡

ሊንክጺንግ ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ መቀመጫ ፡፡

፫፫፤ ኖርላንድ ፡፡

ግፊል ፡፡ ሆርኖሰንድ ፡፡ የኤጲስቆጶስ ፡ መቀመጫ ፡፡ አ ያሌ ፡ መሻዮጥም ፡፡

፬፬፤ ለጵላንድ ፡ ፻፻፤ ሰው ፡፡

## ፬፤ ኖርዌግን ፡፡

ክርስቲያንያ ፡ የኖርዌግን ፡ ከተማ ፡ ፻፻፤ ሰዎች ፡፡ የንጉ ሥ ፡ የመስለንዩ ፡ መኖርያ ፡፡ ኡኒዌርሲታስ ፡፡ የከዋክብት ፡ መጠበቅያ ፡ የትምህርትም ፡ አታክልት ፡፡ ፯፻፻፤ ትራዝ ን ፡ የሚዝ ፡ ቢብልዮቴካ ፡፡ የበጎ ፡ ስራም ፡ ጉባኤ ፡፡ የሚ ስዮንና ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጉባኤም ፡፡ ብዙ ፡ መስሪዮ ችም ፡፡

ክርስቲያንስፈልድ ፡ ፳፲፻፤ ሰው ፡፡ የወንጌል ፡ ወንድ ሞች ፡ ኮሎኒያ ፡፡

በርግን ፡ ፲፰፲፻፤ ሰው ፡ እጅግ ፡ መሻዮጥ ፡፡

ድሮንትሀይም ፡ ፱፲፻፤ ሰው ፡፡ የኤጲስቆጶስ ፡ መቀመ ጫ ፡፡ ብዙ ፡ መስሪዮትም ፡፡

ኖርድላንድ ፡ ለጶች ፡ የሚባሉ ፡ ሰዎች ፡ ፯፲፻፤

አልስተርሆንግ ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ መቀመጫ ፡፡

---

## የኤውሮጳ ፡ ሩስያ ፡ ወይስ ፡ ሞስኮብ ፡፡

ስፍራ ፡፡ ወሰንም ፡፡ ታላቅነትም ፡፡ ወርድዋ ፡ ፴፰°፤ — ፸፰°፡፡ ርዝመትዋም ፡ ፳፩°፤ — ፸፩°፤ ነው ፡፡ ወሰንዋም ፡ በሰ ን ፡ የውርጭ ፡ ባሕር ፡፡ በምሥራቅም ፡ የእስያ ፡ ሩስያ ፡፡ በደ ቡብም ፡ ጥቁር ፡ ባሕር ፡ የቱርክ ፡ መንግሥትም ፡ ገሊትያ ም ፡፡ በምዕራብም ፡ ሲሌስያ ፡ ጵሩስያም ፡ ሽዌድንና ፡ ኖር

ዊግንም ፡ የምሥራቅ ፡ ባሕርም ፡፡ ጶሎንያም ፡ ሳትቈጠር ፡ የኤውሮጳ ፡ ሩስያ ፡ ታላቅነት ፡ ፩፡ ሚልዮን ፡ ሚላ ፡ ነው ፡፡ መንግሥቱም ፡ ሁሉ ፡ በኤውሮጳ ፡ በስያም ፡ ባሜሪካም ፡ ያለት ፡ ግዛት ፡ ሁሉ ፡ ቢቈጠር ፡ ፱፡ ሚልዮን ፡ ፱፻፲፻፡፡ ሚላ ፡ ታህላለች ፡ የምድር ፡ ሁሉ ፡ ዘጠኘኛ ፡ ክፍል ፡፡

የምድር ፡ ጠባይዕ ፡፡ ክሊማ ፡ ጤና ፡ ነው ፡ በ፵፰°፤—፶°፤ ከወርድዋ ፡ ይተኰሳል ፡፡ ምድርም ፡ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ ታፈራለች ፡፡ በ፶፩°፤—፷°፤ ክሊማ ፡ መኻከለኛ ፡ ነው ፡ ምድርም ፡ ታፈራለችና ፡ ተሰራች ፡፡ ከ፷°፤ ወዲያ ፡ ግን ፡ መብቈል ፡ አለቀ ፡ ሰዎችም ፡ ሬንዲርንና ፡ ዓሣውን ፡ ብቻ ፡ ይበላሉ ፡፡ በሰሜን ፡ ደርቻም ፡ መብረቅና ፡ ነጐድጓድ ፡ ጥቂት ፡ ነው ፡፡ የሰሜን ፡ ብርሃን ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይበራል ፡፡ የደቡብና ፡ መኻከለኛ ፡ ሩስያ ፡ ሜዳ ፡ ናት ፡፡ የሰሜን ፡ ክፍልዋ ፡ ግን ፡ ደጋ ፡ ነው ፡፡ ታላቆች ፡ ተራሮች ፡፡ ኡራል ፡ ርዝመቱ ፡ ከ፲፻፤ ሚላ ፡ የሚበልጥ ፡ በኤውሮጳና ፡ በእስያ ፡ መኻከል ፡፡ ከውከሱስም ፡ አለኑስም ፡ በሩስያ ፡ ለጽለንድም ፡ ያሉ ፡ ተራሮች ፡ ስኮቶይፍስ ፡ ከተባለ ፡ ካጽ ፡ ጋራ ፡፡ ውኆችም ፡፡ በምዕራብ ፡ የፊንያና ፡ የሊፍላንድ ፡ ጉበቶች ፡፡ በሰሜንም ፡ ነጭ ፡ ባሕር ፡፡ በደቡብም ፡ የኣሶውና ፡ ጥቁር ፡ ባሕር ፡፡ የምድር ፡ ባሕሮች ፡፡ የከስጵያ ፡ ባሕር ፡ የለደጋ ፡ ባሕርም ፡ የኦኔጋ ፡ ባሕርም ፡ የኢልመን ፡ ባሕርም ፡ የጳይጶስ ፡ ባሕርም ፡ የጵዩና ፡ ባሕርም ፡ የኡልኣ ፡ ባሕርም ፡፡ ታላቆች ፡ ወንዞችመ ፡ ፲፮፤ ከርሳቸውም ፡ ፰፤ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ይሔደሉ ፡ እርሳቸውም ፡ ኒመን ፡ ኔዋም ፡ ዲናም ፡ ቶርንያም ፡ ነርዋም ፡ አሌህ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ባሕር ፡ ይገባሉ ፡፡ ኦኔጋም ፡ ድዊናም ፡ ጰትሾራም ፡ ወደ ፡ ውርጭ ፡ ባሕር ፡ ይገባሉ ፡፡ ፬ም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ይሔደሉ ፡ እርሳቸውም ፡ ድኒጵር ፡ ደንም ፡ ደኑብም ፡ ወደ ፡ ጥቁር ፡ ባሕር ፡ ይደርሳሉ ፡ ዎልጋም ፡ ወደ ፡ ከስጵያ ፡ ባሕር ፡ ትገባለች ፡፡ አያሌ ፡ መስኖችም ፡ አሉ ፡፡

ምድር ፡ የምታወጣ ፡፡ እህል ፡ የዛፍ ፡ ፍሬም ፡ ዘይትም ፡ በለስም ፡ ለውዝም ፡ መናም ፡ ቶምባኾም ፡ ወይንም ፡ የጸጕር ፡ ለምድም ፡ ንብም ፡ ላምም ፡ በግም ፡ ፈረስም ፡ አራዊትም ፡ ገመልም ፡ ዓሣም ፡፡ ነሃስም ፡ ብረትም ፡ ወርቅም ፡

ብርም ፡ ኣልማዝም ፡ መርሞርም ፡ ጭውም ፡ ሌሎች ፡ ማ
ነሪሎችም ፡፡

የ፮ ፡ ስራ ፡፡ ባላገሮች ፡ በያመት ፡ በያመትም ፡ ይማሪ
ሉ ፡ ስራቸው ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ፈጻሜ ፡ አልደርሰም ፡ እንደ ፡ ሌ
ሎች ፡ ፈርንጆች ፡ ስራ ፡፡ እጅግ ፡ የሚሰረት ፡ ስራ ፡ ይህ ፡ ነ
ው ፡፡ የቀርበት ፡ ስራ ፡ ሐረጻም ፡ የመርከብም ፡ ሸማ ፡ ቁማ
ሸም ፡ የተቀረጠ ፡ እንጨትም ፡ ጶታሳም ፡ ቅጥራንም ፡ ዝ
ፈትም ፡ ጭውም ፡ ብርጭቆም ፡ ሳምናም ፡ ያሣ ፡ ሰብም ፡
ጥዋፍም ፡ ኒትሩምም ፡ ባሩድም ፡ ሡክርም ፡ የደን ፡ መጸ
ጻም ፡ አረቂም ፡ የሚታሉች ፡ እቃም ፡ ነፈጥም ፡ ታጼቶች
ም ፡ ዘርፈም ፡ ቶምባኮም ፡ ጨንም ፡፡ የጥጥ ፡ ሸማም ፡ ጉ
ኝም ፡ ሀርም ፡ የሸልምም ፡ ስራ ፡፡ መሻየጥም ፡ እጅግ ፡
#### *a.* የጎታ ፡ ግዛት ፡፡

ጎታ ፡ ያመረች ፡ ከተማ ፡ ፲፪፲፻። ሰዎች ፡፡ ፍሪደንስተይ ን ፡ የዱክ ፡ ቤት ፡፡ ደህና ፡ ቢብልዮቴካ ፡ ብዙም ፡ የመቅ ረጽ ፡ የብልሃትም ፡ የናቱሪልያም ፡ መሰብሰቢዮች ፡፡ የመ

ምህራ.ንም ፡ ሲማናር ፡፡ ብዙ ፡ ማስተማርዮችና ፡ መስ ራ.ዮችም ፡፡

## ፬. የአልትንቡርግ ፡ ግዛት ፡፡

አልትንቡርግ ፡፡ ፱፲፻፡ ሰዎች ፡፡ ብዙ ፡ ማስተማርዮች ና ፡ መስራ.ዮች ፡፡

፫፫፡ የመይኒንግን ፡ ዱክያ ፡፡ ፫፻፡ ሚላ ፡ ፪፸፲፻፡ ሰዎች ፡፡

መይኒንግን ፡ ከተማ ፡ የዱክም ፡ መኖርያ ፡ ፱፰፻፡ ሰዎ ች ፡፡ የዱክ ፡ ቤትም ፡ እጅግ ፡ ያመራ.ል ፡፡ የመምህራ.ን ም ፡ ሲማናር ፡፡

ሶንንበርግ ፡ ፲፱፻፡ ሰዎች ፡ እጅግ ፡ መሻየጥ ፡ በቅርበ ት ፡ በሙሲካም ፡ በጨወታ ፡ እቃም ፡፡

### ፱፱፡ የሂልድቡርግሀውስን ፡ ዱክያ ፡፡

፰፲፯፡ ሚላ ፡፡ ፴፰፲፻፡ ሰዎች ፡፡

ሂልድቡርግሀውስን ፡ ከተማ ፡ ፳፫፻፡ ሰዎች ፡፡ የበግ ፡ ጸጕር ፡ መስራ.ዮች ፡፡

### ፫፫፡ የኮቡርግ ፡ ዱክያ ፡፡ ፺፲፻፡ ሰዎች ፡፡

ኮቡርግ ፡ ፳፲፻፡ ሰዎች ፡፡ የዱክ ፡ መኖርያ ፡፡ የመምህ ራን ፡ ሲማናር ፡፡

ሳልፈልድ ፡ ፫፪፻፡ ሰዎች ፡፡ የሚታሎች ፡ ጕድጓዶች ፡፡

ቴማር ፡ ፲፬፻፡ ሰዎች ፡ የክርታስ ፡ ወፍጮች ፡፡

በውምሆልድር ፡ በረደን፡ ግሬ ፡ ደርቻ ፡ ፪፻፡ ሰዎች ፡፡ የብረት ፡ መስሬ.ዮች ፡፡

---

## 5. የሬውስ ፡ ገዦች ፡ ግዛት ፡፡

፯፻፡ ሚላ ፡፡ ፹፫፲፻፡ ሰዎች ፡፡

ግረይጽ ፡ ፯፲፻፡ ሰዎች ፡ አያሌ ፡ ማስተማርዮች ፡፡ ፰፡ ሴ ማናሮችም ፡፡ አንዲት ፡ ለቀሳወስት ፡ አንዲትም ፡ ለሕዝ ብ ፡ መምህራን ፡፡ አያሌ ፡ መስሬ.ዮችም ፡፡

ሾለደጵ ፡ ፺፲፻፡ ሰዎች ። ኤብርስደርፍ ፡ ፲፩፻፡ ሰዎች ።
የወንጌል ፡ ወንድሞች ፡ ጉባኤ ።

---

6. የሾዋርጽቡርግ ፡ ገዦች ፡ ግዛት ።

፲፩፷፯፡ ማላ ፡ ፲፻፻፡ ሰዎች ።

ሶንድርስሀውስን ፡ ፫፱፻፡ ሰዎች ። ግርውሰን ፡ ፱፲፻፡ ሰዎች ። የበግ ፡ ጸጕርና ፡ የተልባግር ፡ መስሪዮች ።

ሩደልስታት ፡ ፷፲፻፡ ሰዎች ። አያሌ ፡ ማስተማርዮችም ፡ የበግ ፡ ጸጕርና ፡ የጪና ፡ ስሪም ፡ መስሪዮች ።

ሾዋርጽቡርግ ፡ የ፪ ገዦች ፡ የድሮ ፡ አባቶቻቸው ፡ መወለጃ ።

---

7. የአንሀልት ፡ ዱክዮች ። ፻፷፫፲፻፡ ሰዎች ።

፩፩፡ የደሰው ፡ ዱክያ ።

ደሰው ፡ ያመረች ፡ ከተማ ፡ ፻፻፡ ሰዎች ፡ ከርሳቸውም ፡ ፺፻፡ አይሁድ ። ብዙ ፡ ማስተማርዮች ። የድኆችና ፡ የሰራተኞች ፡ ታላቅ ፡ ቤት ። ብዙ ፡ መስሪዮች ።

ጸርብስት ፡ ፺፲፻፡ ሰዎች ። ግምናስዩም ። የሴቶች ፡ ማስተማርያ ። የበግ ፡ ጸጕርም ፡ የቶምበኾም ፡ የጪናም ፡ የወርቅና ፡ የብርም ፡ መስሪዮች ።

፪፪፡ የበርንቡርግ ፡ ዱክያ ።

በርንቡርግ ፡ ከተማ ፡ ፸፺፻፡ ሰዎች ። ቤት ፡ ለኦርፋኖች ፡ ለድውያንም ፡ ለሰራተኞችም ። አያሌ ፡ መስሪዮችም ።

፫፫፡ የኬትን ፡ ዱክያ ።

ኬትን ፡ ያመረች ፡ ከተማ ፡ ፷፺፻፡ ሰዎች ። ቢብልዮቴካም ። የሥልንና ፡ የናቱራልያ ፡ መሰብሰቢያ ። የሴቶችም ፡ ማሳደግያ ። የመምህራንም ፡ ሲሚናር ። የጥጥ ፡ የወርቅም ፡ የብርም ፡ ዘርፍ ፡ መስሪዮች ።

---

፫፫ የሂልድስሀይም : ግዛት ::

ሂልድስሀይም :: ፲፩፲፪ ሰዎች :: ደግ : ቤተ : ክርስቲያን :: ፪ ግምናስዮችም :: የቀኀወስትም : ሴሚናር :: ግዛትም : የስራ : ቤትም :: ፪ ሆስጲታሎችም :: አያሌ : መስሪዮችና : መኽየጥም :: ጎስለር : ፯፲፪ ሰዎች :: ብዙ : መስሪዮች ::

፬፬ የሉንቡርግ : ግዛት ::

ሉንቡርግ : ፲፩፲፪ ሰዎች : ብዙ : መስሪዮች :: የጭው : ማፊያ ::

፭፭ የብሬምንና : የወርድን : የሃድልንም : ግዛት ::

ስታዴ : ፭፲፪ ሰዎች :: ብዙ : መስሪዮች :: አያል : መኽየጥም :

፮፮ የሆጋና : የዲጵሆልጵ : ግዛት ::

፯፯ የኦስነብሪክ : ግዛት ::

ኦስነብሪክ : ፱፲፪ ሰዎች : የኤጲስቆጶስ : መቀመጫ :: የመጽሐፍ : ቅዱስ : ጉባኤ :: አያሌ : መስሪዮችም ::

፰፰ የምሥራቅ : ፍሪስላንድ : ግዛት ::

፱፱ የበንትሀይምና : የአርምበርግ : ግዛት ::

---

10. የሀስን : ኤለክቶሬት :: ፬፻፶፯ ሚላ :: ፭፹፭፲፪ ሰዎች ::

ጋዢዋ : ኤለክቶር : ይባላል :: እርሱም : ከመንግሥቱ : ጉባኤ : ጋራ : ይገዛል :: ይህች : ምድርም : በ፬ ክፍል : ተከፈለች ::

ክስል : ያመረች : ከተማ : የኤለክቶርም : መኖርያ :: ፲፰፲፪ ሰዎች :: ዊልሀልምስሄህ :: የመጽሐፍ : ቅዱስና : የሚስዮን : ጉባኤ ::

መርቡርግ : ፯፬፻ ሰዎች :: ኡኒዌርሲታስ :: ብዙ : ሌሎ

ችም ፡ ማስተማርዮች ፡፡ ፫፲፻፡፡ ትሪዝንም ፡ የሚዝ ፡ ቢብ
ልዮቲካ ፡፡ ብዙ ፡ መስሪዮችም ፡፡

ፉልደ ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ መቀመጫ ፡፡ ፯፲፻፡፡ ሰዎች ፡፡ የቦ
ኒፋክዩስ ፡ መቃበር ፡፡

ሃነው ፡፡ ፲፪፲፻፡፡ ሰዎች ፡፡ እጅግ ፡ መኻየጥ ፡፡

ሽመልካልድን ፡፡ ፩፳፻፡፡ ሰዎች ፡፡ ብዙ ፡ መስሪዮች ፡፡
ከዚህ ፡ የሽማልካልድን ፡ መሐላ ፡ ተማለ ፡ በጵሮትስታን
ቶች ፡ ገዦች ፡ መኻከል ፡፡

---

11\. የወልደክ ፡ ግዛት ፡፡ ፩፶፰፡ ሚላ ፡፡ ፶፪፲፻፡፡ ሰዎች ፡፡

አሮልስን ፡ ታናሽ ፡ ያመረችም ፡ ከተማ ፡፡ ፲፪፻፡፡ ሰዎች ፡፡
የግዢ ፡ መኖርያ ፡፡ የበግ ፡ ጸጕርም ፡ መስሪዮች ፡፡

ኮርበኽ ፡፡ ፲፯፻፡፡ ሰዎች ፡ ግምናስዩም ፡፡ የበግ ፡ ጸጕር ፡
መስሪዮች ፡፡

ጲርሞንት ፡ ፪፲፻፡፡ ሰዎች ፡ የገዢ ፡ አምባ ፡፡ የከበረ ፡ የ
ጤና ፡ ምንጭ ፡፡

---

12\. የሊጳ ፡ ግዛት ፡፡ ፯፩፲፻፡፡ ሰዎች ፡፡

በ፪፡ ተከፈለች ፡ ከ፪፡ ገዦችም ፡ በታች ፡ ናት ፡፡

፩፩፡ የሊጳ ፡ ደትሞልድ ፡ ግዛት ፡፡

ደትሞልድ ፡ ከተማ ፡ ፪፲፻፡፡ ሰዎች ፡ ግምናስዩም ፡፡ የ
መምህሪንም ፡ ሴሚናር ፡፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ ጉባኤ ፡
የድኆች ፡ ቤቶችም ፡ የስሪ ፡ ደህና ፡ ማስተማርያም ፡፡

ለምጎ ፡ ፫፩፻፡፡ ሰዎች ፡፡ ሊጽስታት ፡ ፯፲፻፡፡ ሰዎች ፡፡

፪፪፡፡ የሊጳ ፡ ሽውምቡርግ ፡ ግዛት ፡፡

ቢክቡርግ ፡ ፳፩፻፡፡ ሰዎች ፡፡ ግምናስዩም ፡ የኦርፈኖች ፡
ቤትም ፡ የተልባግርም ፡ መስሪዮች ፡፡

---

ንምሳ ፡፡ ኦልድንቡርግ ፡፡ የደንማርክ ፡ ግዛት ፡፡ 

13. የኦልድንቡርግ ፡ ግረንዱክያ ፡፡ ፪፯፳፡፡ ሚላ ፡
፵፪፻፻፡፡ ሰዎች ፡፡

፩፩፡፡ የኦልድንቡርግ ፡ ዱክያ ፡፡

ኦልድንቡርግ ፡ ከተማ ፡ ፫፫፻፡፡ ሰዎች ፡፡ አያሌ ፡ ማስተማርያዎች ፡ መስሪያዎችም ፡፡ መሸየጥም ፡፡

፪፪፡፡ የኤውቲን ፡ ግዛት ፡፡

ኤውቲን ፡ ፪፬፻፡፡ ሰዎች ፡፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጉባኤ ፡፡ እጅግ ፡ መሸመት ፡፡

፫፫፡፡ የቢርክንፈልድ ፡ ግዛት ፡ በረይን ፡ ግራ ፡ ደርቻ ፡፡

ቢርክንፈልድ ፡ ፲፬፻፡፡ ሰዎች ፡፡ የብረት ፡ መስሪያዎች ፡፡ ታላቅ ፡ ገቢያ ፡ ለንስሶች ፡፡

ኦበርስተይንና ፡ ኢደር ፡ የከበረውን ፡ ደንጊያ ፡ ከዚህ ፡ ይሰራሉ ፡፡

---

14. የደንማርክ ፡ ግዛት ፡ በንምሳ ፡፡

ደህች ፡ ግዛት ፡ በሁለት ፡ ክፍል ፡ ናት ፡፡ ሆልስተይንና ፡ ለወንቡርግ ፡፡

፩፩፡፡ የሆልስተይን ፡ ዱክያ ፡፡ ፫፪፱፡፡ ሚላ ፡፡
፻፯፻፻፡፡ ሰዎች ፡፡

ግሊክስታት ፡ በአልብ ፡ ብርቱ ፡ ከተማ ፡ ፫፪፻፡፡ ሰዎች ፡፡ ግምናስዩም ፡፡ ብዙ ፡ መስሪያዎችም ፡፡

ወንድስበክ ፡ ፴፻፡፡ ሰዎች ፡፡

ኪል ፡ ፳፲፻፡፡ ሰዎች ፡፡ ኡኒቬርሲታስ ፡፡ ፳፻፻፡ ትሪዝም ፡ ያለው ፡ ቢብልዮቴካ ፡፡ የከዋክብትም ፡ መጠበቅያ ፡፡ የናቱራልያም ፡ መሰብሰቢያ ፡፡ የድደችም ፡ መፈወሻና ፡ ማስተማርያ ፡፡ የመምህራንም ፡ ማስተማርያ ፡፡ አያሌ ፡ ቤቶችም ፡ ለነደያንና ፡ ለድውያን ፡፡ ብዙ ፡ መስሪያዎችም ፡፡ እጅግ ፡ መሸየጥም ፡፡ ደህና ፡ መርስም ፡፡

አልቶና ፡ ፫፫፲፻፡፡ ሰዎች ፡፡ ግምናስዩም ፡፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጉባኤ ፡፡ ብዙ ፡ መስሪያዎችም ፡፡ እጅግ ፡ መሸየጥ

ም ፡፡ ፫፡ መርከቦች ፡ አሉ ፡ ያልቶና ፡ ገንዘብ ፡ የሚሻየጡ ባቸው ፡፡

ክርስቲያንስፈልድ ፡ የወንጌል ፡ ወንድሞች ፡ ኮሎኒያ ፡፡

## ፪፪፡፡ የለወንቡርግ ፡ ዱክያ ፡፡

ለወንቡርግ ፡ በአልብ ፡ ፴፪፻፡፡ ሰዎች ፡፡ መርከቦች ፡፡ አያሌ ፡ መሻየጥ ፡፡

ረጽቡርግ ፡፡ በደሴት ፡ በባሕር ፡ የምትኖር ፡፡ ፪፲፻፡፡ ሰዎች ፡፡ እጅግ ፡ መሻየጥ ፡፡

---

## 15. የመክልንቡርግ ፡ ስትሬሊጽ ፡ ግረንዱክያ ፡፡

፱፻፡፡ ሚላ ፡ ታህላለች ፡፡ ፸፪፲፻፡፡ ሰዎች ፡ ይኖሩባታል ፡፡

---

## 16. የመክልንቡርግ ፡ ሽዌሪን ፡ ግረንዱክያ ፡፡

፬፸፴፡፡ ሚላ ፡ ፴፰፻፻፡፡ ሰዎች ፡፡ ግረንዱክም ፡ ከመንግሥቱ ፡ ጉባኤ ፡ ጋራ ፡ ይገዛል ፡፡

ሽዌሪን ፡ ከተማ ፡ የግረንዱክም ፡ መኖርያ ፡ ፻፻፡፡ ሰዎች ፡፡ ግምናስዩም ፡፡ ሉድዊግስሉስት ፡ ያመረ ፡ ስፍራ ፡፡

ሮስቶክ ፡ ፲፫፲፻፡፡ ሰዎች ፡፡ ኡኒዌርሲታስ ፡፡ እጅግ ፡ መሻየጥ ፡፡

---

## 17. ለራሳቸው ፡ የተገዙ ፡ ከተሞች ፡፡

እርሳቸውም ፡ ሀምቡርግ ፡ ሊበክም ፡ ብሬምንም ፡፡

## ፩፩፡፡ ሀምቡርግ ፡ በግዛትዋ ፡ ጋራ ፡፡

ሀምቡርግ ፡ ለመሻየጥ ፡ መጀመርያ ፡ ከተማ ፡ በንምሳ ፡ እጅግ ፡ ባለጠጋ ፡፡ ፲፫፻፻፡፡ ሰዎች ፡፡ ፲፩፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡፡ የቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ግምብ ፡ ከፍታው ፡ ፬፶፯፡ እግር ፡ ነው ፡፡ አያሌ ፡ ቢብልዮቴኮችም ፡ ብዙ ፡ ማስተማርዮችም ፡፡ የሚሸዮን ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ የታናሾች ፡ መጻሕፍትም ፡ የብዙ ፡ ሌላም ፡ የበጎ ፡ ስራ ፡ ጉባኤዮችም ፡፡ የ

ሚስዮንም ፡ ማስተማርያ ፡፡ ብዙ ፡ መስሪያዎችም ፡ ለሚሰሬ ፡ ስሬ ፡ ሁሉ ፡፡ ታላቅ ፡ መሰብሰቢያም ፡ ለነጋዶች ፡ አያሌ ፡ መልወጫችም ፡፡

ለሀምቡርግ ፡ ግዛትም ፡ እሌህ ፡ ቦዖች ፡ ይገባሉ ፡፡ ኮክስሃፈን ፡ ሪጽቢትልም ፡ ኔወርክም ፡ በርገዶርፈም ፡፡

## ፸፯፡ ሊበክ ፡ ከግዛትዋ ፡ ጋሬ ፡ ፵፬፻፲፪፡ ሰዎች ፡፡

ሊበክ ፡ ፴፫፻፲፪፡ ሰዎች ፡፡ ለቅድስት ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማለፊያ ፡ ሰዓት ፡ አላት ፡ በዥግ ፡ ብልሃት ፡ ተሰርታ ፡ የከዋክብትን ፡ መንገድ ፡ የምታሳይ ፡፡ የከተማ ፡ ቤት ፡ ከቢብልዮቴካዋ ፡ ጋሬ ፡፡ የነጋዶችም ፡ መሰብሰቢያ ፡፡ አያሌ ፡ ቤቶችም ፡ ለድኆችና ፡ ለሰሬተኞች ፡፡ የኦርፈኖች ፡ ቤትም ፡፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ ጉባኤ ፡፡ ደህና ፡ ግምናስዩምም ፡፡ ብዙ ፡ መስሪያዎችም ፡ እዥግ ፡ መሻየጥም ፡፡

ትራብሚንድ ፡ መርስ ፡፡ ታላቅ ፡ ፈሮስ ፡፡

## ፸፰፡ ብሬምን ፡ ከግዛትዋ ፡ ጋሬ ፡፡

ብሬምን ፡ በዌስር ፡ ወንዝ ፡ ለሰሜን ፡ ባሕር ፡ ቅርብ ፡ ናት ፡፡ ፲፻፻፡ ሰዎች ፡፡ ፲፰፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስና ፡ የሚስዮን ፡ ጉባኤ ፡፡ ፪፡ ግምናስዮች ፡ ብዙም ፡ ሌሎች ፡ ማስተማርዮች ፡፡ ሆስጲታልም ፡፡ የፈሲቄ ፡ ጉባኤ ፡፡ አያሌ ፡ ቢብልዮቴኮችም ፡፡ የከዋክብትም ፡ መጠበቅያ ፡፡ የቀሳወስትም ፡ ሴሚናር ፡፡ ደህና ፡ ቤቶችም ፡ ለድኆች ፡ ብዙ ፡ መስሪያዎችም ፡ እዥግ ፡ መሻየጥም ፡፡

---

የኤውሮጳ ፡ ጌዎግራፊያ ፡ መጨረሻ ፡፡

# እስያ ::

## ስለ ፡ እስያ ፡ እንዲያው ::

ስፍራ :: ወሰንም :: ታላቅነትም :: እስያ ፡ በታላቅነት ዋ ፡ ከሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ በጠባይዋና ፡ በታሪክዋም ፡ ከሁሉ ፡ የከበረ ፡ የምድር ፡ ክፍል ፡ ናት :: ርት ፡ ከምሥራቅ ፡ ርት ፡ ከ፷፬° ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ርት ፡ እስከ ፡ ፪፻° ድረስ ፡ ነው :: ወርድዋም ፡ ከደ ፡ ወድ ፡ ከ፩° ይጀምራል ፡ ወደ ፡ ሰ ፡ ወደ ፡ ፸፰° ይሔዳል :: በሰሜንም ፡ በሰ ፡ ውርጭ ፡ ባሕር ፡ በምሥራቅም ፡ በምቅ ፡ ዉቅያኖስ ፡ በምዕራብም ፡ በኡራልና ፡ በደን ፡ አድርጋ ፡ በኤውሮጳ ፡ በመካከለኛ ፡ ባሕርም ፡ በክፍሎቹም ፡ በስዌጽ ፡ ኢስትሞስም ፡ በአፍሪካና ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ በደቡብም ፡ በደ ፡ ዉቄያኖስ ፡ ተወሰነች :: ርዝመትዋም ፡ ፯፰፻፫ ወርድዋም ፡ ፭፻፶ ሚላ ፡ ነው ::

የምድር ፡ ጠባይ :: በሰሜን ፡ እስያ ፡ አየር ፡ ብርድና ፡ እጅግ ፡ ብርቱ ፡ ነው ፡ ክረምትም ፡ ረዥሞ ፡ በጋ ፡ ያዕራልና ፡ ይተኰሳል ፡ ምድርም ፡ ከዚያ ፡ በደቡብ ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ መታረስና ፡ መዘራት ፡ ትችላለች :: ቡብዙ ፡ ስፍራም ፡ በረካ ፡ ናት :: መካከለኛ ፡ እስያም ፡ እጅግ ፡ ደጋ ፡ ናት :: ጎቢ ፡ የምትባልም ፡ ታላቅ ፡ ያሸዋ ፡ ምድረ ፡ በደ ፡ ትገኝባታለች :: በታላቆች ፡ ተራሮችም ፡ ላይ ፡ ክሊማ ፡ ብርድ ፡ ነው :: ወደ ፡ ደና ፡ ወደ ፡ ምቅ ፡ ብቻ ፡ ተራሮች ፡ ዝቅ ፡ ወደሉ ፡ ምድር ፡ ታፈራለችና ፡ ተሰራች :: በደቡብ ፡ እስያ ፡ ግን ፡ አየር ፡ ወደሚተኰስ ፡ ደርቅ ፡ ወራት ፡ ከዝናም ፡ ወራት ፡ ጋራ ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ ሚለዋወጡ ፡ ምድር ፡ በከበረ ፡ ፍሬ ፡ ሁሉ ፡ ሀብታም ፡ ናት :: ከዚያም ፡ ሰው ፡ ይበዛል :: ተራሮች :: በሰሜን ፡ እስያ :: ወደ ፡ ምብ ፡ የኡራልና ፡ የወርኾቱር ፡ ተራሮች :: ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ አልታይ ፡ ይገጠማል :: ወደ ፡ አዜብም ፡ የያንስክ ፡ ተራሮት ፡ ወደ ፡ ልባም ፡ የኦኾጽክና ፡ የከምቸትካ ፡ ተራሮች ፡ አሉ :: በመካከለኛ ፡ እስያም ፡ የእስያ ፡ ተራሮች ፡ ሁሉ ፡ መካከልና ፡ መሰብሰቢያ ፡ አለ ፡ እርሱም ፡ የቦግደዉላ ፡ ተራሮች ፡ ይባላል ::

ከርሳቸውም ፡ ወደ ፡ ምቅ ፡ ታላቅ ፡ አልታይና ፡ ነጭ ፡ ተራሮች ፡ አሉ ፡ ወደ ፡ ምብ ፡ የሂመላያ ፡ ተራሮች ፡፡ ከካስጵያ ፡ ባሕርም ፡ ወደ ፡ ምብ ፡ ከውክሶስ ፡ አራራትም ፡ ሉካንም ፡ ተውሮስም ፡ አሉ ፡፡ በደቡብ ፡ እስያም ፡ የብሉርና ፡ የጋትስ ፡ ተራሮች ፡ አሉ ፡ ሊባኖስም ፡ ሌሎችም ፡፡ ካጶች ፡፡ ኮሞሪንና ፡ ሮማኝ ፡ በደቡብ ፡፡ የውርጭ ፡ ካጵም ፡ የቹኮትኮይኖስ ፡ ካጵም ፡ በሰሜን ፡፡ ባሕሮችና ፡ ታላቆች ፡ ወንዞች ፡፡ በሰ ፡ የውርጭ ፡ ባሕር ፡ ከካሮስ ፡ ከኦብም ፡ ከትይሙርግም ፡ ከኽተንግም ፡ ከቻምክም ፡ ጉብቶች ፡ ጋራ ፡፡ ወደርሱም ፡ የኦቢ ፡ የየኒሰይም ፡ የሌናም ፡ ወንዞች ፡ ይገባሉ ፡፡ የከምቸትካ ፡ ባሕርም ፡ የአነዲር ፡ ወንዝ ፡ ወደ ሚገባበት ፡፡ በምሥራቅም ፡ የቱንጉስያ ፡ ወይስ ፡ የኦኾጽክ ፡ ባሕር ፡ የኣሙርን ፡ ወንዝ ፡ የሚቀበል ፡፡ የያጳን ፡ ባሕርም ፡ የጨን ፡ ባሕርም ፡፡ በደቡብም ፡፡ የበንጋል ፡ ጉብት ፡ ገንጅስንና ፡ ቡረምጹትርን ፡ የሚቀበል ፡፡ የፋርስ ፡ ጉበትም ፡፡ በምዕራብም ፡፡ የአሮው ፡ ባሕር ፡ ኩበንን ፡ የሚቀበል ፡፡ የከስጲያ ፡ ባሕርም ፡፡ ወደርሱም ፡ ዎልጋ ፡ ኡራልም፡ ቴረክም ፡ ይገባሉ ፡፡ የባሕር ፡ ጸባቦች ፡፡ በሰ ፡፡ የወይገጵ ፡ መንገድ ፡ በሰሞዬደች ፡ ምድርና ፡ በኖዋያ ፡ ሰምልያ ፡ ደሴት ፡ መኻከል ፡፡ በልባም ፡ የቤሪንግ ፡ መንገድ ፡፡ በደ ፡ የመለካ ፡ መንገድ ፡ የሱንደ ፡ መንገድም ፡፡ የባበልመንደብ ፡ መንገድም ፡ በኤርትራ ፡ የኦርሙዝ ፡ መንገድም ፡ በፋርስ ፡ ጉበት ፡፡ በምብ ፡፡ የሬዋደስያ ፡ ወይስ ፡ የከፋ ፡ መንገድ ፡ የደርደነሎችም ፡ መንገድ ፡፡ የምድር ፡ ባሕሮችም ፡፡ በሰ ፡ እስያ ፡ የባይከል ፡ ባሕር ፡፡ በመኻከለኛ ፡ እስያም ፡ የከስጲያ ፡ ባሕር ፡፡ የሎጥ ፡ ባሕርም ፡ በጳለስቲና ፡፡ ዋንም ፡ በአርሜኒያ ፡ አራልም ፡ በተታርያ ፡፡ በምሥራቅ ፡ እስያም ፡፡ ቦልኻስና ፡ ሰይሳን ፡ በምንጎልያ ፡፡ ሌሎችም ፡፡

ምድር ፡ የምታወጣ ፡፡ በሰ ፡ እጅግ ፡ ደግ ፡ ለምድ ፡ ሬንደርም ፡ እንጨትም ፡ ሚነራሎችም ፡፡ በመኻከለኛ ፡ እስያም ፡ እህል ፡ እጅግ ፡ ሩዝም ፡ ሩበርብም ፡፡ ደህና ፡ ፈረስም ፡ ገመልም ፡ ላምም ፡ የበደ ፡ አህያም ፡ ነሽም ፡ በግም ፡፡ ወርቅም ፡ ብርም ፡ ባዜቃም ፡ ብረትም ፡፡ በደ ፡ የደ

ይጣንም ፡ ማምለክ ፡ በስሎንና ፡ በየኢዲች ፡ ለበግደድ ፡ በሚቀርቡ ፡፡ የድሬቦች ፡ ማምለክም ፡ በሊባኖስ ፡ ተረፈ ፡፡ እሌህ ፡ ሁሉም ፡ አረማውያን ፡ ናቸው ፡፡ አይሁድም ፡ የሌዩ ፡ ልዩ ፡ አይነት ፡ አሉ ፡ በሶርያ ፡ በቦኻራም ፡ በሩስያም ፡ በህንድም ፡፡ የክርስቲያንም ፡ ብዙ ፡ ከሥላሞች ፡ በታች ፡ ናቸው ፡ በቱርክያና ፡ በፋርስ ፡ መንግሥት ፡ የቀሩም ፡ በሩስያና ፡ በንግሊዝ ፡ ግዛት ፡ ናቸው ፡፡ የሃይማኖት ፡ መጀመርያ ፡ በእስያ ፡ ነበረ ፡፡ ከዚያ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ መድኅኒት ፡ ተገልጥዋልና ፡ ከአደም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ድረስ ፡፡ ከየሩሳሌም ፡ ዘንድ ፡ የወንጌል ፡ ዕውቀት ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ወጣች ፡ ከቆንስታንቲኖስ ፡ ዘመንም ፡ ጀምሮ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ገዛች ፡፡ ምነው ፡ እስያ ፡ ሁሉ ፡ ዛሬ ፡ ጨለማ ፡ ናት ፡፡ ይህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ነው ፡ በክርስቲያን ፡ ኃጢአት ፡ የሰውን ፡ ቃል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ አድርገዋልና ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ስለዚህ ፡ በሰው ፡ ባርነት ፡ በታች ፡ አደረጋቸው ፡ እርሳቸው ፡ በኃጢአታቸው ፡ አዝነው ፡ ወደ ፡ ሐዋርያት ፡ ይውሃትና ፡ ሕይወት ፡ እስኪመለሱ ፡ ድረስ ፡፡ ዛሬም ፡ የምዕራብ ፡ ወንድሞቻቸው ፡ የጵሮተስታንቶች ፡ አይነተኞች ፡ ክርስቲያናት ፡ ያዝኑላቸዋል ፡ መለክተኞቻቸውንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ይዘው ፡ ይሰዱላቸዋል ፡፡ ደሩ ፡ ጥቂት ፡ ናቸው ፡ ከለልባቸውና ፡ በደስታ ፡ የሚቀበሉት ፡፡ ያም ፡ ወደሚገኝበት ፡ የክርስቶስን ፡ ነገር ፡ ወደማይሰሙ ፡ የወንጌል ፡ መለክተኞች ፡ ትቢያቸውን ፡ ከግራቸው ፡ አርግፈውት ፡ ክርስቲያንንም ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ እሥላሞች ፡ ወደ ፡ አይሁድም ፡ ወደ ፡ አረማውያንም ፡ ያልፋሉ ፡፡ ባረማውያንም ፡ መኻከል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስራ ፡ እጅግ ፡ ነው ፡ በዘመናችን ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በመለክተኞች ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ እስያ ፡ ሁሉ ፡ ደረሰ ፡፡ የሲቢርያ ፡ ሽማኖች ፡ እንኳ ፡ ሰሙት ፡፡ በህንድም ፡ የወንጌል ፡ ማስተማርዎች ፡ መልተዋል ፡፡ ሕፃናትም ፡ እንኳ ፡ የተዕቢተኞችን ፡ የብረማኖችን ፡ ስንፍና ፡ አይተው ፡ ይጸይፋሉ ፡ ካረማውያንም ፡ ብዙ ፡ ሃይማኖትን ፡ ተቀበሉ ፡፡ ደሩ ፡ እኛ ፡ እጅግ ፡ እንጠንቀቅ ፡ ፊተኞች ፡ ሁነ

ን ፡ የምንመስል ፡ ኗለኞች ፡ እንደንሆን ፡ አረማውያንም እንደደቀድሙን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ በመ ግባት ፡፡

መከፈል ፡፡ እስያ ፡ በ፫፡ ክፍል ፡ ትከፈላለች ፡፡ በሰሜ ን ፡ እስያ ፡፡ በመኻከለኛ ፡ እስያም ፡፡ በደቡብ ፡ እስያም ፡፡

## ፩፡፡ የሰሜን ፡ እስያ ፡

## ወይስ ፡

## የእስያ ፡ ሩስያ ፡፡

ስ ፡፡ ወ ፡፡ ታት ፡፡ ርት ፡ ፵፫°፡ ከምቅ ፡ ርት ፡ እስከ ፡ ፻፹፩°፡ ከ ምብ ፡ ርት ፡ ድረስ ፡፡ ወድ ፡ ፵፬°፡ —፫፰°፡፡ ወደ ፡ ሰ ፡ በውርጭ ፡ ባሕር ፡ ወደ ፡ ምብ ፡ በኤውሮጳ ፡ ሩስያ ፡ ወደ ፡ ደ ፡ በጪን ፡ መንግሥት ፡ በተታርያም ፡ ወደ ፡ ምቅ ፡ በኦኾጽክ ፡ ባሕር ፡ በከምቻትካ ፡ ባሕርም ፡ በቤሪንግ ፡ መንገድም ፡ ተወሰነች ፡ ታትዋም ፡ ፬፡ ሚልዮን ፡ ሚላ ፡ ያህላል ፡፡

የምድር ፡ ጠባይ ፡፡ በሰ ፡ እጅግ ፡ ይበርደል ፡ በክረም ት ፡፡ ስለዚህ ፡ ሞስ ፡ የሚባል ፡ የሬንዲር ፡ ቀለብ ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይበቅልም ፡፡ በመኻከልም ፡ ታላቆች ፡ ውኃ ፡ የሌ ላቸው ፡ በረኾች ፡ አሉ ፡፡ በደቡብም ፡ በበጋ ፡ እጅግ ፡ ይሞ ቃል ፡፡ የደውሮስ ፡ በረኻ ፡ ምድር ፡ ጭው ፡ ነው ፡፡ ከሌላ ፡ የተሻለች ፡ ምድር ፡ በቦልጋ ፡ ቀኝ ፡ ደርቻ ፡ ናት ፡፡ ተራሮ ች ፡፡ ኡራል ፡ ወርቆቱርም ፡ እጅግ ፡ አልማስ ፡ ወርቅም ፡ ብረትም ፡ ነሣስም ፡ ወደሚገኝበት ፡ ያልታደም ፡ የሳደንስ ክም ፡ የደውሮስም ፡ የበደከልም ፡ ተራሮች ፡ የኦኾጽክና ፡ የከምቸትካ ፡ ተራሮችም ፡ በመኻከላቸው ፡ አያሌ ፡ ውል ካኖች ፡ ያሉ ፡፡ ታላቆች ፡ ወንዞችም ፡፡ ኦቢ ፡ ሌናም ፡ የኒሰ ይም ፡ እንደጊርካም ፡ በሰ ፡፡ ደንም ፡ ኩባንም ፡ ቦልጋም ፡ ኡራልም ፡ በሊባ ፡፡ አንጕራና ፡ ሴሊንጋም ፡ በአዜብ ፡ አናደርም ፡ በምሥኣ ፡፡ የምድር ፡ ባሕሮችም ፡፡ የከስጲ ያ ፡ ባሕር ፡ የአራል ፡ ባሕርም ፡ የበደከል ፡ ባሕርም ፡ አያሌ ፡ ሌሎችም ፡፡

ምድር ፡ የምታወጣ ፡፡ በሊባ ፡ እጅግ ፡ እህል ፡ ጥ

ጥም ፡ ወይንም ፡ ሀርም ፡ ከብትም ፡፡ በሲቢርያ ፡ ሰ ፡ እጅግ ፡ ደኅና ፡ የሀርምሊን ፡ የጾብልም ፡ የጥቁርና ፡ የሀረንጓዴ ፡ ቀበሮም ፡ የበረኻ ፡ ፈረስና ፡ የሬንደር ፡ ብዛትም ፡፡ ወደ ፡ ደ ፡ እጅግ ፡ እንጨት ፡ በበደከል ፡ ባሕር ፡ በኩልም ፡ እጅግ ፡ ከብት ፡ በተራሮችም ፡ ብዙ ፡ ሚታሎችና ፡ አልማስ ፡ ሌሎችም ፡ ሚነራሎች ፡፡

የጅ ፡ ስራ ፡ ጥቂት ፡ ነው ፡፡ በቦልጋ ፡ በኩል ፡ የቆርበት ፡ የሀርም ፡ የከዊያርም ፡ የሚታሎችም ፡ መስሪዮች ፡ አሉ ፡፡ መሻየጥም ፡ በረሮች ፡ እጅ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ፋርስና ፡ ወደ ፡ ጪንም ፡፡ የለምድ ፡ ገቢያም ፡ ወደ ፡ ኤውሮጳና ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ አሜሪካ ፡ ይሔደል ፡፡

ባላገሮች ፡ ፷፤ ሚልዮን ፡ ያህላሉ ፡፡ ማምለካቸውም ፡ የክርስቲያን ፡ የሥላሞችም ፡ ያረማውያንም ፡ ማምለክ ፡ ነው ፡ ያይሁድም ፡፡

የመንግሥት ፡ መግዛት ፡፡ በሩስያ ፡ ቄሣር ፡ መስለኞች ፡ ትገዛለች ፡ እርሳቸውም ፡ ከጌታቸው ፡ ርቀዋልና ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ያደርጋሉ ፡፡

መከፈል ፡፡ በ፲፪፤ ግዛት ፡ ትከፈላለች ፡፡

### 1. የአስትረኻን ፡ ግዛት ፡፡

አስትረኻን ፡ ታ ፡ ከተማ ፡ በቦልጋ ፡ አፊ ፡ ፹፲፻፤ ሰዎች ፡፡ እጅግ ፡ መሻየጥ ፡፡ ካረስ ፡፡ ሳረቶፍ ፡፡ ሰረጵታ ፡፡

### 2. የካሰን ፡ ግዛት ፡፡

ካሰን ፡ ፲፷፲፻፤ ሰዎች ፡ የጳጳስ ፡ መቀመጫ ፡፡ ኡኒዌርሲታስም ፡ አያሌ ፡ መስሪዮችም ፡፡

### 3. የኦርንቡርግ ፡ ግዛት ፡፡

ኦርንቡርግ ፡ ፷፪፲፻፤ ሰዎች ፡፡ አምባ ፡፡ እጅግ ፡ መሻየጥ ፡፡ የጋሻ ፡ ጦር ፡ መሰብሰቢያ ፡፡ ግዞት ፡ ለኤውሮጳ ፡ በደዮች ፡፡

ኡራልስክ ፡ የኮሰኮች ፡ ስፍራ ፡፡

4. የጆርሚያ ፡ ግዛት ፡፡

5. የቶቦልስክ ፡ ግዛት ፡፡

ቶቦልስክ ፡ በኢርቲሽ ፡ ወንዝ ፡ የሲቢርያ ፡ ከተማ ፡ ፲፰፻፻፡፡ ሰዎች ፡ ከርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ ካገሬ ቸው ፡ የተሳደዱ ፡ በደለኞች ፡፡ የኤጲስቆጶስ ፡ ዐቀብዐጫ ፡፡ እጅግ ፡ መሻ የጥም ፡፡

ከተሪንንቡርግ ፡ የተራሮች ፡ ስራ ፡ ማስተማርዮች ፡፡

6. የቶምስክ ፡ ግዛት ፡፡

ቶምስክ ፡፡ ፲፪፻፡፡ ሰዎች ፡፡ አያሌ ፡ መሻየጥ ፡፡

7. የየኒሰይስክ ፡ ግዛት ፡

የኒሰይስክ ፡ ታላቅ ፡ ገቢያ ፡፡

8. የኢርኩጽክ ፡ ግዛት ፡

ኢርኩጽክ ፡ ፳፻፡፡ ሰዎች ፡፡ የላማ ፡ አረማውያን ፡ ሁላቸው ፡ ጥቂት ፡ ክርስቲያን ፡ ቀርተው ፡፡ ዛሬ ፡ ፳፬፡ አመት ፡ የወንጌል ፡ መለክተኞች ፡ ከዚያ ፡ አስተማረ ፡፡ ከብዙ ፡ ድካምም ፡ በኋላ ፡ አሁን ፡ አያሌ ፡ አረማውያን ፡ በውነት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመለሱ ፡ መምህራናቸውንም ፡ በማስተማር ፡ ያግዛሉ ፡፡

9. የያኩጽክ ፡ ግዛት ፡፡

10. የነርቺንስክ ፡ ግዛት ፡፡

11. የሲሊንጊንስክ ፡ ግዛት ፡፡

12. የኦኾጽክ ፡ ግዛት ፡፡

---

፪፡፡ መካከለኛ ፡ ወይስ ፡ ደጋ ፡ እስያ ፡፡

በሰሜንና ፡ በደቡብ ፡ እስያ ፡ በመካከል ፡፡ ደህች ፡ ምድር ፡ ገና ፡ በጣም ፡ አልታወቀችም ፡፡ ያሉባት ፡ ሰዎች ፡ ፳፫፡

ሚልዮን ፡ ያህላሉ ፡፡ በሌህም ፡ ምድሮች ፡ ትከፈላለች ፡፡
1. ከውካስያ ፡፡ 2. ተታርያ ፡፡ 3. ደጋ ፡ ጤን ፡፡ 4. ቲቤት ፡፡
5. ኔጳል ፡፡

1. የከውካስያ ፡ ኢስትሞስ ፡፡

ወደ ፡ ሰ ፡ በእስያ ፡ ሩስያ ፡ ወደ ፡ ምቅ ፡ በከስጲያ ፡ ባሕር ፡ ወደ ፡ ደ ፡ በፋርስ ፡ ወደ ፡ ምብ ፡ በጥቁር ፡ ባሕርና ፡ በእስያ ፡ ቱርክያ ፡ ተወሰነች ፡፡ ይህች ፡ ምድርም ፡ እጅግ ፡ ደግ ፡ ናት ፡፡ የከወከሱስ ፡ ተራሮች ፡ የኩባንም ፡ የፋሲስም ፡ የቴረክም ፡ የኩርም ፡ የከረስም ፡ ወንዞች ፡ አሉባት ፡፡ ምድርም ፡ የምታወጣ ፡ እጅግ ፡ የጅ ፡ ስራና ፡ መኻየጥ ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ ነው ፡፡

ባላገሮች ፡፡ ተታሮች ፡ (እርሳቸውም ፡ እሥላሞች ፡) ጌዎርጊዮችም ፡ (እርሳቸውም ፡ የሩም ፡ ክርስቲያን ፡) አርመኖችም ፡፡ የቀመኞች ፡ ወገንም ፡ ቸርከሶች ፡ የተባሉ ፡፡
መከፈል ፡፡

፩፩፡ በሰሜን ፡፡

*a.* ቸርከስያ ፡ ባላገሮችዋ ፡ በስም ፡ ክሩስያ ፡ በታች ፡ ያሉ ፡ ደሩ ፡ ወትሩ ፡ ሁከትን ፡ ያደርጋሉ ፡፡

*b.* የከልሙኮች ፡ ምድር ፡ ከከውከሱስ ፡ ወደ ፡ ምቅ ፡፡ አርዌ ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ፡ ለሩሶችም ፡ ይገዛሉ ፡፡

*c.* ደግስታን ፡ በከውከሱስ ፡ ምቅ ፡ በከስጲያ ፡ ባሕር ፡ በኩል ፡፡

ደርበንት ፡፡ ባኩ ፡፡ በባኩ ፡ አቅራቢያ ፡ ወትሩ ፡ እሳት ፡ ከምድር ፡ ወጥቶ ፡ ይቃጥላል ፡፡ እሳትንም ፡ የሚያመልኩ ፡ የድሮ ፡ ፈርሶች ፡ ከዚህ ፡ ይሰበሰባሉ ፡፡

*d.* ለስጊስታን ፡፡ ደግ ፡ ምድር ፡፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ቀመኞች ፡ ናቸው ፡፡

፪፪፡ በደቡብ ፡፡

የሩስያ ፡ ጌዎርጊያ ፡ ወይስ ፡ ግሩሲኒያ ፡፡

ቲፍሊስ ፡ ደህና ፡ ከተማ ፡ ፪፻፻፡፡፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ የአርመኖችና ፡ የሩሞች ፡ የጵሮትስታንቶችም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡፡

ራሮችም ፡ ታላቅ ፡ ምድር ፡ ከቱርኮችና ፡ ከፋርሶች ፡ እጅ ፡ ወሰዱ ፡፡ ከተሞች ፡፡ አኻልጺግ ፡ በጥቁር ፡ ባሕር ፡ እጅግ ፡ መሻየጥ ፡ ያለበት ፡፡ ኤሪዋን ፡ የአርመኖች ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ መቀመጫ ፡፡

---

## 2. ታላቅ ፡ ተታርያ ፡ ወይስ ፡ ጀጋታይ ፡፡

ስ ፡፡ ወ ፡፡ ታት ፡፡ ርት ፡ ፶፫° — ፫፬° ፡፡ ወድ ፡ ፴፯° — ፶፬° ፡፡ ወደ ፡ ሰ ፡ በሩስያ ፡ ወደ ፡ ምቅ ፡ በደጋ ፡ ጪንም ፡ ወደ ፡ ደ ፡ በጪን ፡ በህንድም ፡ በፋርስም ፡ ምድሮች ፡ ወደ ፡ ምብ ፡ በከስጲያ ፡ ባሕር ፡ ተወሰነች ፡፡ ታትዋም ፡ ፶፻፻ ሚላ ፡ ነው ፡፡ የምድር ፡ ጠባይ ፡፡ ክሊማና ፡ የምድር ፡ ደግነት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነው ፡፡ ታላቆች ፡ ተራሮችም ፡ ሙስተግና ፡ የብሉር ፡ ተራሮች ፡ ናቸው ፡፡ ታላቆች ፡ ወንዞችም ፡፡ ሲር ፡ አሙድም ፡ ወደ ፡ አራል ፡ ባሕር ፡ ይገባሉ ፡፡ የምድር ፡ ባሕሮች ፡፡ የከስጲያ ፡ የአራልም ፡ አያሴ ፡ ሌሎችም ፡ የጨውና ፡ የምድረ ፡ በደ ፡ ባሕሮች ፡፡

ምድር ፡ የምታወጣ ፡፡ እህል ፡ ሩዝም ፡ ወይንም ፡ ጥጥም ፡ ተልባም ፡ ከነቢስም ፡ ሀርም ፡፡ ፈረስም ፡ በግም ፡ ላምም ፡ ገመልም ፡፡ ነሃስም ፡ ብረትም ፡ እርሳስም ፡ ወርቅም ፡ ብርም ፡ ጨውም ፡ ነፍታም ፡ የደንጊያ ፡ ቅቤም ፡ ሌላ ፡ ነገርም ፡፡

የጅ ፡ ስራ ፡ መሻየጥም ፡፡ ሀር ፡ ጥጥም ፡ የበግ ፡ ጸጕርም ፡ ሌላ ፡ እቃም ፡ ይሰራሉ ፡፡ ሰራተኞችና ፡ ነጋዴችም ፡ ቡኻሮች ፡ ናቸው ፡፡

ባላገሮች ፡ ፫፡ ሚልዮን ፡፡ እርሳቸውም ፡ ተታሮች ፡ ተኾከንቶችም ፡ ኡስበኮችም ፡ ቡኻሮችም ፡ ሁላቸውም ፡ ጥቂት ፡ ቀርተው ፡ እሥላሞች ፡ ናቸው ፡፡

የመንግሥት ፡ መግዛት ፡፡ እንደ ፡ አደሎች ፡ የሚዘሩ ፡ አሕዛብ ፡ ከየሾማግሎቻቸው ፡ በታች ፡ ናቸው ፡ የሚቀሩም ፡ ገዦች ፡ አልዋቸው ፡፡

መከፈል ፡፡ ፩፡ የሰሜን ፡ ተታርያ ፡፡ ፪፡ የደቡብ ፡ ተታርያ ፡፡

### ፲፩፡ የሰሜን ፡ ተታርያ ፡፡

*a.* የኪርጊሶች ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡፡ ኪርጊሶች ፡ ቀመኞች ፡ ናቸው ፡፡

*b.* የተሸከንቶች ፡ ምድርና ፡ ቱርክስታን ፡፡ ቱርኮች ፡ በድሮ ፡ ዘመን ፡ ከዚህ ፡ ተቀመጡ ፡ ወደ ፡ ዛሬ ፡ ምድራቸው ፡ ወጥተው ፡ ሳይሬልሱ ፡፡ ፴፻፻፡ የሚያህሉ ፡ ሰዎች ፡፡ ተሸከንት ፡ ታ ፡ ከተማና ፡ ገቢያ ፡፡ ፬፻፻፡ ሰዎች ፡ የኻን ፡ መኖርያ ፡፡

ቱርክስታን ፡ የእሥላሞች ፡ መቅደስ ፡ ሸይኽ ፡ አኽመድ ፡ የሚባል ፡ ወደ ፡ ተቀበረ ፡፡

*c.* የቱርኮማኖች ፡ ምድር ፡ በከስጲያና ፡ በአራል ፡ ባሕር ፡ በመኻከል ፡፡

*d.* የኪዋ ፡ ምድር ፡ በኣሙ ፡ ወንዝ ፡ ፍርያም ፡ ናት ፡፡ ፴፻፻፡ ሰዎች ፡፡

ኪዋ ፡ የኻን ፡ መኖርያና ፡ ከተማ ፡ ፻፻፡ ሰዎች ፡፡

*e.* የክረክልጶኮች ፡ ምድር ፡፡

### ፲፪፡ የደቡብ ፡ ተታርያ ፡ ወይስ ፡ ታላቅ ፡ ቡኻርያ ፡፡

ምድር ፡ እጅግ ፡ ፍርያም ፡ ናት ፡፡ የብሉር ፡ ታግለር ፡ ተራሮች ፡ አሉባት ፡ እጅግ ፡ ሜታሎችን ፡ የሚያወጡ ፡፡ ፬፡ ወይስ ፡ ፳፡ ሚልዮን ፡ ሰዎች ፡፡ እርሳቸውም ፡ እሥላሞች ፡፡

ቦኻራ ፡ ታ ፡ ከተማ ፡ እጅግ ፡ መሸየጥ ፡ ወደለበት ፡፡ ብዙ ፡ አይሁድ ፡፡

ሰመርካንድ ፡ በሶግድ ፡ ወንዝ ፡፡ የሥለሞች ፡ የከበረች ፡ ማስተማርያ ፡፡ የከዋክብትም ፡ መጠበቅያ ፡፡ አያሌ ፡ መስሪዮችም ፡፡

---

### 3. የጪን ፡ ደጋ ፡ እስያ ፡፡

ከታ ፡ ተታርያ ፡ ጀምራ ፡ እስከ ፡ ያጳን ፡ ባሕር ፡ ትሔደለች ፡፡ በሰ ፡ በእስያ ፡ ሩስያ ፡ በደ ፡ በታ ፡ በጪን ፡ መከበብያ ፡ ተወሰነች ፡፡ ታት ፡፡ ፪፡ ሚልዮን ፡ ሚላ ፡፡ የምድር ፡ ጠባይ ፡፡ ምድር ፡ እጅግ ፡ ደጋ ፡ ናትና ፡ ክሊማ ፡ በብዙ ፡ ስፍ

ራ ፡ እጅግ ፡ ይበርደል ። ወደ ፡ ደ ፡ ብዙ ፡ የጠለቁ ፡ የሚያፈ ሩም ፡ ቍሎች ፡ አሉ ። ታ ፡ ተራሮች ። ቦግዩ ፡ ሙስታግም ፡ አልታይም ። ታ ፡ ያሸዋ ፡ በረኻ ፡ አላት ፡ ኮቢ ፡ የሚባል ። ታ ፡ ወንዞች ። ወደ ፡ ባይከሊ፡ የሚገባ ፡ ሴሊንጋ ፡ ወደ ፡ ባሕርም ፡ የሚገባ ፡ አሙር ፡ ሌሎች ፡ ወንዞችም ፡ ብዙ ፡ አሉ ፡ በኮቢ ፡ አሸዋ ፡ የሚጠፉ ። ምድር ፡ የምታወጣ ። መድኃኒት ፡ ፈረስም ፡ አህያም ፡ ገመልም ፡ ነሽም ፡ በግም፡ እርያም ፡ የቢሳም ፡ እንስሳም ፡ ጥቁር ፡ ቢርም ፡ የነምር ፡ ታናሽ ፡ ምሳይም ፡ ጾብልም ፡ ሀርመሊንም ፡ መርድርም ።

ባላገሮች ። ፲፪ ወይስ ፲፫ ሚልዮን ፡ ይሆናሉ ። ማም ለካቸውም ፡ ተከፍለው ፡ የሥላሞችን ፡ ተከፍለውም ፡ የ ሽማኖችን ፡ ማምለክ ፡ ይከተላሉ ። በወገናቸውም ፡ ተታ ሮች ፡ ሞንጎሎችም ፡ መንቹ ፡ ቱንጉሶችም ፡ ናቸው ። እሌ ህም ፡ ሁሉ ፡ የመንቹ ፡ ቱንጉሶች ፡ ሲቀሩ ፡ ለጪና ፡ ቄሣር ፡ ይገዛሉ ። የቀሩም ፡ ከያጸን ፡ በታች ፡ ናቸው ።

መከፈል ። ፩ ታናሽ ፡ ቡኻርያ ። ፪ ሞንጎልያ ። ፫ መንቹርያ ። ፬ የኮርያ ፡ ጴኒንሱላ ።

## ፩ ታናሽ ፡ ቡኻርያ ።

በታ ፡ ቡኻርያም ፡ በሰ ፡ ተታርያም ፡ በሞንጎልያም ፡ በቲ ቤትም ፡ መኻከል ፡ ፩ ሚልዮን ፡ ሰዎች ። ምድሪቱም ፡ በ ፰ ግዛቶች ፡ ተከፈላለች ። የታወቁ ፡ ከተሞችም ፡ እሌህ ፡ ናቸው ። የርኪን ፡ ታ ፡ ገቢያ ። ከሽገርም ፡ ቱርፈንም ፡ ኮ ቱንም ፡ ቻነይም ።

## ፪ ሞንጎልያ ።

ከታናሽ ፡ ቡኻርያ ፡ ወደ ፡ ምቅ ፡ ወደ ፡ ሰ ፡ በሲቢርያ ፡ ወ ደ ፡ ምቅ ፡ በቱንጉስያ ፡ ወደ ፡ ደ ፡ በጪን ፡ ተወሰነች ። ፬ ሚ ልዮን ፡ ሰዎች ፡ እርሳቸውም ፡ ተከፍለው ፡ ሞንጎሎች ፡ ተ ከፍለውም ፡ ከልሙኮች ፡ ሁላቸውም ፡ የላማ ፡ ማምለ ክ ፡ ያሉ ። ለጪን ፡ ቄሣርም ፡ ይገዛሉ ።

ሞንጎልያም ፡ በምቅ ፡ በምብ ፡ ትከፈላለች ።

ኡርጋ ፡ የጪን ፡ ብርቱ ፡ ስፍራ ፡ በሩስያ ፡ ወሰን ። የሞን

ጎሎች፡ ገዢዎ፡ የላማም፡ ሊቀ፡ ካህናታቸው፡ መኖርያ ።

## ፫፫፡፡ መንቹርያ፡ ወይስ፡ ቱንጉስያ ።

፳፤ ሚልዮን፡ ሰዎች፡ የላማ፡ ወገን ። ለጨን፡ ቄሣርም፡ ይገዛሉ ። ታላቅ፡ ወንዝ፡ አሙር፡ የምድር፡ ባሕርም፡ ሁንካ፡ ነው ። ምድርም፡ በ፫፤ ግዛት፡ ተከፈለች ። *a.* ጺ.ጺ.ከር፡ ከትማዋም፡ ጺ.ጺ.ከር ። *b.* ኪ.ሪዮ፡ ከተማዋም፡ ኪ.ሪዮ፡ የቄሣር፡ መስለኒ፡ መቃመጫ ። *c.* ልያ.ቶንግ፡ ፪፤ ሚልዮን፡ ሰዎች፡ ከተማም፡ ሺ.ንያንግ፡ የኩንሺ.፡ መቃበር፡ ወደለበት፡ የዛሬ፡ ቄሣሮች፡ የትውልደቸው፡ አባት ።

## ፬፬፡፡ የኮርያ፡ ጴኒንሱላ ።

ከመንቹርያ፡ ወደ፡ አዜብ፡ በያጳን፡ ባሕርና፡ በብጫ፡ ባሕርም፡ በመኻከል፡ የተዘረጋች፡ ናት ። ፰፤ ወይስ፡፲፤ ሚልዮን፡ ሰዎች፡ እርሳቸውም፡ ጪኒሶችና፡ ቱንጉሶች ። አምልኳቸውም፡ የኮንፉጽ፡ መንገድ፡ ነው ። የኮርያ፡ ንጉሥም፡ ለጪን፡ ቄሣር፡ ግብርን፡ ይገበራል ። ካገሩም፡ አንድ፡ ክፍል፡ ከያጳን፡ በታች፡ ነው ። እንግዶችንም፡ ወደ፡ አገሩ፡ ከመግባት፡ ይከለክላሉ ።

ኩንግ፡ ኪ.ታዎ፡ ከተማ፡ የንጉሥም፡ መኖርያ ። የንጉሥ፡ ቢብልዮቴካ፡ ጠባቂዩ፡ የንጉሥ፡ ዘመድ፡ የሚሆን ።

---

## 4. ቲቤት ።

ርት፡ ፳፰°፤—፴፭°፤ ወድ፡ ፸፯°፤—፻፬°፤ ታላቅነትዋም፡ ፶፻፻፤ ሚላ፡ ነው ። ደህች፡ ምድርም፡ በሰሜን፡ ደጋና፡ መካን፡ ናት፡ ክሊማም፡ ብርድ፡ ነው ። በደ፡ ግን፡ ክሊማና፡ ምድር፡ ደግ፡ ናቸው ። ከምድር፡ ተራሮች፡ ሁሉ፡ የሚበልጡ፡ በዚች፡ ምድር፡ ይገኛሉ፡ እርሳቸውም፡ የሂመላያ፡ ተራሮች፡ ናቸው ። ከርሳቸውም፡ አንዱ፡ ደወለጊር፡ የሚባል፡ ከፍታው፡ ፳፱፲፪፤ እግር፡ ያህላል ። ታላቆች፡ ወንዞች ። ገንጀስ፡ ቡረምጹትርም፡ አያሌ፡ ሌሎችም ። የምድር፡ ባሕሮችም ። ተርኪሪና፡ ያምድሮ ።

የምድር ፡ ጠባይ ፡፡ ክሊማ ፡ በሰ ፡ ብርድ ፡ በደ ፡ ትኩ
ስ ፡ በሁሉም ፡ ጤና ፡ ነው ፡፡ ብዙ ፡ ቡልካኖች ፡ አሉ ፡ ም
ድርም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ትናወጻለች ፡፡ ታላቆች ፡ ወንዞች ፡፡ ህ
ዋንግሆ ፡ ያንጸግያንግም ፡ ከርሳቸውም ፡ ሌሉ ፡ ታላቆችና ፡
ታናሾች ፡ ወንዞች ፡ ፲፱፤ ያህላሉ ፡፡ ብዙ ፡ መስኖችም ፡ አሉ ፡
አንዱም ፡ የቁሣር ፡ መስኖ ፡ የሚባል ፡ ፲፫፱፤ ፡ ሚላ ፡ ይ
ሔደል ፡

ምድር ፡ የምታወጣ ፡፡ እህል ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅም ፡ ጫ
ይ ፡ ጥጥም ፡ ሀርም ፡ መድኃኒትም ፡ ሡክርም ፡ ወይንም ፡፡
ላምም ፡ በግም ፡ ፈረስም ፡ የጪን ፡ መሬትም ፡፡

በጅ ፡ ስራም ፡ ብልሃተኞች ፡ ናቸው ፡፡ በጪን ፡ መሬትና ፡
በዝሆን ፡ ጥርስ ፡ በሌላ ፡ ነገርም ፡ የሚሰሩት ፡ እቃ ፡ ድንቅ ፡
ነው ፡፡ ደሩ ፡ ብልሃታቸው ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ አባቶቻቸው ፡ እ
ንደደረጉ ፡ እንዲሁም ፡ ልጆቻቸው ፡ ያደርጋሉ ፡ በብልሃታቸ
ውም ፡ አያድጉም ፡ አዲስ ፡ ነገርም ፡ አይጨሙሩላትም ፡፡ እ
ግዚአብሔርንም ፡ አያውቁምና ፡ ምድራዊት ፡ ብልሃታቸው ፡
ለነፍሳቸው ፡ ደህንነት ፡ አይጠቅምላቸውም ፡፡

መሻየጣቸውም ፡ አጅግ ፡ ነው ፡፡ ደሩ ፡ እንግዶችን ፡
ወደገራቸው ፡ አያስገቡም ፡፡ የንግደች ፡ ነጋደች ፡ ገቢያ ፡ በ
ባሕር ፡ ደር ፡ ያሉች ፡ ከተማ ፡ ካንቶን ፡ ብቻ ፡ ናት ፡፡

ባላገሮች ፡፡ ጪኒሶች ፡ የመንቹ ፡ ተታሮችም ፡ ህንደውያ
ንም ፡ ሞንጎሎችም ፡ ብዙ ፡ አይሁድም ፡፡ የመንግሥት ፡
ማምለክም ፡ የኮንፋጽ ፡ የላዎም ፡ የፎም ፡ ማምለክ ፡ ነ
ው ፡ ያረማውያን ፡ መንገድ ፡፡ በቀደምም ፡ ከሮምያ ፡ ከቶ
ሊካውያን ፡ መለክተኞች ፡ ብዙ ፡ ገቡ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችንም ፡
በስም ፡ ክርስቲያን ፡ አደረጉ ፡፡ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ ታላቅ ፡
ስደት ፡ ሆነባቸው ፡ ብዙም ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሞቱ ፡፡ ዛሬም ፡
ክርስቲያን ፡ ተብለው ፡ የተገኙ ፡ ጥቂት ፡ ናቸው ፡፡ ከወንጌ
ል ፡ መለክተኞችም ፡ አንደንድ ፡ ወደ ፡ ውሥጥ ፡ ገባ ፡ አያ
ሌም ፡ በወሰን ፡ ተቀምጠው ፡ በወንጌል ፡ ያስተምራሉ ፡፡ ዝ
ንድሮም ፡ በእንግሊዞችና ፡ በጪን ፡ መካከል ፡ የተነሣ ፡ ጦ
ር ፡ ለወንጌል ፡ የጪንን ፡ ደጅ ፡ እንዲከፍት ፡ ተስፋ ፡ ይደ
ረጋል ፡፡ የወንጌል ፡ መለክተኞች ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ በ

ጨን ፡ ቋንቋ ፡ አስተረጐመው ፡ ብዙም ፡ ሌሎችን ፡ ደህና ፡ መጻሕፍትን ፡ ለሕዝቡ ፡ ሰጡ ፡፡ አያሌ ፡ ጪኒሶችም ፡ በውነት ፡ ለክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ ተገዙ ፡፡

የመንግሥት ፡ መግዛት ፡፡ የቄሣር ፡ ፈቃድ ፡ በሕዝቡ ፡ ጉባኤ ፡ አልተወሰነም ፡፡ ባላገሮች ፡ መንግሥታቸውን ፡ የሰማይን ፡ መንግሥት ፡ ይልዋታል ፡፡ ሹማምታቸውም ፡ መንደሪኖች ፡ ይባላሉ ፡፡

መክፈል ፡፡ ይህች ፡ መንግሥት ፡ በ፲፰፡ ክፍል ፡ ተከፈላለች ፡፡

ጰኪንግ ፡ የከበረች ፡ ከምድር ፡ ከተሞችም ፡ ሁሉ ፡ በስፋትና ፡ በሰዎች ፡ ቍጥር ፡ የምትበልጥ ፡ ከተማ ፡ የቄሣርም ፡ መኖርያ ፡ ፪፡ ወይስ ፡ ፫፡ ሚልዮን ፡ ሰዎች ፡፡ የቄሣር ፡ ቤት ፡ ታላቅ ፡ ናት ፡ እጅግ ፡ ባለጠግነትም ፡ አለባት ፡፡ ያረማውያን ፡ መቅደሶች ፡ አያሌም ፡ የሥላሞች ፡ መስጊዶች ፡ የሬምና ፡ የሮምያ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡፡ አያሌ ፡ ማስተማርዮችም ፡፡

ሀንግቼውፉ ፡ ፩፡ ሚልዮን ፡ ሰዎች ፡ ከርሳቸውም ፡ ፯፻፻፡ የሀር ፡ ሸማኞች ፡፡

ካንቶን ፡፡ የከበረች ፡ ከተማ ፡ በባሕር ፡ ደርቻ ፡ ፩፡ ሚልዮን ፡ ፳፻፻፡ ሰዎች ፡፡ የጪን ፡ መጀመርያ ፡ ገቢያ ፡ የንግዶችም ፡ ስፍራ ፡፡ መካ ዉ ፡ የጶርቱጊሶች ፡ ግዛት ፡፡

ናንኪንግ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡፡

## የጪን ፡ ደሴቶች ፡፡

ፎርሞሳ ፡ በጪን ፡ ባሕር ፡ የምትኖር ፡ ተከፍላ ፡ ለጪን ፡ ተከፍላም ፡ ለራስዋ ፡ ትገዛለች ፡፡

የሎቹ ፡ ደሴቶች ፡ እጅግ ፡ ፍርያሞች ፡ ናቸው ፡፡ እህል ፡ ጫይም ፡ ብርብሪም ፡ ጥጥም ፡ ላምም ፡ ቀርቀሮም ፡ ነሃስም ፡ ይበዛባቸዋል ፡፡ ለሁለት ፡ ገዞችም ፡ ይገዛሉ ፡ አንዱ ፡ ለጪን ፡ አንዱም ፡ ለያጳን ፡፡ ብዙም ፡ የወርቅ ፡ የብርም ፡ የክርታስም ፡ የሌላ ፡ ስራም ፡ መስሪዮች ፡ አሉባቸው ፡፡

## 2. ያጳን ፡ ወይስ ፡ ኒፎን ።

ይህች ፡ መንግሥት ፡ ከስያ ፡ መንግሥቶች ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ምቅ ፡ ናት ። ርት ፡ ፻፴፩°፤ — ፻፵፪°፤ ወድ ፡ ፴°፤ — ፵፩°፤ የያጳን ፡ መንግሥትም ፡ ሁሉ ፡ ደሴቶች ፡ ናቸው ፡ ፫፤ ታላቆች ፡ ብዙም ፡ ታናኾች ፡ ደሴቶች ።

የዚች ፡ መንግሥትም ፡ ምድር ፡ በደሴቶች ፡ ሁሉ ፡ ደህና ፡ አይደለችም ፡ ደሩ ፡ በጎ ፡ አድርገው ፡ ይሰርዋታል ። ምድር ፡ የምታወጣ ። ሩዝ ፡ ጥጥም ፡ ከነቢስም ፡ ብርብሪም ፡ ቶምበኾም ፡ ዝንጃብርም ፡ ጫይም ፡ የዛፍ ፡ ፍሬም ፡ ወይንም ፡ የመድኃኒትም ፡ አታክልት ። ጎሽም ፡ ታናሽ ፡ ፈረስም ። ወርቅም ፡ ናስም ፡ ብረትም ፡ ቆርቆሮም ፡ ባዜቃም ፡ የከበሩ ፡ ደንጎችም ፡ ሌሎችም ፡ የሚጠቅሙ ፡ ሚነራሎች ።

በብልሃትና ፡ በውቀት ፡ የያጳን ፡ ሰዎች ፡ ከሚቀሩ ፡ ከስያ ፡ አሕዛብ ፡ ይበልጣሉ ። መስሪዮቻቸው ፡ እጅግ ፡ ደህና ፡ ናቸው ። የሀር ፡ የጥጥም ፡ የጨንም ፡ ስራ ፡ ተቀብቶ ፡ የተሣለውንም ፡ ደህናውን ፡ ክርታስ ፡ ይሰራሉ ። እርሶ ፡ በርሳቸውም ፡ ይሻያየጣሉ ፡ ከጨንና ፡ ከሆላንድ ፡ ሰዎችም ፡ ጋራ ፡ ሌሎች ፡ ነጋዴች ፡ ግን ፡ ተከለከሉ ።

ባላገሮች ። ፴፤ ሚልዮን ፡ ያህላሉ ። ማምለካቸውም ፡ የደላይላማ ፡ የኮንፉጽም ፡ የፎም ፡ ማምለክ ፡ ነው ። በቀደምም ፡ ብዙ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ከዚያ ፡ ተገኙ ፡ ስደትም ፡ ተነሣባቸው ፡ ፪፤ ሚልዮንም ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሞቱ ። ዛሬም ፡ ሃይማኖት ፡ እንዳይገባ ፡ ይከለክላሉ ።

የመንግሥት ፡ መግዛት ። ሁለት ፡ ገዦች ፡ አሉ ፡ አንዱ ፡ ለሥጋ ፡ ኩቦ ፡ የሚባል ፡ አንዱም ፡ ለነፍስ ፡ ደይሪ ፡ የሚባል ። በቀደም ፡ ደይሪ ፡ ብቻ ፡ ይገዛ ፡ ነበር ፡ የወታደር ፡ አለቃ ፡ እስኪነሣበት ፡ ድረስ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ ይህ ፡ አለቃ ፡ ኩቦ ፡ ተብሎ ፡ መግዛትን ፡ ሁሉን ፡ ወሰደ ፡ ለደይሪም ፡ የማምለክን ፡ መግዛት ፡ ተወለት ። ለኩቦም ፡ ፶፻፻፤ ወታደር ፡ እንዳሉ ፡ ይባላል ።

መከፈል ። በአይነተኛ ፡ ያጳንና ፡ በሚገበሩ ፡ አገሮች ። አይነተኛ ፡ ያጳንም ፡ በ፫፤ ክፍል ፡ ተከፈለች ። አያሌ ፡ ታላቆች ፡ ደሴቶች ፡ እሌህ ፡ ናቸው ። ያጳን ፡ (ደግሞ ፡ ኒፎን ፡ ተ

የበምቡስ ፡ ሽምበቆም ፡ ኢንዲጎም ፡ ሀርም ፡፡ ዝሆንም ፡ ዚ
ንጅሮም ፡ ጎማሬም ፡ የቢሳም ፡ እንስሳም ፡ ፈረስም ፡ ታላ
ቅ ፡ ነብርም ፡ በግም ፡ ላምም ፡ ታላቅ ፡ እባብም ፡ አዞም ፡፡
ወርቅም ፡ ብርም ፡ ነሓስም ፡ ብረትም ፡ ቀርቀሮም ፡ እርሳስ
ም ፡ የደንጊያ ፡ ከሰልም ፡ የከበረ ፡ ደንጊያም ፡ የልዩ ፡ ል
ዩ ፡ ወገን ፡ አልማስም ፡ ሉልም ፡ ጨውም ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ል
ዩ ፡ ሌላ ፡ ነገርም ፡፡

የጅ ፡ ስራ ፡ መሸየጥም ፡፡ የሀር ፡ የጥጥም ፡ የበግ ፡ ጸ
ጕርም ፡ የተልባም ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስራ ፡ የተሣለም ፡ የ
ሚታልም ፡ የቢሉርም ፡ የቀርበትም ፡ ስራ ፡ እጅግ ፡ ደግ ፡
ሰርተው ፡ ይሸየጡበታል ፡፡ የኢንዲጎ ፡ መስሪዮችም ፡ ብ
ዙ ፡ ናቸው ፡ እርሱንም ፡ ቅርፊትንም ፡ እጅግ ፡ ይሸየጣ
ሉ ፡፡ ከሌላ ፡ ይልቅም ፡ የሚሸየጡ ፡ የእንግሊዝ ፡ የህን
ድ ፡ ኮምጳኒ ፡ የተባሉ ፡ የነጋደች ፡ ጉባኤ ፡ ናቸው ፡፡

ባላገሮች ፡፡ ከሌሎች ፡ ይልቅ ፡ የህንዲ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፡
በ፬ ፡ መለየት ፡ የተለዩ ፡፡ ፩ ብራሚኖች ፡ እርሳቸውም ፡ ካ
ህናትና ፡ አዋቆች ፡፡ ፪ ሻትሮች ፡፡ እርሳቸውም ፡ ወታደሮ
ች ፡፡ ፫ በንያኖች ፡ እርሳቸውም ፡ ነጋደችና ፡ ብልሃተኞች ፡፡
፬ ሱድሮች ፡ እርሳቸውም ፡ ሰራተኞችና ፡ ድኆች ፡ ናቸው ፡፡
ከሌህ ፡ ፬ መለየትም ፡ ሌሎች ፡ አሉ ፡፡ ከህንዲ ፡ ወገን
ም ፡ ሌለ ፡ በህንድ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡ ሞጎ
ሎች ፡ ፈርሶችም ፡ አፍጋኖችም ፡ ሲክስም ፡ ዓረቦችም ፡
ጥቍርና ፡ ነጭ ፡ አይሁድም ፡ አርመኖችም ፡ ፈርንጆችም ፡
ከርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ እንግሊዞችና ፡ ጶርቱጊሶች ፡ ናቸው ፡፡
እሌህ ፡ ሰዎችም ፡ በብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋች ፡ ይናገራ
ሉ ፡፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ የተተረጐመባቸው ፡ የህንድ ፡ ቋ
ንቋች ፡ ከ፳ ይበዛሉ ፡፡ የህንድ ፡ አምልኮም ፡ የብረማ
ኖች ፡ አምልኮ ፡ ነው ፡፡ እርሳቸውም ፡ ፫፻፴ ሚልዮን ፡ አ
ማልክትን ፡ ያመልካሉ ፡፡ ከሌህ ፡ ሁሉም ፡ በላይ ፡ ፫ ናቸ
ው ፡ ብራማ ፡ ዊሽኑም ፡ ሲዋም ፡፡ ብራማ ፡ ፈጣሪ ፡ ዊሽኑ
ም ፡ ጠባቂ ፡ ሲዋም ፡ አፍራሽና ፡ አጥፊ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡፡ ከ
ሆስታቸውም ፡ በላይ ፡ ብራም ፡ ነው ፡ የሁሉ ፡ መጀመርያና ፡
ምንጭ ፡ የማይታይ ፡ ዓለምንም ፡ ሁሉን ፡ የሚሞላ ፡፡ ከዓ

ለምም ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የሚሆን ፡፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ በሮ ምያ ፡ መልእክት ፡ በመጀመርያ ፡ ምዕራፍ ፡ ስለ ፡ አረማው ያን ፡ የሚለው ፡ በጣም ፡ ይገለጻል ፡ በህንዱ ፡ ሰዎች ፡፡ አም ልኳቸውም ፡ የሥጋ ፡ አምልኮ ፡ ርኵሰትም ፡ የመላቸበት ፡ ነ ው ፡፡ እርሳቸውም ፡ እጅግ ፡ ይደክማሉ ፡ አማልክትን ፡ ለ ማስታረቅ ፡ ጽድቅንም ፡ ቅድስናውንም ፡ ለማገኘት ፡፡ ነፍ ሳቸውን ፡ የሚገድሉ ፡ ብዙ ፡ አሉ ፡፡ ሌሎችም ፡ በመግረ ፍ ፡ በድካምም ፡ በመውጋትም ፡ በመንደድም ፡ ባለመናገር ም ፡ ባለመንቀሳቀስም ፡ ሥጋቸውንና ፡ ነፍሳቸውን ፡ ይሠ ቅያሉ ፡ አማልክታቸውን ፡ ደስ ፡ ያሳኙ ፡ ዘንድ ፡ ክርስቶስ ን ፡ አያውቁምና ፡፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ የወንጌል ፡ ብርሃን ፡ ወጣባ ቸው ፡፡ የወንጌል ፡ መለክተኞች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ በመኻከላቸው ፡ አስተምረው ፡ የእግዚአብሔርም ፡ በረ ከት ፡ ከማስተማራቸው ፡ ጋራ ፡ ኑሮ ፡ ብዙ ፡ አረማውያን ፡ ከጣዖታታቸው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመለሱ ፡ ከልባቸ ውም ፡ ክርስቲያን ፡ ሆኑ ፡፡ በወንጌል ፡ መለክተኞችም ፡ በ ማስተምርያቸው ፡ ብዙ ፡ እአላፍ ፡ አሽክሮች ፡ የክርስቶ ስን ፡ የመድኃኒቱን ፡ መንገድ ፡ ይማራሉ ፡፡ በዚህ ፡ ትምህር ትም ፡ ብዙ ፡ ለዘላለም ፡ ደህንነት ፡ ጠቢባን ፡ ይሆናሉ ፡ በ ክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡፡ ከህንዱ ፡ አምልኮም ፡ በቀር ፡ የእ ሥላም ፡ የፈርስም ፡ የሲክስም ፡ ያይሁድም ፡ የክርስቲያ ንም ፡ ማምለክ ፡ አሉ ፡፡ የተገኙ ፡ ክርስቲያንም ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፡፡ እርሳቸውም ፡ ጵሮትስታንቶች ፡ ሮማ ውያንም ፡ አርመኖችም ፡ የቶማስ ፡ ወገን ፡ ሶርያውያንም ፡፡

የ ህን ድ ፡ መ ግዛ ት ፡፡ የህንዱ.ስታን ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ ዛ ሬ ፡ በጣም ፡ ለንግሊዞች ፡ ይገዛል ፡፡ የቀረች ፡ ምድር ፡ ክፍ ልም ፡ ለንግሊዞች ፡ ትገበራለች ፡ ተከፍላም ፡ ለሌሎች ፡ ፋ ርንጆች ፡ ተከፍላም ፡ ለየገዢዋ ፡ ትገዛለች ፡፡

## A. የንግሊዞች ፡ ግዛት ፡፡

የእንግሊዞች ፡ ግዛት ፡ ኢየተጨመረ ፡ ይበዛል ፡፡ የህንድ ፡ ኮምጳኒ ፡ የተባለች ፡ የእንግሊዝ ፡ ነጋዶች ፡ ጉባኤ ፡ ከንግሊ ዝ ፡ ንግሥት ፡ በታች ፡ ትገዛዋለች ፡፡ ምድሪቸውም ፡ በ፬፤

ግዛት ፡ ተከፈለች ፡፡ በየግዛትም ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ገዢ ፡ ተሾ መ ፡ በሁላቸውም ፡ ላይ ፡ የንግሥት ፡ መስለኒ ፡ ተሾመ ፡ በ ከልክታ ፡ የሚቀመጥ ፡፡ ብዙ ፡ ከሚስዮን ፡ ጉባኤዮች ፡ የ ወንጌልን ፡ መልክተኞች ፡ ይልካሉ ፡፡ የሚወጣ ፡ ግብርም ፡ ምናልባት ፡ ፪፻፤ ሚልዮን ፡ ቀርሽ ፡ ያህላል ፡ ወታደሮች ም ፡ ከ፷፻፻፤ ይበዛሉ ፡፡

*a.* የከልክታ ፡ ግዛት ፡ ወይስ ፡ በንጋል ፡፡

ከልክታ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ በገንጀስ ፡ ወንዝ ፡ ፩፤ ሚልዮ ን ፡ ሰዎች ፡፡ የመስለኒና ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ መኖርያ ፡፡ ብዙ ፡ ማስተማርዮችም ፡፡ አያሌም ፡ የወንጌል ፡ መልክተኞች ፡፡ ፎርት ፡ ዊልየም ፡ ብርቱ ፡ አምባ ፡፡ የጾር ፡ ማስተማርያ ፡፡ የእንግሊዝ ፡ ኡኒቬርሲታስ ፡ ለህንድ ፡ ብላቴኖች ፡፡ አያሌ ም ፡ የውቀትና ፡ የበጎ ፡ ስራ ፡ ጉባኤዮች ፡፡ ታላቅ ፡ የትምር ት ፡ አታክልት ፡፡ ብዙ ፡ መርከቦችም ፡፡

ደካ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡፡ ደህና ፡ ገቢያና ፡ ብዙ ፡ መስሪዮች ፡፡

ቡርድዋን ፡፡ የወንጌል ፡ መልክተኞች ፡፡ አያሌ ፡ ማስተ ማርዮች ፡ ለወንደችና ፡ ለሴቶች ፡ አሽክሮች ፡፡

ክርሽናጉር ፡፡ አምና ፡ ከዚህ ፡ አያሌ ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ባን ድ ፡ ጊዜ ፡ ከአረሚነታቸው ፡ ወደ ፡ እውነተኛ ፡ አምላክ ፡ ተ መለሱ ፡፡ አያሌ ፡ የወንጌል ፡ መልክተኞች ፡፡

ሙርሺደበድ ፡፡ በቀደም ፡ የበንጋል ፡ ከተማ ፡፡

በናሬስ ፡ በገንጀስ ፡፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ለህንድ ፡ ማምለክ ም ፡ የተቀደሰች ፡ አገር ፡ ፴፻፻፤ ሰዎች ፡፡ የወንጌል ፡ መልክ ተኞች ፡፡ ነግጾርና ፡ ጎረክጾር ፡ የሚስዮን ፡ ስፍሮች ፡፡

*b.* የአግራ ፡ ግዛት ፡፡

አግራ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ያዛዢም ፡ መኖርያ ፡፡ አያሌ ፡ ከወንጌል ፡ መልክተኞች ፡፡

ዴሊ ፡፡ የታላቅ ፡ ሞጉል ፡ ከተማ ፡፡ እርሱ ፡ እሥላም ፡ ነ ው ፡ በቀደምም ፡ የህንድ ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡ ነበር ፡ እንግሊዞች ፡ እስኪያወርዱት ፡ ድረስ ፡፡ ሁሉንም ፡ ወሰዱበት ፡ ከዚች ፡ ከተማ ፡ በቀር ፡ አዝነውለታልና ፡፡

c. የመድራስ ፡ ግዛት ፡፡

መድራስ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ የመሻየጥና ፡ የመርከቦች ፡ መሰብሰቢያ ፡፡ ፬፻፶፱፡ ሰዎች ፡፡ ያዛዢና ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ መቀመጫ ፡፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የተባለች ፡ ብርቱ ፡ አምባ ፡፡ አያሌም ፡ ከወንጌል ፡ መለክተኞች ፡፡ የሚስዮንና ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጉባኤዮችም ፡፡ እጅግ ፡ መሻየጥም ፡ ብዙ ፡ መስሪዮችም ፡፡

መልያጵር ፡ ወደስ ፡ ቅዱስ ፡ ቶማስ ፡፡ የቅዱስ ፡ ቶማስ ፡ ወገን ፡ ክርስቲያናት ፡ ይህነን ፡ ስፍራ ፡ እጅግ ፡ ያከብራሉ ፡፡

ትሪቺኖጶሊና ፡ ቲነበሊ ፡ የሚስዮን ፡ የተባረኩ ፡ ስፍሮች ፡፡ ብዙ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተመለሱ ፡ አረማውያን ፡፡ ብዙ ፡ ማስተማርዮች ፡፡

d. የቦምባይ ፡ ግዛት ፡፡

ቦምባይ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ደህና ፡ ታላቅ ፡ መርስም ፡ ለጾርና ፡ ለመሻየጥ ፡ መርከቦች ፡፡ ፪፻፶፱፡ ሰዎች ፡፡ ያዛዢና ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ መቀመጫ ፡፡ የሚስዮንና ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ የሌላ ፡ በጎ ፡ ነገርም ፡ ጉባኤዮች ፡፡ አያሌም ፡ ከወንጌል ፡ መለክተኞች ፡፡ አያሌ ፡ ማስተማርዮችም ፡፡ እጅግ ፡ መሻየጥም ፡፡ የዝሆንና ፡ የሰልሰታ ፡ ደሴቶችም ፡ ይቀርባሉ ፡፡

ሱራት ፡ ፺፻፱፡ ሰዎች ፡ ታላቅ ፡ ገቢያ ፡፡ ብዙ ፡ መስሪዮችም ፡፡

ተሊቸሪ ፡ የጾር ፡ እቃ ፡ መሰብሰቢያ ፡፡

ሚሶር ፡ ብርቱ ፡ ከተማ ፡፡ ከሊኩት ፡ ደህና ፡ ገቢያ ፡፡ ኮቺን ፡ ደህና ፡ ገቢያ ፡፡ መንገሎርና ፡ ደርወር ፡ ነስክም ፡ የሚስዮን ፡ ቦቶች ፡፡ ኮቲምና ፡ ትረበንኮር ፡ የቶማስ ፡ ወገን ፡ ስፍሮች ፡፡ የወንጌል ፡ መለክተኞችም ፡ ከዚያ ፡ አሉ ፡፡

## B. የሌሎች ፡ ፈርንጆች ፡ ግዛት ::

### *a.* የሆላንድ ፡ ግዛት ::

ለሆላንድ ፡ አንዳንድ ፡ ታናሽ ፡ ክፍል ፡ አላት ፡ በበንጋል ፡ በኮሮመንድልም ፡ በመለባርም ፡ ደርቻ ፡ ፲፻፻፤ ሰዎች ::

ጳልየከት ፡ በኮሮመንድል ፡ ደርቻ :: ፎርት ፡ ገልድርን ፡ አምባ :: ሰድረስ ፡ በበንጋል :: ብዙ ፡ መስሪዮች ::

### *b.* የፈረንሲሶች ፡ ግዛት :: ፲፩፻፻፤ ሰዎች ::

ቸንደርናጉር ፡ በበንጋል :: ጶንዲቸሪና ፡ አርያንኩጳን ፡ በኮሮመንድል ፡ ደርቻ ፡ የመሻየጥ ፡ ከተሞች ::

### *c.* የጶርቱጊሶች ፡ ግዛት :: ፳፭፻፻፤ ሰዎች ::

ጎኣ ፡ ብርቱ ፡ ከተማ :: የመሻየጥ ፡ ስፍራ ፡ ፲፻፻፤ ሰዎች :: ከርሳቸውም ፡ ፪፲፻፤ ሞነክሶችና ፡ ቀሳወስት ፡ በላያቸውም ፡ አንድ ፡ ሜትሮጶሊታን ፡ አለ ::

### *d.* የደኖች ፡ ግዛት ፡ ፭፻፻፤ ሰዎች ::

ትረንክባር ፡ በኮሮመንድል ፡ ደርቻ :: ሴረምጶር ፡ በበንጋል :: በሌህ ፡ ሁለት ፡ ቦቶችም ፡ አያሌ ፡ ከወንጌል ፡ መለክተኞች ፡ አሉ :: በሴረምጶርም ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ በብዙ ፡ ቋንቋዎች ፡ አስተረጐሙ ::

---

## C. የሌሎች ፡ የህንድ ፡ አሕዛብ ፡ ግዛት ::

እርሳቸውም ፡ ተከፍለው ፡ ለራሳቸው ፡ ተከፍለውም ፡ ለእንግሊዞች ፡ ይገዛሉ ::

### *a.* የሲክስ ፡ ግዛት ::

እርስዋም ፡ በሲንድና ፡ በገንጀስ ፡ መኻከል ፡ ትኖራለች ፡ ፫፤ ሚሊዮን ፡ ሰዎችም ፡ አሉባት :: ንጉሥም ፡ አላቸው ፡ ለወታደሩ ፡ የፈርንጆችን ፡ ሥርዓት ፡ ያስደረገ ፡ እንደሁም ፡ በረታ :: አምልኳቸውም ፡ በቀደም ፡ የብረማኖች ፡ መንገድ ፡ ነበረ ፡ ዛሬም ፡ ተለውጠው ፡ ለብቻቸው ፡ ናቸው ::

ለሆር ፡ ታላቅ ፡ ብርቱም ፡ ያመረችም ፡ ከተማ ፡ የንጉሥ

ም ፡ መናርያ ፡፡ አመርሶር ፡ ደህና ፡ ገቢያ ፡፡ ሙልታን ፡ ፍ ፡ አቶክም ፡ አምቦች ፡፡

### b. የማረቶች ፡ ግዛት ፡፡

፷፤ ሚልዮን ፡ ሰዎች ፡፡ እርሳቸውም ፡ ጥቂት ፡ ቀርተው ፡ ሁሉ ፡ ለእንግሊዞች ፡ ይገዛሉ ፡ ወይስ ፡ ይገበሬሉ ፡፡

ጶና ፡ ፲፻፻፤ ሰዎች ፡፡ ጶሬንትር ፡ አምባ ፡ የንግሊዞች ፡ ወታደር ፡ ያሉበት ፡፡ ጀግርናት ፡፡ ከዚያ ፡ ታላቅ ፡ መቅደስ ፡ አለ ፡ ለጣዖታቸው ፡፡ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ከሩቅ ፡ መጥተው ፡ ከዚህ ፡ ነፍሳቸውን ፡ ለጣዖት ፡ መሥዋትን ፡ አድርገው ፡ ይገድላ ፡ እንግሊዞች ፡ ዛሬ ፡ ይከለክልዋቸዋል ፡ እንጅ ፡፡

በጶና ፡ በኮል ፡ ያልማስ ፡ ጉድጓደች ፡ አሉ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ኢየፈቃደ ፡ ቈፍሮ ፡ የሚረባባቸው ፡፡

### c. የረስቡቶችና ፡ የጀቶች ፡ ግዛት ፡፡

ተከፍላ ፡ ከንግሊዞች ፡ ተከፍላም ፡ ከማረቶች ፡ በታች ፡ ናት ፡፡

### d. ጎልኮንደ ፡ ፳፤ ወይስ ፡ ፷፤ ሚልዮን ፡ ሰዎች ፡፡

ገዡ ፡ እሥላም ፡ ነው ፡፡ እንግሊዞችም ፡ ከርሶ ፡ ጋሬ ፡ ተሰማሙ ፡ በግዛቱም ፡ ይጠብቁታል ፡ ሸፍጣ ፡ እንዳያደርግ ፡፡ ደህች ፡ መንግሥትም ፡ እጅግ ፡ ባለጠጋ ፡ ናት ፡ በህል ፡ በሩዝም ፡ በጥጥም ፡ በብርብሪም ፡ ባልማስም ፡፡

ሀይድረበድ ፡ ፲፪፻፻፤ ሰዎች ፡ የኒዛም ፡ (ንጉሥ ፡) መናርያ ፡ የተዋበችም ፡ ከተማ ፡፡ ጎልኮንደ ፡ ደህና ፡ ከተማ ፡፡ የደግ ፡ አልማስ ፡ መጀመርያ ፡ ስፍራ ፡፡ አውሬንገበድ ፡ ብርቱ ፡ አገር ፡፡

e. ሌሎችም ፡ ታናሾች ፡ አሕዛብ ፡ አሉ ፡ ከርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ ቀመኞች ፡ ናቸው ፡ እንግሊዞችም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይመትዋቸዋል ፡፡

የከበረ ፡ ፍሬም ፡ እጅግ ፡ ይወጣል ፡ እንደ ፡ ቡን ፡ ሡክር ም ፡ ብርብሪም ፡ ዚንጅብርም ፡ ቅርፊትም ፡ ጫደም ፡ ጥጥ ም ፡ ሙጫም ፡ ሩዝም ፡፡ ዝሆንም ፡ ታላቅ ፡ አባብም ፡ የ ቢሳም ፡ እንስሳም ፡፡ ነሃስም ፡ ብረትም ፡ ወርቅም ፡፡

ባላገሮች ፡፡ ከጪን ፡ ሰዎች ፡ ይሻላሉ ፡፡ አያሌ ፡ ክርስቲ ያንም ፡ በዚች ፡ መንግሥት ፡ ይገኛሉ ፡፡

በኬ ፡ ከተማ ፡ ፶፲፱፡ ሰዎች ፡፡ ፏዩዋም ፡ ፲፱፱፡ ሰዎች ፡፡ ቱሮንና ፡ ሁወሃም ፡ ደህኖች ፡ ገቢዮች ፡፡

### E. የመለካ ፡ ጴኒንሱላ ፡፡

ምድር ፡ እጅግ ፡ ፍርያም ፡ ናት ፡ አልተሰራ.ችም ፡ እንጅ ፡፡ ደህች ፡ ጴኒንሱላም ፡ ተከፍላ ፡ የእንግሊዞች ፡ ተከፍላም ፡ የሆለንድ ፡ ግዛት ፡ ናት ፡፡

መለካ ፡ የሆለንድ ፡ ግዛት ፡ ከተማ ፡ ፲፬፲፱፡ ሰዎች ፡፡

ኳደ ፡ ሊጎርም ፡ ገቢዮች ፡፡

---

## ፫፫፡፡ የህንድ ፡ ደሴቶች ፡፡

### A. ለክደቦች ፡፡

እርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ ታናሾች ፡ ደሴቶች ፡ በሥላም ፡ ንጉ ሥ ፡ በታች ፡ ናቸው ፡፡ ከሌሎችም ፡ የሚበልጡ ፡ ለኮንደ ፡ ጰሪንከጳርም ፡ መትላርም ፡ ናቸው ፡፡

### B. መልደቦች ፡፡

፲፰፲፱፡ ያህል ፡ ታናሾች ፡ ደሴቶች ፡ ናቸው ፡፡ እጅግ ፡ ፍሬ ን ፡ ያፈራ.ሉ ፡ ክሊማ ፡ ግን ፡ ጤና ፡ አይደለም ፡፡ በላገሮች ም ፡ እሥላሞች ፡ ናቸው ፡፡ የንጉሥም ፡ መኖርያ ፡ በማሌ ፡ ደሴት ፡ ነው ፡፡

### C. ስላን ፡፡

፳፫፲፱፡፡ ሚላ ፡ ፩፡ ሚልዮን ፡ ተ፳፱፱፡፡ ሰዎች ፡፡ በጰልክ ም ፡ መንገድ ፡ ከኮሮመንደል ፡ ደርቻ ፡ ተለየች ፡፡ በውሥጥ ም ፡ እጅግ ፡ ደ.ርና ፡ ተራ.ራ. ፡ አለ ፡፡ ክሊማ ፡ መካከለኛና ፡ ጤና ፡ ነው ፡፡ ምድርም ፡ እጅግ ፡ ፍርያም ፡ ናት ፡ ከሌላ ፡ ደ ልቅም ፡ ቅርፈ. ፡ የሚሉትን ፡ የዛፍን ፡ ቅርፍት ፡ ታወጣለ

ች ፡ ለመድኃኒትና ፡ ለመጻፊጫ ፡ የሚጠቀሙውን ፡፡ የ፯፤ አይነትም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የከበረ ፡ ደንጊያ ፡ ደህና ፡ ሉልም ፡ ቀርቅሮም ፡ እርሳስም ፡ ብረትም ፡ ባዜቃም ፡፡ ታላቅ ፡ ዝሆንም ፡ ታላቅ ፡ ዢንጅሮም ፡ ፈረስም ፡ ላምም ፡ ጎሽም ፡ ብሆርም ፡ የቢሳም ፡ እንስሳም ፡ ሀርትም ፡ እርያም ፡ ነብርም ፡ ቀበሮም ፡ ኤዞም ፡ እባብም ፡ ታላቅ ፡ ሸረሪትም ፡፡

ባላገሮች ፡፡ ፪፤ ሚልዮን ፡ ያህላሉ ፡፡ አምልኳቸውም ፡ የቡድሃ ፡ አምልኮ ፡ ነው ፡ ሰይጣንንም ፡ ያከብራሉ ፡፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ ከርሳቸው ፡ ብዙ ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ ተመለሱ ፡፡ የወንጌልም ፡ መልክተኞች ፡ አያሌ ፡ አሉ ፡ የሚያስተምርዋቸው ፡፡ ደች ፡ ደሴትም ፡ ለእንግሊዞች ፡ ትገዛለች ፡፡

ኮሎምቦ ፡ በምዕራብ ፡ ደርቻ ፡፡ የደሴት ፡ ከተማ ፡ ያዛዢም ፡ መናርያ ፡፡ እጅግ ፡ መሻየጥና ፡ መስሪዮች ፡፡

ትሪንኮማሌ ፡ ብርቱ ፡ ከተማ ፡ የጾር ፡ መርከቦችም ፡ መሰብሰቢያ ፡፡

ያፍናጳትናም ፡ ብርቱ ፡ ከተማ ፡፡ የጥጥ ፡ መስሪዮችና ፡ እጅግ ፡ መሻየጥ ፡፡

ካንዲ ፡ የሚስዮን ፡ ስፍራ ፡፡

### D. የአንደማን ፡ ደሴቶች ፡፡

፪፤ ደሴቶች ፡ በበንጋል ፡ ጉበት ፡ የእንግሊዞች ፡ ግዛት ፡፡ ሰዎች ፡ አረዊት ፡ ናቸው ፡፡

ኮርንወሊስ ፡ ከተማ ፡ ደህና ፡ መርስ ፡፡ የበንጋል ፡ ግዛት ፡፡

### E. የኒኮባር ፡ ደሴቶች ፡

እርሳቸውም ፡ በበንጋል ፡ ጉበት ፡ ደገኛሉ ፡ ተከፋለውም ፡ የደንማርክ ፡ ግዛት ፡ ናቸው ፡፡

### F. የሱንደ ፡ ደሴቶች ፡፡

#### a. ሱመትራ ፡፡ ፻፷፯፲፱፤ ሚላ ፡፡

አያሌ ፡ ተራሮች ፡ አሉ ፡፡ ከርሳቸውም ፡ አያሌ ፡ ቡልካኖች ፡ ናቸው ፡፡ ክሊማ ፡ ለፈርንጆች ፡ ጤና ፡ አይደለም ፡፡ ብዙ ፡ ወንዞች ፡ አሉ ፡፡ ምድርም ፡ እጅግ ፡ ፍርያም ፡ ናት ፡፡

ባላገሮች ፡ ፬፤ ወይስ ፡ ፭፤ ሚልዮን ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ወገን ፡፡

አረማውያን ፡ እሥላሞችም ፡ ጥቂት ፡ ክርስቲያንም ፡ ናቸው ፡፡ የደሴትም ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ የሆለንዲ ሶችና ፡ የ እንግሊዞች ፡ ግዛት ፡ ነው ፡፡ አንዲት ፡ ማናንካቦ ፡ የም ትባል ፡ መንግሥትም ፡ ንጉሥዋ ፡ እሥላም ፡ ነው ፡፡ የር ሶ ፡ ከተማ ፡ ጳረንቡንግ ፡ ናት ፡፡ ከዚያ ፡ የጾርን ፡ እቃ ፡ ይሰራሉ ፡፡

ፎርት ፡ ማርልብሮ ፡ የእንግሊዝ ፡ የበንኩሌን ፡ ገዢ ፡ መኖርያ ፡፡

ጳለንባግና ፡ ጳታንግ ፡ የሆለንድ ፡ አገሮች ፡፡

*b.* ያዋ ፡፡ ፳፻፻፤ ሚላ ፡፡ ፬፤ ወይስ ፡ ፭፤ ሚልዮን ፡ ሰዎችም ፡፡

ባላገሮች ፡ እሥላሞች ፡ የጪን ፡ አረማውያንም ፡ ፈረን ጆችም ፡ ናቸው ፡፡ ክሊማ ፡ ጤና ፡ ነው ፡ ምድርም ፡ ፍርያ ም ፡ ናት ፡፡ እጅግ ፡ እህልንና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አታክልትን ፡ ታ ወጣለች ፡፡ መንግሥትም ፡ ለሆለንድ ፡ ንጉሥ ፡ ናት ፡፡

በታቢያ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ የሆለንዲሶችም ፡ ታላቅ ፡ ገቢ ያ ፡፡ ፲፪፻፻፤ ሰዎች ፡ ከርሳቸውም ፡ ፻፻፤ ፈረንጆች ፡፡ አያሌ ፡ ማስተማርዮችና ፡ መስሪዮች ፡፡ እጅግ ፡ መሻየጥም ፡፡ መተሪን ፡ ፹፲፻፤ ሰዎች ፡፡

ከዚህም ፡ ይቀርባሉ ፡ ያዛጀ ፡ ደሴት ፡ የሆለንድ ፡ ግዛ ት ፡ የምትሆን ፡ የመደራ ፡ ደሴትም ፡ ፳፫፻፻፤ ሰዎች ፡፡

G. ቦርኔዎ ፡፡

ከሌሎች ፡ ከእስያ ፡ ደሴቶች ፡ ሁሉ ፡ ትበልጣለች ፡፡ ምድ ር ፡ ደጋ ፡ ናት ፡ አያሌ ፡ ቡልካኖችም ፡ አሉባት ፡ ምድርም ፡ ብ ዙ ፡ ጊዜ ፡ ትናወጣለች ፡፡ ምድርም ፡ የምታወጣ ፡ እጅግ ፡ ነ ው ፡፡ ባላገሮች ፡ ፬፤ ሚልዮን ፡ ያህል ፡ ይሆናሉ ፡፡ እርሳቸው ም ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፡ ለብዙ ፡ ነገሥታትም ፡ ይ ገዛሉ ፡፡ አያሌ ፡ እሥላሞች ፡ አሉ ፡ የቀሩ ፡ ሰዎች ፡ አረማ ውያን ፡ ናቸው ፡፡ ለሆለንድም ፡ ጥቂት ፡ ግዛት ፡ አለች ፡ በ ዚች ፡ ደሴት ፡፡ አያሌም ፡ ከወንጌል ፡ መለክተኞች ፡ ዛሬ ፡ ከዚህ ፡ ያስተምራሉ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ የብዙ ፡ አረማ ውያንን ፡ ልብ ፡ ወደ ፡ ወንጌል ፡ ትምህርት ፡ አዘነበለ ፡ አ ያሌም ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ገቡ ፡፡

ደ ፡ ምቅ ፡ በህንድ ፡ ወደ ፡ ደ ፡ በህንድ ፡ ውቅያኖስና ፡ በፈር
ስ ፡ ጉበት ፡ ወደ ፡ ምብ ፡ በፈርስ ፡ ጉበት ፡ በቱርክያም ፡ በ
ረስያም ፡ ተወሰነች ፡፡ ታላቅነትዋም ፡ ፳፻፱፤ ሚላ ፡ ነው ፡፡

የምድር ፡ ጠባይ ፡፡ ከታላቆች ፡ ተራሮች ፡ የተነሣ ፡ ክ
ሊማ ፡ መካከለኛ ፡ ነው ፡፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ግን ፡ ይተኰሳል ፡፡
የፈርስ ፡ ምድር ፡ በወንዞችና ፡ በባሕሮች ፡ በኵል ፡ እንጅ ፡
ደርቅና ፡ መካን ፡ ናት ፡፡ ታላቆች ፡ ተራሮች ፡፡ ከውከሶስ ፡
ታውረስም ፡ አራራትም ፡ ህዛርደራም ፡ ወይስ ፡ የኀርዲያና
ች ፡ ተራሮች ፡፡ የቢሉርና ፡ የቲቤት ፡ ተራሮች ፡ ክፍልም ፡፡
የምድር ፡ ታላቆች ፡ ባሕሮች ፡፡ የከስጵያ ፡ የዛይራም ፡ የዋ
ደህንድም ፡ የበክተጋንም ፡ የኡርሚያም ፡ ባሕሮች ፡፡ ታላ
ቆች ፡ ወንዞች ፡፡ አራስ ፡ ቤሃድሶም ፡ ሃረትም ፡ ኪሲል
ም ፡ አሰንም ፡ ሲንድም ፡፡

ምድር ፡ የምታወጣ ፡፡ ሀር ፡ ገመልም ፡ ፈረስም ፡ ላም
ም ፡ በግም ፡ አህያም ፡ አንበሳም ፡ ሌሎች ፡ አራዊትም ፡፡
ጥጥም ፡ ወይንም ፡ የከበረም ፡ የዛፍ ፡ ፍሬ ፡ ሽቱም ፡ ለው
ዝም ፡ አፍዩንም ፡ ሙጫም ፡ ተርጰንቲንም ፡ ኢንዲጎም ፡
ሩዝም ፡ ሌላ ፡ እህልም ፡፡ ብረትም ፡ ነሃስም ፡ ነፍታም ፡ ባ
ልሳምም ፡ ጨውም ፡ ሌሎች ፡ ሚነራሎችም ፡፡

የጅ ፡ ስራ ፡፡ የሀር ፡ የወርቅና ፡ የብርም ፡ የለምድም ፡
ልዮ ፡ ልዮ ፡ ስራ ፡ ስጀድም ፡ ታጴቶችም ፡ ብዙ ፡ ሌላ ፡ ስራ
ም ፡፡ መሻየጥ ፡፡ በአርመኖች ፡ በቡካሮችም ፡ በበንያና
ችም ፡ በእንግሊዞችም ፡ በረሶችም ፡ እጅ ፡ ነው ፡፡ የመሻ
የጥ ፡ ደግ ፡ ከተሞች ፡ ተብሪዝ ፡ ረሽትም ፡ አቡሺርም ፡
ናቸው ፡፡

ባላገሮች ፡፡ ፱፤ ሚልዮን ፡ ያህላሉ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ አይነት ፡
ሰዎች ፡፡ የመንግሥት ፡ አምልኮም ፡ እሥላም ፡ ነው ፡ የዓ
ሊ ፡ መንገድ ፡ የሺዮች ፡ ወገንም ፡ ከዓረብና ፡ ከቱርክ ፡ እ
ሥለሞች ፡ የተለዩ ፡፡ ሰቤዎችም ፡ አይሁድም ፡ ጥቂት ፡ ክ
ርስቲያንም ፡ አሉ ፡፡

መከፈል ፡፡ በምሥራቅና ፡ በምዕራብ ፡ ፈርስ ፡፡

ከሻን ፡ ፫፻፻ ሰዎች ፡፡ ከስቢን ፡ ፯፻፻ ሰዎች ፡፡ ቴብሪዝ ፡ ታላቅ ፡ ገቢያ ፡ ፴፲፻ ሰዎች ፡፡ ሺራዝ ፡ ያማረች ፡ ከተማ ፡ ፲፻፻ ሰዎች ፡፡ ለዚች ፡ ከተማም ፡ የቀደም ፡ የጴርሴጶሊስ ፡ ፍራሾች ፡ ይቀርባሉ ፡፡ አቡሺር ፡ በፋርስ ፡ ጉበት ፡ እጅግ ፡ መሻየጥ ፡፡

---

## 5. የዐረብ ፡ ምድር ፡ ወይስ ፡ ዐራቢያ ፡፡

ስ ፡፡ ወ ፡፡ ታት ፡፡ ርት ፡ ፴፪° — ፶፱° ወድ ፡ ፲፪° — ፴፭° ወደ ፡ ሰ ፡ በእስያ ፡ ቱርክያ ፡፡ ወደ ፡ ምብ ፡ በስዌጽ ፡ ኢስትሞስ ፡ አድርጋ ፡ በምሥርና ፡ በኤርትሬ ፡ ባሕር ፡፡ ወደ ፡ ደ ፡ በመንደብ ፡ ደጅ ፡ በዐድን ፡ ባሕርም ፡ በህንድ ፡ ውቅያኖስም ፡፡ ወደ ፡ ምቅ ፤ በፋርስ ፡ ጉበትና ፡ በእስያ ፡ ቱርክያ ፡ ተወሰነች ፡፡ ታላቅነትዋም ፡ ፺፻፻ ሚላ ፡ ነው ፡፡

የምድር ፡ ጠባይ ፡፡ በቈላ ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ ይተኰሳል ፡፡ በደጋና ፡ ወደ ፡ ሰ ፡ በክረምት ፡ ይበርደል ፡፡ ስሙም ፡ የሚባልም ፡ ንፋስ ፡ እጅግ ፡ ይተኰሳልና ፡ ይጐደል ፡፡ ብዙም ፡ ያሸዋ ፡ በረኾች ፡ አሉ ፡፡

ምድር ፡ የምታወጣ ፡፡ ቡን ፡ ሽቱም ፡ ሙጫም ፡ መናም ፡ እህልም ፡ መድኃኒትም ፡ ጥጥም ፡ ሡክርም ፡ ቶምበኾም ፡ ወይንም ፡ በጢኽም ፡ ባሚያም ፡ በትንጀንም ፡ ተምርም ፡፡ ማለፊያ ፡ ፈረስም ፡ አህያም ፡ ገመልም ፡ ላምም ፡ በግም ፡ ነብርም ፡ ጅብም ፡ አንበሳም ፡ ቀበሮም ፡ ዝንጅሮም ፡ ሰጐንም ፡ ሎልመ ፡ የከበረ ፡ ደንጊያም ፡ ብረትም ፡ ነሃስም ፡ መግኔትስም ፡፡

የጅ ፡ ስራና ፡ መሻየጥ ፡ ጥቂት ፡ ነው ፡፡ ታላቅ ፡ ገቢያ ፡ መካ ፡ ነው ፡፡ እሥላሞች ፡ ካለም ፡ ሁሉ ፡ መጥተው ፡ በዚህ ፡ ይሰበሰባሉ ፡ ለመስገድና ፡ ለመሻየጥ ፡፡ ሌሎችም ፡ የመሻየጥ ፡ ስፍሮች ፡ ጅደ ፡ ምኻም ፡ ዐደንም ፡ መከላም ፡ መስከትም ፡ ሳናም ፡ ናቸው ፡፡

ባላገሮች ፡ ፲ ወይስ ፡ ፲፪ ሚልዮን ፡፡ እርሳቸውም ፡ ሁሉ ፡ ጥቂት ፡ ቀርተው ፡ የሐሳዊ ፡ ነቢይን ፡ የሞሀመድን ፡ መንገድ ፡ ይከተላሉ ፡ በ፫ መለየትም ፡ ተለዩ ፡፡ የሱኖች ፡

መለየት ፡ የነቢዩችም ፡ (የዓሊ ፡) ወገንም ፡ የወሃቦች ፡ ወገንም ፡፡

የምድር ፡ መግዛት ፡፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ ዛሬ ፡ ለምሥር ፡ ባሻ ፡ ትገዛለች ፡ እርስዋም ፡ የኤርትራ ፡ ደርቻ ፡ ሁሉ ፡ ሀጃስና ፡ የመን ፡፡ በየመን ፡ ውሥጥም ፡ የሳና ፡ ኢማም ፡ ይገዛል ፡፡ በምሥራቅና ፡ በፋርስ ፡ ጉበት ፡ ደርቻም ፡ የመስከት ፡ ኢማም ፡ ይገዛል ፡፡ ያለዚያም ፡ የዐረብ ፡ ነገዶች ፡ ሁሉ ፡ ለየሽማግሎቻቸው ፡ ይገዛሉ ፡፡

መከፈል ፡፡ በ፮፤ ክፍል ፡ ተከፈለች ፡፡ ፩፤ የሲና ፡ ጴኒንሱላ ፡፡ ፪፤ ሀጃዝ ፡፡ ፫፤ የመን ፡፡ ፬፤ ሀድረመውት ፡፡ ፭፤ ዖማን ፡፡ ፮፤ ነግድ ፡፡

ሳና ፡ የሳና ፡ ከተማ ፡ የኢማምም ፡ መኖርያ ፡፡ ሎሀያ ፡ የመሻየጥ ፡ ስፍራ ፡ መርስም ፡፡ ሆደይደ ፡ ገቢያና ፡ መርስ ፡፡ ምኻ ፡ ደህና ፡ ገቢያ ፡ መርስም ፡ ፲፪፲፪፤ ወይስ ፡ ፲፫፲፪፤ ሰዎች ፡፡ ጅደ ፡ ደህና ፡ ገቢያ ፡፡ አያሌ ፡ መርከቦችም ፡፡ ፹፲፪፤ ሰዎች ፡፡ መካ ፡ የእሥላሞች ፡ መጀመርያ ፡ መቅደስና ፡ መሰብሰቢያ ፡፡ ምናልባት ፡ ፲፪፪፤ ሰዎች ፡፡ ታይፍ ፡ የወሃቦች ፡ መጀመርያ ፡ ስፍራ ፡፡ ጎንፏደ ፡ መርስ ፡፡ የምቦ ፡ መርስ ፡ መዲና ፡ የሞሀመድ ፡ መቃበር ፡፡ አከባ ፡ አምባ ፡ በአከባ ፡ ጉበት ፡፡ ከዚያ ፡ የጴትራ ፡ ታላቆች ፡ ፍራሾች ፡ ይቀርባሉ ፡፡ ቶር ፡ ታናሽ ፡ መንደር ፡ በባሕር ፡ ደር ፡ በሲና ፡ ጴኒንሱላ ፡፡ የሲናና ፡ የሆሬብ ፡ ተራሮች ፡ ከዚህ ፡ ይቀርባሉ ፡፡ ዐደን ፡ በዐደን ፡ ጉበት ፡ ብርቱ ፡ ስፍራ ፡ የእንግሊዞች ፡ ግዛት ፡፡ ሁለት ፡ መርሶች ፡፡ መከላ ፡ መርስ ፡፡ መስከት ፡ የመስከት ፡ ከተማ ፡፡ ዝቢድ ፡ ታላቅ ፡ ማስተማርያ ፡ ወደለ ፡ በሆደይደና ፡ በምኻ ፡ መኻከል ፡፡ ታድሞር ፡ በሶርያ ፡ ውድማ ፡ የከበሩ ፡ ፍራሾች ፡ ከቀደሞች ፡ ከጸልሚራ ፡ ከተማ ፡፡

---

## 6. የእስያ ፡ ቱርክያ ፡፡

ስ፡፡ ወ፡፡ ታት፡፡ ርት ፡ ፳፯°፤ — ፵°፡፡ ወድ ፡ ፴°፤ — ፵፪°፡፡ ወደ ፡ ምቅ ፡ በፋርስ ፡ መንግሥት ፡፡ ወደ ፡ ደ ፡ በዐረብ ፡ ምድርና ፡

## B. ከረማኒያ ::

በኮኒያና ፡ በአደና ፡ ትከፈላለች ::

ኮኒያ ፡ የቀደም ፡ ኢቆኒዩም ፡ ፲፰፲፻፡ ሰዎች :: አያሌ ፡ መስሪዮች :: ደህና ፡ ገቢያ :: ቂሣርያ ፡ የረም ፡ ሜትሮጶሊታን ፡ መቀመጫ :: ተርሱስ ፡ ወይስ ፡ ጠርሴስ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ወደ ፡ ተወለደበት :: ዛሬ ፡ ታናሽ ፡ መንደር ፡ ናት :: አደና ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ::

## C. አምሳን ::

በጥቁር ፡ ባሕር ፡ የ፪፡ ባሾች ፡ ግዛት ፡ በሲዋስና ፡ በትሬብዙንት ፡ የሚኖሩ ::

ሲዋስ ፡ የቀደም ፡ ጶንጦስ ፡ የባሻና ፡ የረም ፡ ሜትሮጶሊታን ፡ መቀመጫ ::

ቶከት ፡ መስሪዮች :: እጅግ ፡ መሻየጥ :: ፬፻፻፡ ሰዎች ::

ትሬብዙንት ፡ ታላቅ ፡ ገቢያ ፡ በጥቁር ፡ ባሕር :: ፯፻፻፡ ሰዎች ::

## D. መሬሽ ::

መሬሽ ፡ የባሻ ፡ መኖርያ :: መላጥያ ፡ የረም ፡ ሜትሮጶሊታን ፡ መቀመጫ ::

አያሌ ፡ ደሴቶችም ፡ ወደዚህ ፡ ይገባሉ :: እርሳቸውም ፡ እሌህ ::

*a.* የገዦች ፡ ፱፡ ደሴቶች ፡ በስተምቡል ፡ አንጻር ::

*b.* በረም ፡ አርኪጴለጎስም ፡ እሌህ ፡ ደሴቶች ፡ የቱርኮች ፡ ግዛት ፡ ሁነው ፡ ይገኛሉ :: ቴኔደስ :: ሚቲሌኔም :: ኪዮስም ፡ ታላቅ ፡ ደሴት ፡ ፲፫፻፻፡ ሰዎች :: ከተማም ፡ ኪዮስ ፡ ትባላለች ፡ ፬፻፻፡ ሰዎች ፡ ያሉባት :: ደህና ፡ ገቢያ :: የረም ፡ ሜትሮጶሊታንም ፡ መቀመጫ :: ሳሞስ ፡ ደሴት ፡ ፶፲፻፡ ሰዎች :: እጅግ ፡ ወይን :: ኮስ :: ጳጥሞስ ፡ ደሴት ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ የነበረባት ፡ ራእዩን ፡ ሲጽፍ :: ሮደስ ፡ በመካከለኛ ፡ ባሕር :: ፬፻፻፡ ሰዎች :: ቆጵሮስ ፡ ፴፻፻፡ ሰዎች :: ኒኮስያ ፡ ከተማ ፡ የረም ፡ ሜትሮጶሊታንም ፡ መቀመጫ ::

፪፪፡፡ ቱርኮመኒያ ፡ ወይስ ፡ የቱርኮች ፡ አርሜኒያ ፡፡

አርዝሩም ፡ በኤፍራጥስ ፡ ምንጭ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ፲፻፻፡ ሰዎች ፡፡ የባሻ ፡ መኖርያ ፡ የአርመን ፡ ሜትሮጶሊታንም ፡ መቀመጫ ፡፡ ደህና ፡ ገቢያ ፡፡

በየጸት ፡ ፲፳፲፻፡ ሰዎች ፡፡ ከርስ ፡ ብርቱ ፡ አምባ ፡ ሩሶች ፡ የወሰዱት ፡ ዛሬ ፡ ፲፫፡ አመት ፡፡

፫፫፡፡ የቱርኮች ፡ ጊዎርጊያ ፡፡

ዛሬ ፡ የሩሶች ፡ ግዛት ፡ ነው ፡፡ አኽልጺክ ፡ ብርቱ ፡ ከተማ ፡፡

፬፬፡፡ ኩርዲስታን ፡፡

የኩርዶች ፡ ምድር ፡ እርሳቸውም ፡ ቀመኞች ፡ ናቸው ፡፡

፭፭፡፡ ኢራክ ፡ ዐረቢ ፡፡

የቀድም ፡ ባቢሎንና ፡ የከለደውያን ፡ ምድር ፡፡

ባግደድ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ በጤግርስ ፡ ወንዝ ፡፡ የባሻ ፡ መኖርያ ፡፡ እጅግ ፡ መሻየጥና ፡ መስሪዮች ፡፡ ሀላ ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡፡ የባቢሎን ፡ ፍራሾች ፡ ለዚች ፡ አገር ፡ ይቀርባሉ ፡፡

መጅድ ፡ ሁሰይን ፡ የእሥላሞች ፡ መቅደስ ፡፡ ሁሰይን ፡ የሙሀመድ ፡ አማች ፡ የዓሊ ፡ ልጅ ፡ ከዚህ ፡ ተቀብርዋልና ፡፡

በሶሪ ፡ በሻትኽልዐረብ ፡ ደር ፡፡ ፭፻፻፡ ሰዎች ፡፡ እጅግ ፡ መሻየጥ ፡፡

መርዲን ፡ በታላቅ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡፡ የነስቶርዮስ ፡ ወገን ፡ የኤጲስቆጶሳቸው ፡ መኖርያ ፡፡

፮፮፡፡ አልጀዚራ ፡፡

በኤፍራጥስና ፡ በጤግርስ ፡ መካከል ፡፡ በሴጀር ፡ ተራሮችም ፡ ላይ ፡ የየዚዶች ፡ ወገን ፡ ሰይጣንን ፡ የሚያመልኩ ፡ ይቀመጣሉ ፡፡

ዲያርብክር ፡ ከተማ ፡ ፲፻፻፡ ሰዎች ፡፡ ከርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ ክርስቲያን ፡፡ ብዙ ፡ መስሪዮችም ፡ እጅግ ፡ መሻየጥም ፡፡

ሞሱል ፡ ብርቱ ፡ ከተማ ፡ ፮፻፻፡ ሰዎች ፡፡ የነስቶርያኖ

ሬጵምግት ፡ ዘንድ ። ከድምሳሴ ፡ ውኃ ፡ የደነች ፡ ትውል
ድ ፡ የኖህ ፡ የልጆቹ ፡ ልጆች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ረስተው ፡ ጣ
ዖታትን ፡ ባመለኩ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብርሃምንና ፡
ዘሩን ፡ መረጸ ፡ ለርሳቸውም ፡ ይህችን ፡ ምድር ፡ ርስት ፡ አ
ድርጊት ፡ ሰጣቸው ። የከናዐናውያንንም ፡ አሕዛብ ፡ ስለ ፡
ኃጢአታቸው ፡ በእሥራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ አወጣ ። እግ
ዚአብሔርም ፡ ራሱን ፡ አዋረደ ፡ ለእሥራኤል ፡ ልጆችም ፡ ን
ጉሥ ፡ ሆነላቸው ፡ እርሳቸውንም ፡ ሕዝቡንና ፡ ርስቱን ፡ አ
ደረጋቸው ። በሙሴና ፡ በነቢያቱም ፡ አፍ ፡ ተናገራቸው ፡ ሕ
ጉንም ፡ ሥርዓቱንም ፡ ሰጣቸው ፡ የምድኃኒቱንም ፡ ተስፋ ፡
አስደረገላቸው ፡ በብዙ ፡ ተአምራትና ፡ በምልክት ፡ በመሥ
ዋዕትም ፡ በምሳሌም ፡ አጸናላቸው ። የሕዝቡንም ፡ ኃጢ
አት ፡ ታገሠ ፡ እጅግ ፡ ሲፈትኑት ፡ ሲያስቈጡትም ፡ ባለማ
መናቸው ፡ ባለመታዘዛቸውም ፡ ጣዖታትንም ፡ በማምለካ
ቸው ። የኃጢአታቸው ፡ ሚዛንም ፡ በመላ ፡ ጊዜ ፡ አረማ
ውያንን ፡ አስመጣባቸው ፡ ማርከው ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ የ
ወሰድዋቸው ። ከዚያም ፡ ፸፡ አመት ፡ ከተቀመጡ ፡ በኋ
ላ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዘነላቸው ፡ ወደ ፡ አገራቸውም ፡ መለ
ሳቸው ። ከዚያም ፡ የሩሳሌምን ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ሠሩ ፡ መ
ቅደሳቸውንም ፡ አገራቸውንም ። ከዚያ ፡ ዘመንም ፡ ጀምሮ
ረው ፡ ከፋርስ ፡ ከመቄዶንያም ፡ ከሶርያም ፡ ከምሥርም ፡
ነገሥታት ፡ በታች ፡ ሆኑ ፡ መቀባውያን ፡ እስኪነሡ ፡ ድረስ ።
እርሳቸውም ፡ የንግደችን ፡ ቀምበር ፡ አፈረሱ ፡ ከልጆቻቸ
ውም ፡ ነገሥታት ፡ ሆኑላቸው ። አይሁድ ፡ ግን ፡ ለውነተኛ ፡
ንጉሣቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ባልተገዙ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ አ
ሳልፎ ፡ በሮማውያን ፡ እጅ ፡ ሰጣቸው ። ሮማውያንም ፡ ሀ
ሮድስን ፡ አነገሡ ፡ በላያቸው ። አይሁድም ፡ የዚያን ፡ ጊ
ዜ ፡ በመንፈሳዊት ፡ ጨለማ ፡ ተቀመጡ ። የእግዚአብሔር
ን ፡ ሕግ ፡ ፊደሉን ፡ ሲጠብቁት ፡ ያለቆቻቸውንም ፡ ቃል ፡ ሲ
ጨምሩለት ፡ መንፈሱን ፡ ጥላው ፡ አፈረሱት ። የሕዝቡ
ም ፡ መምህራን ፡ እርሳቸውም ፡ ፈሪሳውያንና ፡ ጻፎች ፡ ለ
ራሳቸው ፡ እውራን ፡ ነበሩ ፡ ስለዚህ ፡ ለውራን ፡ መሮች ፡
ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ተሳኑ ፡ ሁለታቸው ፡ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ ሳይወ

ድቁ ፡፡ እግዚአብሔርንም ፡ በውነት ፡ ፈርተው ፡ ያለምን ፡
መድኃኒት ፡ ተስፈ ፡ የጠበቁ ፡ ጥቂት ፡ ነበሩ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜ
ንም ፡ እግዚአብሔር ፡ አንዱን ፡ የተወደደውን ፡ ልጁን ፡ ሰ
ደደ ፡ እርሱም ፡ በቤተልሔም ፡ ከማርያም ፡ ድንግል ፡ ተወ
ለደ ፡ በቀደም ፡ እንደ ፡ ተነበየ ፡ በነቢያት ፡፡ በብዙ ፡ ምሳ
ሌም ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ እንደ ፡ ተሣለ ፡ እንደ ፡ ተመሰለ
ም ፡ እንዲሁም ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በትምህርቱ ፡ በተአም
ራቱም ፡ በስራውም ፡ ሁሉ ፡ በሕማማቱም ፡ በሞቱም ፡ በትን
ሣኤውም ፡ የመድኃኒታችነን ፡ ስራ ፡ ሰራ ፡፡ አሥራ ፡ ሁለ
ቱንም ፡ ሐዋርያቱን ፡ ላከ ፡ በዓለም ፡ ሁሉ ፡ የሕማማቱንና ፡
የትንሣኤውን ፡ ወንጌል ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡፡ መንፈሱን
ም ፡ በታላቅ ፡ ልክ ፡ ሰጣቸው ፡ በተአምራት ፡ በኃይልም ፡
በጥበብም ፡ በሃይማኖትም ፡ መላቸው ፡፡ እርሳቸውም ፡ ለ
ክርስቶስ ፡ ስም ፡ መመስከራቸውን ፡ በየሩሳሌም ፡ ጀመ
ሩ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ ምስክራቸውን ፡ ባረከ ፡ ብዙ ፡ ሺህ
ንም ፡ ካይሁድ ፡ ወገን ፡ ለሃይማኖት ፡ አስገዛ ፡፡ እንዲሁም ፡
የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ እርስዋም ፡ በውነት ፡ በየሱ
ስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚያምኑ ፡ ጉባኤ ፡ የምትሆን ፡ በየሩሳ
ሌም ፡ ጀመረች ፡፡ በጅግ ፡ መከራና ፡ በስደትም ፡ በይሁደና ፡ በ
ሰማርያ ፡ በገሊላ ፡ አገርም ፡ ተዘረጋች ፡፡ ከዚያም ፡ በሐዋር
ያት ፡ ሰብከት ፡ ወጣች ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ አሕዛብም ፡ ደረሰ
ች ፡፡ ያይሁድ ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ ባመፃቸውና ፡ በጸላትነታቸው ፡ ኑ
ረው ፡ የተሰበከላቸውን ፡ መድኃኒት ፡ ንቀዋልና ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ከፊቱ ፡ ጣላቸው ፡፡ የሮሚያ ፡ ሥራዊትም ፡ የሩሳሌ
ምን ፡ አፈረሱ ፡ ከልደት ፡ ወዲህ ፡ በ፸፤ አመት ፡፡ አይሁድ
ም ፡ ባሕዛብ ፡ መኻከል ፡ ሁሉ ፡ ተበተኑ ፡፡ ከዚያ ፡ ዘመን
ም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያይሁድ ፡ ምድር ፡ የል
ዩ ፡ ልዩ ፡ ሕዝብ ፡ ግዛት ፡ ሆነች ፡፡ በሮምያ ፡ ቄሣሮች ፡ ዘመ
ን ፡ ኤልያ ፡ ከጲቶሊና ፡ የተባለች ፡ አገር ፡ በየሩሳሌም ፡ ስ
ፍራ ፡ ተሠራች ፡ አይሁድና ፡ ክርስቲያንም ፡ ተቃመጡባት ፡፡
በሀድርያኖስ ፡ ዘምን ፡ ግን ፡ በርኮኽባ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሐሳ
ዊ ፡ መሢሕ ፡ ተነሣ ፡፡ ካይሁድም ፡ ብዙ ፡ አእላፍን ፡ አስ
ቶ ፡ ክርስቲያንን ፡ አሳደደ ፡ በቄሣር ፡ ላይም ፡ ተነሣ ፡፡ ቄ

ሣር ፡ ሀድርያን ፡ ግን ፡ ተዋግው ፡ መታውም ፡ ብዙ ፡ አይሁድም ፡ ሞቱ ፡፡ የቀረም ፡ ለብርቱ ፡ ባርነት ፡ ተማረኩ ፡፡ በቆንስታንቲኖስ ፡ ዘመንም ፡ የሩሳሌምና ፡ ግዛትዋ ፡ ከበቀደም ፡ ከበረች ፡ የቄሣር ፡ እናት ፡ ሄሌና ፡ ወደ ፡ ያ ፡ በሔደች ፡ ጊዜ ፡ በወንጌል ፡ የታወቀውን ፡ ስፍራ ፡ ለማየት ፡፡ እርስዋም ፡ በየሩሳሌም ፡ ስትሆን ፡ የጌታውን ፡ መቃብር ፡ ያገኘች ፡ የጌታውንም ፡ መስቀል ፡ ያወጣች ፡ ትባላለች ፡፡ ደረ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ይዘው ፡ ስፍራውንም ፡ አይተው ፡ በጣም ፡ የመረመሩት ፡ የዚህ ፡ ነገርን ፡ እውነት ፡ ይጠራጠራሉ ፡፡ ከዚያ ፡ ዘመንም ፡ ጀምሮ ፡ ብዙ ፡ ክርስቲያን ፡ ከቅርብና ፡ ከሩቅ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ሔዱ ፡ የክርስቶስን ፡ መቃብር ፡ ለማየት ፡፡ በኒቅያ ፡ ሲኖደስም ፡ የየሩሳሌም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ሆነ ፡፡ አያሌ ፡ አመትም ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ለቅዱስ ፡ መቃብር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሠራች ፡፡ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ ቄሣር ፡ ዩልያኖስ ፡ ከሐዲ ፡ ሃይማኖትን ፡ የካደ ፡ የክርስቲያን ፡ ነገር ፡ ለመጉደት ፡ ብሎ ፡ ካይሁድ ፡ ጋራ ፡ ወደጅነት ፡ አደረገ ፡ በየሩሳሌምም ፡ አሰበሰባቸው ፡ ብርንም ፡ ሰራተኞችንም ፡ ሰጣቸው ፡ የቀደሙን ፡ የሰሎሞንን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሮማውያን ፡ ያፈረሱትን ፡ መልሰው ፡ ይሠሩት ፡ ዘንድ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ከለከላቸው ፡፡ ሰራተኞች ፡ የቤተ ፡ መቅደስን ፡ መሠረት ፡ በማሱ ፡ ጊዜ ፡ ምድር ፡ ተናውጣለችና ፡ እሳትም ፡ ከምድር ፡ ወጣ ፡ የሚያስፈራቸው ፡ ስራቸውንም ፡ አስተዋቸው ፡፡ አንድ ፡ አመትም ፡ በኋላ ፡ ዩልያኖስ ፡ በፈርስ ፡ ለይ ፡ ባደረገ ፡ ዘምቻ ፡ ሞተ ፡፡ በሞቱም ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ከጸላትዋ ፡ እጅ ፡ አደነ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ክርስቲያን ፡ በቍጥር ፡ ባለማዊ ፡ ሸልምም ፡ በክብርም ፡ በሥጋዊት ፡ ደህንነትም ፡ በበዙ ፡ ጊዜ ፡ ባይነተኛ ፡ በመንፈሳዊት ፡ ደህንነታቸው ፡ ተጐዱ ፡፡ እጅግ ፡ ፀብና ፡ መለየት ፡ ተነሣች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ከሰው ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ መደብለቅ ፡ ጀምረዋልና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አለቆች ፡ ክብራቸውን ፡ እሹ ፡ ከጌታቸው ፡ ክብርና ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደህንነት ፡ ይልቅ ፡፡ እንዲሁም ፡ አይነተኛ ፡ ባፉ ፡ ብቻ ፡ ያልሆነች ፡ በልብ ፡ እንጅ ፡ ያለ

ች ፡ ሃይማኖት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ጠፋች ፡ ፍቅርም ፡
በብዙ ፡ ክርስቲያን ፡ ልብ ፡ በረደ ። ጌታችን ፡ ግን ፡ ቅናተኛ ፡
ነውና ፡ ወገኖቹ ፡ ለርሱ ፡ ብቻ ፡ የሚገባውን ፡ ክብር ፡ ለራሳ
ቸው ፡ ወይስ ፡ ለሌላ ፡ ፍጥረት ፡ ቢሰጡ ፡ ይቈጣል ። እንደ
ሁም ፡ በዚህ ፡ ሆነ ። እግዚአብሔር ፡ በቍጣው ፡ ብርቱን ፡
መቅሠፍትን ፡ አስመጣ ፡ በቤቱ ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ
ም ፡ አላስወገደውም ። ይህ ፡ መቅሠፍትም ፡ ያሰተኛ ፡ ነቢ
ይ ፡ የሙሀመድ ፡ መግዛት ፡ ነው ። የሙሀመድ ፡ ወገን ፡ በ
ልደት ፡ አመት ፡ ፮፻፳፪፤ ሙሀመድ ፡ በሞተበት ፡ አመት ፡
ወደ ፡ ሶርያ ፡ ገቡ ። ክርስቲያንም ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከለል
ባቸው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በተመለሱ ፡ እርሳቸው ፡ በ
እሥላሞች ፡ በአቡብክርና ፡ በዕምር ፡ ኃይል ፡ ድል ፡ በነ
ሡ ። ቂሮስ ፡ ግን ፡ የየሩሳሌም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ባመት ፡
፮፻፴፱፤ ለዕምር ፡ ብርን ፡ ሰጠ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ እንደይገ
ባ ። እሥላሞችም ፡ ፫፤ አመት ፡ ቈይተው ፡ ተመለሱ ፡ ገቡ
ም ፡ የሰሎሞንም ፡ ሀይከል ፡ በቀደም ፡ በነበረበት ፡ ስፍራ ፡
ላሰተኛ ፡ አምልኳቸው ፡ መቅደስን ፡ ሠሩ ። ጰለስቲናንና ፡
ሶርያን ፡ ሁሉን ፡ ገዙ ። ገናም ፡ የክርስቲያን ፡ ብዛት ፡ ዓይ
ናቸውን ፡ አልከፈቱም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ አልተመ
ለሱም ፡ ልባቸው ፡ ደንድንዋልና ። ስለዚህም ፡ የእሥላሞ
ች ፡ ኃይልና ፡ ግዛት ፡ በዛ ፡ በሩምም ፡ መንግሥት ፡ በፋርስ
ም ፡ በምሥርም ፡ በአፍሪቃም ፡ በስጳኒያም ፡ በሲቄልያ
ም ፡ ተዘረጉ ። ወደ ፡ ፈረንኮችም ፡ ምድር ፡ ገቡ ፡ ደሩ ፡
በጽዋቴ ፡ አገር ፡ ተመቱ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ ኃይላቸው ፡
በምዕራብ ፡ በጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ጐደለች ። በሩም ፡ መን
ግሥት ፡ ግን ፡ ግዛታቸው ፡ በዛች ። ባመት ፡ ፲፻፺፱፤ አንድ ፡
ባሕታዊ ፡ ስሙን ፡ ጴጥሮስ ፡ የሚሉት ፡ ከየሩሳሌም ፡ ወደ ፡
ሮሚያ ፡ መጣ ፡ ከጳጳስ ፡ እጅም ፡ ረዴትን ፡ ለመነ ፡ በየሩ
ሳሌም ፡ ለሚቀመጡ ፡ ወዲያም ፡ ለሚሔዱ ፡ ክርስቲያን ፡
ከሥላሞች ፡ እጅ ፡ ያድናቸው ፡ ዘንድ ። ኡርባን ፡ ሁለተኛ
ም ፡ የሮሚያ ፡ ጳጳስ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሲኖደስን ፡ ሰበሰበ ፡
የመስቀልንም ፡ ዘምቻ ፡ በሥላሞች ፡ ላይ ፡ አዘዘ ። ሰደፍ
ንም ፡ መምዘዝ ፡ የሚችል ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ የሩ

ሳሌም ፡ ሊሔድ ፡ ነበረ ፡፡ ያልሔደም ፡ ብርን ፡ ሊሰጥ ፡ ነበ
ር ፡፡ የሔደውንም ፡ ሁሉን ፡ ከኃጢአቱ ፡ ሁሉ ፡ ፈታው ፡፡ የዚ
ያን ፡ ጊዜም ፡ ብዙ ፡ አእላፋት ፡ ተሰበሰበው ፡ የመስቀል
ን ፡ ጦር ፡ ለመዋጋት ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ሔደ ፡፡ ከርሳቸው
ም ፡ ብዙ ፡ ከሞቱ ፡ እጅግ ፡ ደምም ፡ ከፈሰሰ ፡ በኋላ ፡ ጎት
ፍሬድ ፡ የሚሉት ፡ ከቡልዮን ፡ አገር ፡ የሩሳሌምን ፡ ከሥላ
ሞች ፡ እጅ ፡ ወሰደ ፡ ከዚያም ፡ ነገሠ ፡፡ ባመትም ፡ ፲፩፻፹፯፤ ሣ
ህለደን ፡ የሚባል ፡ የሥላሞች ፡ ንጉሥ ፡ አገሪን ፡ ከክርስቲያ
ን ፡ እጅ ፡ ወሰደ ፡፡ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ ፍርንጆች ፡ ደግሞ ፡ አን
ድ ፡ ጊዜ ፡ ገብተው ፡ ለጥቂት ፡ ዘመን ፡ ገዝዋት ፡ እሥላሞች
ም ፡ ደግሞ ፡ አወጥዋቸው ፡፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስም ፡ ጰለስቲና
ና ፡ የሩሳሌም ፡ የእሥላሞች ፡ ግዛት ፡ ናቸው ፡፡ የክርስቲያ
ን ፡ አይነትም ፡ ሁሉ ፡ አይሁድም ፡ ወትሩ ፡ ወደዚያ ፡ ይሔደ
ሉ ፡፡ አይሁድም ፡ ያለፈችን ፡ ምስጋናቸውን ፡ ያለቅሱ ፡ ዘ
ንድ ፡ የሚመጣውንም ፡ መሢሓቸውን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ለ
መሔደቸው ፡ መክንያትን ፡ ያደርጋሉ ፡፡ ክርስቲያንም ፡ ቢሔ
ዱ ፡ መክንያታቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ ስ
ራ ፡ የሆነበትን ፡ ክርስቶስም ፡ በሥጋ ፡ የነበረበትን ፡ ነፍሳችነን
ም ፡ ያደነበትን ፡ ስፍራ ፡ ያዩ ፡ ዘንድ ፡፡ ይህም ፡ ብቻ ፡ ቢሆን ፡
እግዚአብሔርንም ፡ በመሔደቸው ፡ በመኖሪቸውም ፡ ቢያ
መሰግኑ ፡ ሌላውንም ፡ ነገር ፡ ባይሹ ፡ ደህና ፡ የሚገባም ፡ ነው ፡፡
ደሩ ፡ ከሚሔዱ ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ አድርገው ፡ የሚሔዱ ፡
ጥቂት ፡ ናቸው ፡፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ከሚሔዱ ፡ ብዙ ፡ አ
ሉ ፡ የነፍሳቸውን ፡ ደህንነት ፡ ባገሬቸው ፡ ያላገኙዋትን ፡ ለ
መኘት ፡ የሚሔዱ ፡፡ እርሳቸውም ፡ በከንቱ ፡ ይሔደሉ ፡ ነ
ፍሳቸው ፡ ባትለወጥ ፡፡ ዓለምን ፡ ሁሉን ፡ የሚመላውን ፡
እግዚአብሔርን ፡ በቤቱ ፡ ያላገኘው ፡ በዓለም ፡ ሁሉ ፡ አያ
ገኘውምና ፡፡ እግዚአብሔርንም ፡ ያገኘ ፡ ሁሉ ፡ በየሩሶሌ
ም ፡ ተሰቅሎ ፡ የሞተውንም ፡ የተነሣውንም ፡ ክርስቶስን ፡
አገኘ ፡ ይህም ፡ ከየሩሳሌም ፡ ከዓለምም ፡ ሁሉ ፡ ይሻላ
ል ፡፡ ያለርሱም ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ መሔድ ፡ ያለ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ እንደ ፡ ተሰራ ፡ ስራ ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ ነው ፡፡ እንዲሁ
ም ፡ የሔደ ፡ ሲመለስ ፡ ከበፊት ፡ ካልሔደ ፡ ይከፋል ፡፡

በጳለስቲናም ፡ የከበሩ ፡ ቦቶች ፡ እሌህ ፡ ናቸው ።

የሩሳሌም ፡ ከተማ ፡ ስምዋ ፡ በዐረብ ፡ ቋንቋ ፡ ቁዱስ ፡ ይባላል ። ባያሌ ፡ ኮረፍቶች ፡ ላይ ፡ ተሠራች ። ፷፲፻፤ ሰዎች ። ከርሳቸውም ፡ ፳፲፻፤ ወይስ ፡ ፯፲፻፤ አይሁድ ፡ ፯፲፻፤ ክርስቲያ ንም ፡ የቀሩም ፡ እሥላሞች ፡ ናቸው ። በጽዮን ፡ ተራራ ፡ ላ ይ ፡ ተሠርቶ ፡ የዳዊት ፡ አምባ ፡ የሚባል ፡ የፈረንጆች ፡ ስራ ፡ ሁኖ ፡ ይመስላል ። የቅዱስ ፡ መቃበርም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያ ን ። የመቃበርና ፡ የመስቀል ፡ ስፍራ ፡ ግን ፡ የተሳሳተ ፡ ይመ ስላል ፡ አይነተኛ ፡ ስፍራቸውም ፡ አልታወቀም ። ክርስቶስ ፡ ከከተማ ፡ በሜዳ ፡ ተሰቅሎ ፡ ሙትዋልና ፡ የመቃበር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስፍራ ፡ ግን ፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ በውሥጥ ፡ ነበ ር ። በዚያች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ የሩሞች ፡ የፈረንጆች ም ፡ የአርመኖችም ፡ የግብጾችም ፡ የሀበሻ ፡ ሰዎችም ፡ ገደ ሞች ፡ በያጠገብዋ ፡ አሉ ። ብዙ ፡ ሌሎችም ፡ ገደሞች ፡ በከ ተማ ፡ አሉ ። አያሌም ፡ ከወንጌል ፡ መለክተኞች ፡ አሉ ። ዛ ሬም ፡ አንዲት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለጵሮትስታንቶች ፡ ት ሠራለች ። ሀራም ፡ ሸሪፍ ፡ በዕምር ፡ የተሠራች ፡ የሥላሞ ች ፡ የከበረች ፡ መስጊድ ፡ የሰሎሞን ፡ ሀይከል ፡ በነበረ ፡ ስ ፍራ ፡ በሞሪያ ፡ ኮረፍታ ፡ ላይ ። የሂኖም ፡ ቈላ ፡ የኪድሮን ም ፡ ወንዝ ፡ የዮሳፍጥም ፡ ቈላ ፡ የሰሊሆምም ፡ መጠመቅ ያ ፡ ጌትሴማኔም ፡ ደብረ ፡ዘይትም ፡ የነገሥታትና ፡ የመሳፍን ትም ፡ መቃበሮች ፡ የአቢሰሎም ፡ ሃወልትም ፡ በከተማ ፡ ዙ ርያ ፡ ይገኛሉ ። በደብረ ፡ ዘይትም ፡ በምሥራቅ ፡ አጠገቡ ፡ ቢታኒያ ፡ አለች ፡ ጌታችን ፡ አልዓዛርን ፡ ወደስነሣው ። ያን ድ ፡ ቀን ፡ መንገድም ፡ ከየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ የሪ ኮና ፡ የሎጥ ፡ ባሕር ፡ አሉ ።

ቤተልሔም ፡ የዳዊት ፡ አገር ፡ ጌታችን ፡ ወዩ ፡ ተወለደ በት ፡ በኮረፍታ ፡ ላይ ፡ ነው ። ከዚያ ፡ ፪፤ ታላቆች ፡ ገደሞች ፡ አሉ ። ሰሎሞንም ፡ ወይስ ፡ ኅዝቅያስ ፡ የሰራቸው ፡ ፫፤ መ ጠመቅዮች ፡ አሉ ፡ ውኃቸውን ፡ ባገደ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ና ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ የሚሰዱ ። ሄብሮን ፡ ፪፻፻፤ ሰዎች ፡ የወደን ፡ ስፍራ ።

የሪኮ ፡ ዛሬ ፡ ታናሽ ፡ መንደር ፡ ናት ፡ አንድ ፡ አሮጌ ፡ የፊ

ረሰም : አማጣ : ወደ ለ :: የኤልሳ : ምንጭ : ቅርብ : ነው ::
የሲቲምም : ሚደ : ይቀርባል : ሰደምና : ገሞሬ : በቀደም :
በእግዚአብሔር : ፍርድ : ስለ : ኃጢአታቸው : ወደ : ጠፉ ::
ዛሬም : ታላቅ : ባሕር : ከዚያ : ይቆማል : ውኃውም : መ
ራራና : ጨው : ነው : ይከብደልም :: የዮርደኖስ : ወንዝም :
ወደዚህ : ባሕር : ገብቶ : ይቆማል ::

ያፋ : በመኻከለኛ : ባሕር : ደር :: መርስ :: ደህና : ገቢያ ::
ልድ : ጴጥሮስ : ኤኔያስን : ወደ : ፈወሰ ::

ረምላ : ፮፡ ገደሎች :: ጋዛ : ከያፋ : ወደ : ደቡብ :: የወደ
ሬ : ደር : ከዚያ : አለ ::

ናብሉስ : የድሮ : ሲኬምና : ሲካር : በቊላ : በዔባልና :
በገሪጺም : ተራሮች : መኻከል : ደህና : ስፍራ :: አያሌ : ሰ
ምሬውያን : ከዚህ : ይገኛሉ :: ሴበስቴ : የቀደም : ሰ
ማርያ ::

የእስድሬሎም : ሜደ :: ታላቅና : ፍርያም : ናት :: የኪ
ሶን : ወንዝ : በከርመል : እግር : በምዕራብ : ወገንዋ : ያል
ፍባታል : ከርመልንም : ዞሮ : ወደ : መኻከለኛ : ባሕር : ይ
ገባል :: በዚች : ሜደም : በቀደም : ይዝረዔል : ዔይንደር
ም : ናይንም : ነበሩ :: የታቦር : ተራራም : በሰሜን : አጠገ
ብዋ : ነው ::

ናዝሬት : ጌታችን : ባሽክርነቱ : ወደ : ተቀመጠ : ደህና :
አገር : በተራራ : ላይ :: ያመረች : ቤተ : ክርስቲያን ::

የዮርደኖስ : ወንዝ : ምንጩ : በሆር : ተራራ : ላይ : ነ
ው : እርሱም : ደግሞ : አንቲሊበኖስ : በሚባል :: ከምን
ጩ : ጥቂት : ወርደ : በታናሽ : በሜሮም : ባሕር : መኻከል :
ያልፋል :: ከዚያም : በኋላ : ወደ : ቈላ : ሲገባ : በጌኔዛሬ
ጥ : ወይስ : ጥብርያደስ : ባሕር : መኻከል : ያልፋል :: ከዚ
ያም : ሲወጣ : በቀና : መንገድ : ወደ : ደቡብ : ይሔደል :
ወደ : ሎጥ : ባሕር : ገብቶ : እስቲያልቅ : ድረስ ::

የጌኔዛሬጥ : ባሕር :: እርሱም : በመጽሐፍ : ቅዱስ :
የኪነረት : የጥብርያደስም : የገሊላም : ባሕር : ተባለ :: ር
ዝመቱ : ፲፡ ሚላ : ወርዱም : ፮፡ ሚላ : ያህላል :: ከዚያ
ም : በቀደም : ጥብርያደስ : ቅፍርናሆምም : ቤተሰይደም :

ሀማደላም ፡ ፻፤ ፡ ከተሞች ፡ አገርም ፡ በዙርያው ፡ ነበረ ። የክርስቶስ ፡ ነገርም ፡ ስራውም ፡ ታአምራቱም ፡ እጅግ ፡ በ ዚህ ፡ በኵል ፡ ሆነ ። ዛሬ ፡ ሁሉ ፡ ባደ ፡ ነው ፡ ጠበሪያ ፡ ብቻ ፡ በጥብርያደስ ፡ ስፍራ ፡ ትገኛለች ። እርስዋም ፡ ታናሽ ፡ አገ ር ፡ ናት ፡ በመከበብያ ፡ የተከበበች ፡ ፬፻፪፤ ወደስ ፡ ፭፻፪፤ ሰ ዎችም ፡ አሉባት ፡ ከርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ አይሁድ ። ላይሁ ድም ፡ ታላቅና ፡ የከበረ ፡ ማስተማርያ ፡ ከዚህ ፡ አላቸው ። ደግሞም ፡ በቅፍርናሆም ፡ ስፍራ ፡ ዛሬ ፡ ታናሽ ፡ መንደር ፡ ደገኛል ። ሳፊት ፡ በተራራ ፡ ላይ ። ከዚያም ፡ አያሌ ፡ አይ ሁድ ፡ አሉ ። ቃና ፡ በገሊላ ፡ ታናሽ ፡ መንደር ። የሩም ፡ ቤ ተ ፡ ክርስቲያን ።

ሽ ወ መ ር ፡ ታላቅ ፡ መንደር ፡ ብዙ ፡ አታክልት ፡ ወደሉ ።

ኻ ደ ፋ ፡ በከርመል ፡ እግር ፡ በባሕር ፡ ደር ። በከርመል ፡ ተራራ ፡ ላይም ፡ ታላቅና ፡ ያመረች ፡ ገደም ፡ አለች ፡ ወትሩ ፡ ፪፤ ወደስ ፡ ፫፤ የከርመሊቶች ፡ ሞነክሶች ፡ ወደሉባት ።

